Amharic Sermon Book for Christian(Ethiopian) volume 1

Hoching Jung

Created with myebookmaker
www.myebookmaker.com

Table of Contents

Chapter: 1 Information

Chapter: 2 **የመጀመሪያ ሰው አዳም** (**ዘፍ፡** 2፥7)

Chapter: 3 **የመጀመሪያ ሴት ሔዋን** (**ዘፍ፡** 2፥18-23)

Chapter: 4 **ቃየልና አቤል** (**ዘፍ፡** 4፥1-16)

Chapter: 5 **ከእግዚአብሔር ጋር አካሄዱን ያደረገው ሄኖክ** (**ዘፍ፡** 5፥21-24)

Chapter: 6 **ኖኅና የጥፋት ውሃ** (**ዘፍ፡** 6፥13-24)

Chapter: 7 **የእምነት አያት አብርሃም** (**ዘፍ፡** 12፥1-4)

Chapter: 8 **መልካም ሴት የሆነችው ሣራ** (**ዘፍ፡** 17፥15-19)

Chapter: 9 **የዋህ ልጅ ይስሐቅ** (**ዘፍ፡** 26፥23-33)

Chapter: 10 **እስራኤል የሆነው ያዕቆብ** (**ዘፍ፡** 32፥21-30)

Chapter: 11**ባለ ራዕዩ ዮሴፍ** (**ዘፍ፡** 39፥1-6)

Chapter: 12 **የእስራኤል የመጀመሪያ መሪ ሙሴ** (**ዘጸ፡** 3፥1-12)

Chapter: 13 **አረመኔ ጠንቋዩ በለዓም** (**ዘኁ፡** 22፥21-35)

Chapter: 14 **ጠንካራ ሰው ኢያሱ** (**ኢያ፡** 1፥1-11)

Chapter: 15 **የኢያሱስ የቀድሞ አያት የሆነችው ጋለሞታ ረዓብ** (**ኢያ፡** 2፥1-21)

Chapter: 16 **የእግዚአብሔርን ተስፋ ያመነው ካሌብ** (**ኢያ፡** 14፥6-15)

Chapter: 17 **ናዝራዊ የሆነ ሳምሶን** (**መሳ፡** 13፥1-7)

Chapter: 18 **ኑኃሚንን የታዘዘችው ሩት** (**ሩት፡** 1፥6-18)

Chapter: 19 **ልጆቹን ሳያስተምር የወደቀ ዔሊ** (**1ኛ ሳሙ፡** 2፥12-17፤ **ቁ፡** 22-25)

Chapter: 20 **አዲስ መንገድ የከፈተው ሳሙኤል** (1ኛ ሳሙ፡ 3፥19-21)

Chapter: 21 **የመጀመሪያ የእስራኤል ንጉሥ ሳኦል** (1ኛ ሳሙ፡ 11፥6-15)

Chapter: 22 **በእግዚአብሔር መንፈስ የተመረጠ ንጉሥ ዳዊት** (1ኛ ሳሙ፡ 16፥6-13)

Chapter: 23 **ጥበበኛው ንጉሥ ሰለሞን** (1ኛ ነገ፡ 3፥4-15)

Chapter: 24 **ሕያው እግዚአብሔርን የገለጠው ኤልያስ** (1ኛ ነገ፡ 18፥16-24)

Chapter: 25 **ሁለት እጥፍ መንፈስን የፈለገው ኤልሳዕ** (2 ነገ፡ 2፥7-14)

Chapter: 26 **እግዚአብሔርን ያመነ ሕዝቅያስ** (2 ነገ፡ 18፥1-8)

Chapter: 27 **የሃይማኖትን ተሃድሶ ያደረገው ኢዮስያስ** (2ኛ.ነገ.22፥1-11)

Chapter: 28 **ሁለት ጊዜ እስራኤላዊያንን ያስተማረው ዕዝራ** (ዕዝ፡ 7፥5-26)

Chapter: 29 **የኢየሩሳሌምን ቅጥር የገነባ ነህምያ** (ነህ፡ 2፥11-20)

Chapter: 30 **የራሷን አገር የወደደችው አስቴር** (አስ፡ 4፥12-17)

Chapter: 31 **የመከራ ሰው ኢዮብ** (ኢዮ፡ 42፥1-6)

Chapter: 32 **ታላቁ ነቢይ ኢሳይያስ** (ኢሳ፡ 6፥8-13)

Chapter: 33 **የዕንባ ነቢይ ኤርምያስ** (ኤር፡ 1፥4-10)

Chapter: 34 **ባለ ራዕይ ነቢይ ሕዝቅኤል**(ሕዝ፡ 1፥1-3)

Chapter: 35 **በእምነት መንገድ ብቻ የሄደው ዳንኤል** (ዳን፡ 1፥8-21)

Chapter: 36 **የንሰሐ ጥሪ ያደረገው የፍቅር ነቢይ ሆሴዕ** (ሆሴ፡ 1፥2-9)

Chapter: 37 **የነነዌን ከተማ ለማዳን የተመረጠ ነቢይ ዮናስ** (ዮና፡ 2፥1-9)

Chapter: 38 **የእስራኤል እናት ዲቦራ** (መሳ፡ 4፥1-10)

Chapter: 39 **የጌዴዎን መታዘዝና ትህትና** (መሳ፡ 7፥1-8)

© 2017 Hoching Jung. All rights reserved.

ISBN 9781520338712

E-mail: jhc678@gmail.com

መጋቢት 09 January 2017

ምስጋና፡- ከሁሉም በላይ ይህ መጽሐፍ እንዲፃፍና እንዲተረጎም የመራውንና የረዳውን እግዚአብሔር እናመሰግናለን፡፡

በትርጉም ሥራና በእርማት የተባበረውን፡- ወንጌላዊ በቀለ ባንጃን

በኮምፒዩተር ፅሁፍ የረዱትን - እህት ሜዴ እሸቱና እህት

መስከረም ደረጀ እናመሰግናለን፡፡

ይህን መጽሐፍ ለሚያነቡት ወገኖች ሁሉ የበረከት መጽሐፍ እንዲሆንላችሁ ታላቅ ምኞታችን ነው፡፡ በመጽሐፉ ውስጥ ያሉት ጥቅሶች ከ54 **እትምና በ**1993 **ዓ.ም የታተመ አዲሱ መደበኛ ትርጉም መጽሐፍ ቅዱስ ስለሆነ ከ**54 **እትምና ከአዲሱ መደበኛ ትርጉም ስለተወሰደ ሁለቱን በማመሳከር ቢያነብቡት የተሻለ ሀሳብ ታገኛላችሁ፡፡**

ሆችንግ ጃንግ

<u>የብሉይ ኪዳን 38ሌዋውያን</u>

<u>ምዕራፍ አንድ</u>

<u>የመጀመሪያ ሰው አዳም (ዘፍ፡ 2፥7)</u>

<u>የአዳም የሕይወት ታሪክ</u>

ከኃጢያት በፊት የተፈጠሩ

እግዚአብሔር አዳምን ፈጠረ፡፡ (**ዘፍ፡** 1፥27 **ምዕ፡** 2፥7)

አዳም በኤዴን ገነት ውስጥ ይኖራል፡፡ (**ዘፍ፡** 2፥8,9)

አዳም እንዲሰራ የተሰጠው ትዕዛዝ፡፡ (**ዘፍ፡** 2፥16-17)

የአዳም ሚስት ሄዋን መፈጠር፡፡ (**ዘፍ፡** 2፥18-25)

ከኃጢአት በኃላ የተፈጠሩት

የሔዋን ኃጢአት፡፡ (**ዘፍ፡** 3፥1-6)

ከኤዴን ገነት መውጣት፡፡ (**ዘፍ፡** 3፥22-24)

የቃየልና የአቤል መወለድ፡፡ (**ዘፍ፡** 4፥1-2)

ቃየል አቤልን ገደለ፡፡ (**ዘፍ፡** 4፥3-8)

አዳም ሴትን የወለደው በ130**ኛው አመት ሲሆን ነው፡፡** (**ዘፍ** 4፥25)

ሌሎች ልጆችን አዳም ወለደ፡፡ (**ዘፍ** 5፥4)

አዳም በ930 **ዓመት ሞተ፡፡** (**ዘፍ፡** 5፥5)

አዳም ማለት ሰው ማለት ነው፡፡ እግዚአብሔር አዳምንና እንስሳቶችን ከምድር አፈር ፈጠረ፡፡ (ዘፍ 2፥19) **ነገር ግን አዳምን ከፈጠረ በኋላ እግዚአብሔር የራሱን እስትንፋስ እፍ ብሎ ሰጠ፡፡ እግዚአብሔር ለአዳም ልዩ በረከቶችን ምግብ እንዲሆንላቸው በምድር ላይ የሚገኙትን የእህል አዝሪትና ዘር በውስጡ ያለውን ፍሬ የሚያስገኙ ተክሎችን ሁሉ ሰጥቷል፡፡**

እንዲሁም በምድር ላይ ለሚኖሩ እንስሳት ሁሉ በሰማይ ለሚበሩ ወፎች ሁሉ በምድር ላይ በደረታቸው እየተሳቡ ለሚንቀሳቀሱ ፍጥረቶች ሁሉ በአጠቃላይ የሕይወት እስትንፋስ ላለው ሁሉ ምግብ እንዲሆንላቸው ልምላሜ ያለውን ሣርና ቅጠል ሁሉ ሰጣቸው፡፡ (ዘፍ 1፥29-30) የሰንበትንም ቀን ባርኮ ሰጣቸው፡፡ (ዘፍ፡ 2፥3) ደግሞም ልዩ ሆኖ እንዲገኝ በእግዚአብሔር አምሳል ፈጠረ፡፡ (ዘፍ 1፥26) ይህ ማለት ሰው ከሁሉም ፍጥረታት የመጀመሪያ ማለት ነው፡፡ (በመዝ፡ 8፥5-8) ላይ ከመላእክት በጥቂቱ አሳንሶ ሰውን ፈጠረ ይላል፡፡ እግዚ/ር በአለም ላይ የሚገኙትን ፍጥረታትን ሁሉ እንዲመራ ለሰው ስልጣንን ሰጠ፡፡

ደግሞም (በማቴ፡ 16፥26) ላይ የሰው ሕይወት ከዓለም ነገሮች እንደሚበልጥ ለማስረዳት ፈልጎ ኢየሱስ ክርስቶስ ሰው መላው ዓለምን ቢያተርፍ ግን ነፍሱን ግን ቢያጣ ምንም ይጠቅመዋል? በማለት ይናገራል፡፡ እግዚአብሔር ሰውን በመልካችን በአምሳላችን እንሥራ ሲል እግዚአብሔር የራሱን እስትንፋስ መስጠቱን ያመለክታል፡፡ የእግዚአብሔርን እስትንፋስ የተቀበለ ሰው ከሌሎች እንስሳት የሚለየው በመንፈሳዊ ሁናቴ ነው፡፡ የዚህ ትርጉም የሰው ልጆች እግዚአብሔርን የሚያመልኩበት በልባቸው የአምልኮ መንፈስ በመኖሩ ሲሆን ሌሎች እንስሳትም ሆነ ፍጥረታት እግዚአብሔርን የሚያመልኩበት መንፈስ የላቸውም ማለት ነው፡፡ ስለዚህ ሰው ከምድር አፈር ተፈጥሯል ነገር ግን በሰው ውስጥ የእግዚአብሔር መንፈስ አለ፡፡ ሰው በጣም ልዩ የሆነው ለዚህ ነው፡፡

እግዚአብሔር ለአዳም ባርኮ የሰጠው (ዘፍ፡ 2፥17) ላይ መልካሙንና ክፉን ከሚያሳውቅ ዛፍ አትብላ ብሎ ተናገረ፡፡ ይህ ማለት ሰው እንዲታዘዝ የህግ ተስፋ አለው ማለት ነው፡፡ እግዚአብሔር ፈጣሪ ነው ሰው ደግሞ ፍጡር ነው ፡፡ መልካሙንና ክፉውን እንዲያውቅ የተሰጠው የእግዚአብሔር ሕግ ነው፡፡ ነገር ግን ሔዋን በእባብ ተፈትና የእግዚአብሔርን ሕግ ጣሰች (ዘፍ፡ 3፥5) አዳምና ሔዋን እግዚአብሔር የሰጠውን በረከት ስላልፈለጉ ከኤዶን ገነት ሥፍራ ወጡ፡፡

አዳምና ሔዋን ኃጢአት ከሠሩ በኋላ እግዚአብሔር ለእነርሱ ሴት ሰጠ፡፡ ከሴት የሚወለደው ልጅ የደህነትን ተስፋ የመጀመሪያ የፀጋ ኪዳን ሆነ፡፡ (ዘፍ፡ 3፥15) ላይ “የእርሷ ዘር የአንተን ራስ ይቀጠቅጣል፣ አንተም የእርሷን ዘር ተረከዝ ትነክሳለህ” ይህ ማለት በሔዋን ዘር ኢየሱስ ተወልዶ የእባቡን ራስ መምታቱን ሲገልጽ አንተ የሴቱን ተረከዝ ትነክሳለህ ማለት ደግሞ ኢየሱስ በመስቀል ላይ መሰቀሉን ያመለክታል፡፡ ነገር ግን ኢየሱስ ከሶስት ቀን ከመቃብሩ ከተነሣ በኋላ የእባቡን (የሰይጣኑን) ራስ ቀጠቀጠው፡፡ ይህ ማለት በዘፍጥረት መጽሐፍ እግዚአብሔር ለእኛ የሰጠው የመጀመሪያ ተስፋ ማለት ነው፡፡

ደግሞም ከአዳም ኃጢአት በኋላ እግዚአብሔር ለአዳም የእንስሳትን ቆዳ አዘጋጅቶ እራቁቱን ሸፈነ፡፡ (ዘፍ፡ 3÷21) ይህ ማለት እግዚአብሔር እንስሳትን ገድሎ ደም ማፍሰሱ በተዘዋዋሪ ኢየሱስ ስለ ኃጢአተኞች የራሱን ደም አፍስሶ ኃጢአታቸውን ሁሉ ይቅር ማለቱን ይገልፃል፡፡ (ዕብ፡ 9÷12-14,22) አዳምና እኛ በሰራነው ኃጢአት ምክንያት ሞት እርግማን ሕመምና ድካም … ወዘተ ሁሉ መጣ፡፡ ነገር ግን ኢየሱስ ከሞት ከተነሣ በኋላ ሁሉንም ኃጢአት ይቅር ብሎ አዲስ ፀጋን ሰጠ፡፡ (ማቴ፡ 11÷28-30፤ ሮሜ፡ 5÷18፤ ምዕ፡ 6÷23) የመጀመሪያ አዳም ሕያው ነፍስ ፍጡር ሲሆን ሁለተኛ አዳም (ኢየሱስ) ሕይወትን የሚሰጥ መንፈስ ነው፡፡ (1 ቆሮ፡ 15÷45)

ምዕራፍ ሁለት

የመጀመሪያ ሴት ሔዋን (ዘፍ፡ 2፥18-23)

ከኃጢያት በፊት

ሔዋን ከአዳም አጥንት ተፈጠረች፡፡ (ዘፍ፡ 2፥18-22)

ሔዋን በኤዴን ገነት ቦታ ትኖራለች፡፡ (ዘፍ፡ 2፥23-25)

ከኃጢያት በኃላ

የእባብ ፈተና ኃጢአትን እንዲሠሩ አደረገ፡፡ (ዘፍ፡ 3፥1-6)

ሔዋን ኃጢአት ከሠራች በኃላ ከገነት ቦታ ወጣች፡፡ (ዘፍ፡ 3፥22-24)

ሄዋን ቃየልንና አቤልን ወለደች (ዘፍ.4÷1-2)

ቃየል አቤልን ገደለ ((ዘፍ.4÷3-8)

ሄዋን ሴትን ወለደች ((ዘፍ.4÷25)

ሄዋን ሌሎችንም ልጆች ወለደች (ዘፍ.5÷4)

በዘፍጥረት ምዕራፍ 1 ውስጥ “መልካም” የሚለው ቃል 6 ጊዜ ተጽፎል፡፡ ነገር ግን በምዕራፍ 2 ላይ “መልካም አይደለም” የሚለው ቃል 1 ጊዜ ብቻ ተጽፎል፡፡ ይህ ማለት እግዚአብሔር ሁሉንም ነገር የሠራው መልካም እንደ ሆነ ማየቱን ይገልፃል፡፡ ነገር ግን አዳም ብቻውን ይሆን ዘንድ መልካም አይደለም አለ፡፡ ሰለዚህ እግዚአብሔር ለአዳም ሔዋንን ሰጠ፡፡ እግዚአብሔር ከአዳም ጐን አጥንት ወስዶ ሴት አድርጐ ሠራ፡፡ አዳምም እንዲህ አለ “ይህች አጥንት ከአጥንቴ ሥጋም ከሥጋዬ ናት” ይህ ማለት ከጐኑ አጥንት የተወሰደ ሰውና ሴት እኩል መሆናቸውን ይገልፃል፡፡ ምክንያቱም እግዚአብሔር ሔዋንን ሲሠራ ከራስና ከእግር አጥንት ወስዶ አላደረገም፡፡

ያ ቢሆን ሰውና ሴት እኩል አይሆኑም ነበር፡፡ ነገር ግን ከጐኑ አጥንት ወስዶ መሥራቱ ለነፍስ ቅርብ ስለሆነ እኩልነታቸውን ይገልፃል፡፡ ሴት የሰው ክብር ስትሆን ከሰው ጋር ተረዳድተው እንዲኖሩ እግዚአብሔር ይፈልጋል፡፡ ስለዚህ እርስ በርሳቸው በፍቅር እንዲሰሩ እግዚአብሔር ፈጠራቸው፡፡

“ሔዋን” ማለት ሕያው ፍጡር ማለት ነው፡፡ (ዘፍ፡ 3፥20) “አዳም” ማለት ሰው ማለት ነው፡፡ ደግሞም ሔዋን ማለት ሕያው ማለት ነው፡፡ ስለዚህ ሁለቱ ባንድ ላይ “ሕያው ሰው” ማለት ነው፡፡ ሴት ሳትፈጠር አዳም ሰው አልነበረም፡፡ ስለ ሴት ሰው

ይኖራል፡፡ ሰው ያለ ሴት አይኖርም፡፡ ደግሞም ሴት ያለ ረዳት አትኖርም፡፡ ይህ ማለት እግዚአብሔርን ለመታዘዝ ምንጩ ቤተሰብ ማለት ነው፡፡ ሔዋን ከእባብ (ከሰይጣን) ፈተናውን ተቀብላ የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ ረስታ ኃጢአትን አደረገች፡፡ በኋላም መልካሙንና ክፋውን ከሚያሳውቅ ዛፍ ፍሬ በልታ ለአዳም ሰጠች አዳምም በላ፡፡ ሔዋን መልካሙንና ክፋውን ከሚያሳውቅ ዛፍ ፍሬን የወሰደችው ለእይታ የሚያምር ስለሆነ ነው፡፡ (ዘፍ፡ 3÷6) “ሴቲቱም” ወይም ሔዋን ዛፉ የሚያምር ፍሬውም ለመብላት የሚያስጐመጅና ጥበብን የሚያስገኝ እንደሆነ ባየች ጊዜ ፍሬውን ወስደ በላች፡

ሔዋን በአይን አምሮት በሥጋ ምኞትና በመንፈስ ምኞት ፈተና ተፈተነች፡፡ እግዚአብሔር አትብሉ ያለውን ሕግ ባለመታዘዝ ሁለቱም ተፈተኑ፡፡ ሐዋርያው ዮሐንስ ሲናገር የሥጋ ምኞትና የዓይን አምሮት የኑሮ ትምክህት ከዓለም ነው አለ፡፡ (1ኛ ዮሐ፡ 2÷16) ነገር ግን ሔዋን ከእግዚአብሔር ቃል ወይም ሕግ እነዚህን አብልጣ አየች፡፡ እኛም ከእግዚአብሔር ቃል የሥጋ ምኞት የዓይን አምሮት የኑሮም ትምክህት ከእግዚአብሔር ሕግ አብልጠን እንዳናይ ልንጠነቀቅ ያስፈልጋል፡፡

ምዕራፍ ሶስት

ቃየልና አቤል (ዘፍ፡ 4፥1-16)

የቃየል መወለድ፡፡ (ዘፍ፡ 4፥1)

ቃየል ገበሬ ነው፡፡ (ዘፍ፡ 4፥2)

ቃየል ከእርሻ ፍሬ በኩራቱን ለእግዚአብሔር የሰጠ ሰው ነው፡፡ (ዘፍ፡ 4፥3)

ቃየል ታናሽ ወንድሙን አቤልን ገደለ፡፡ (ዘፍ 4፥8)

በቃየል ላይ የእግዚአብሔር ፍርድ፡፡ (ዘፍ፡ 4፥9-15)

ቃየል በኖድ ምድር ተቀመጠ፡፡ (ዘፍ፡ 4፥16)

ቃየል ልጆችን ወለደ፡፡ (ዘፍ(ዘፍ.4÷1-2)፡ 4፥17)

አዳምና ሔዋን ከኤዴን ገነት ወጡ፡፡ ነገር ግን እግዚአብሔር በረከትን ሰጣቸው፡፡ ቃየል ማለት መቀበል ማለት ሲሆን አቤል ማለት እስትንፋስ ማለት ነው፡፡ ይህ ማለት እግዚአብሔር በረከትን ሰጠ ማለት ነው፡፡ የእነዚህ የሁለት ወንድሞች ሥራ የታላቁ የቃየል ሥራ እርሻ የሚያርስ ገበሬ፣ ሁለተኛው የአቤል ሥራ በግ የሚያረባ ሰው ነው፡፡ ቃየል ከምድር ፍሬ ለእግዚአብሔር በኩራት ሲሰጥ አቤል ከበጎቹ የሰባውን የመጀመሪያውን በግ ለእግዚአብሔር ሰጠ፡፡ ነገር ግን እግዚአብሔር ወደ ቃየልና ወደ መስዋዕቱ አልተመለከተም፡፡ ወደ አቤልና ወደ መስዋዕቱ ተመለከተ፡፡ ምክንያቱም (ዕብ፡ 11፥4) **ላይ ‘‘አቤል ከቃየል መስዋዕት የሚበልጠውን መስዋዕት ለእግዚአብሔር ያቀረበው በእምነት ነው” ይላል፡፡**

ይህ ማለት አቤል ያቀረበው መሥዋዕት በፍጽም እምነት ነበር፡፡ ነገር ግን ቃየል ያቀረበው መሥዋዕት ያለእምነት ነበር:: ብዙ ክርስቲያኖች ለእግዚአብሔር መስዋዕት ሲያቀርቡ ያለ እምነት ያቀርባሉ ነገር ግን እግዚ/ር አምልኮአቸውን አይቀበልም፡፡ ቃየል ራሱን የማይወድና የማይጠግብ ሰው ነው፡፡ በዚህ ምክንያት ታናሽ ወንድሙን አቤልን ተቆጥቶ ወደ ሜዳ በመውሰድ ገደለ፡፡

እግዚአብሔር ቃየልን ስለ ወንድሙ “ያንተ ታናሽ ወንድም አቤል የት ነው ያለው” ብሎ ጠየቀ (ዘፍ፡ 3፥9) **በተመሳሳዩም እግዚአብሔር አዳምን ወዴት ነህ ያለህው ብሎ ሲጠይቅ እርሱም በገነት ድምፅህን ሰማሁ እራቆቴንም ስለሆንኩ ፈራሁ ተሸሸግኩ አለ**

እንደዚህ አይነት ጥያቄ በእኛም በብዛት የሚታይ ነው ዛሬም እግዚአብሔር እኛን ወዴት ናችሁ? ብሎ ይጠይቀናል ለቃየል የቀረበው ጥያቄ ዛሬ እኛንም ሚመለከት ነው እኛ ከቤተሰቦቻችን ጋር ከጎረቤቶቻችን ጋር በፍቅርና በሰላም እንኖራን?

የአቤል ደም የጽድቅ ሰው ደም የሚወክል ነው፡፡ ኢየሱስ በማቴ፡ 5፥10-12 ላይ “ስለ ጽድቅ የሚሰደዱ የተባረኩ ናቸው፡፡ መንግሥተ ሰማያትም የእነርሱ ናትና” ብሎ ተናገረ፡፡ ቃየል አቤልን ስለገደለ እግዚአብሔር እርሱን ሲወቅስ ኃጢአቱን ሸሽጐ ስለ ኃጢአቱ ንሰሐ አልገባም፡፡ በ1ኛ ዮሐንስ 1፥9 ላይ “በኃጢአታችን ብንናዘዝ ኃጢአታችንን ይቅር ሊለን ከአመፃም ሊያነጻን የታመነ ነው” ይላል፡፡

ይህ ማለት እኛ ስለኃጢአታችን ንሰሐ ብንጠይቅ የእኛ ኃጢአት ይቅር ይባላል ማለት ነው፡፡ ቃየል ከእግዚአብሔር በሕይወት እንዲኖር የሚያደርገውን ፀጋ ተቀበለ፡፡ ነገር ግን እርሱ ንሰሐ ስላልገባ የዘላለም ሕይወትን አያገኝም፡፡ ለኛ እግዚአብሔር በዓለም ላይ እንዲንኖር በረከትንንና የዘላለም ሕይወትን ይሰጠናል:: ነገር እኛ የአለምን በረከት ብቻ መፈለግ ጥሩ እንዳልሆነ ልናስተውል ያስፈልጋል፡፡ (1ኛ ጢሞ፡ 6፥17-19)

ምዕራፍ አራት

ከእግዚአብሔር ጋር አካሄዱን ያደረገው ሄኖክ (ዘፍ፡ 5፥21-24)

ሄኖክ የኖረበት ዘመን የጨለማ ዘመን ነው፡፡ ሄኖክ ማቱሳላን ከወለደ በኋላ 300 ዓመት ከእግዚአብሔር ጋር እየሠራ የኖረ ሰው ነው፡፡ ማቱሳላ ማለት ወደፊት ከሞት ይመለሳል ማለት ነው፡፡ ይህ ማለት ከማቱሳላ እድሜ ጀምሮ የሚሆን ነው ማለት ነው፡፡ የማቱሳላ ዘመን ብዙ የጥፋት ውሃ በሀጥያተኞች ላይ የሚዘንብበት ወቅት ነው፡፡ ማቱሳላ እንደሞተ ኖህም መርከብ ሰርቶ ከጨረሰ በኃላ የጥፋት ዝናብ ከሰማይ ወርዶ ሕዝቡን አጠፋ፡፡ ሄኖክ በዘመኑ በውጪና በውስጥ የሚሰራ ሰው ነው፡፡

በሄኖክ ዘመን ሁሉም ሰዎች ከእግዚአብሔር ጋር አካሄዱን አላደረጉም:: ስለዚህ ሄኖክ ከእግዚአብሔር ጋር አካሄዱን ስላደረገ እግዚአብሔር ተደስቷል፡፡ ሄኖክ ከእግዚአብሔር ጋር አካሄዱን እንዴት አደረገ? መልሱ ሄኖክ በእምነት ከእግዚአብሔር ጋር አደረገ፡፡ (ዕብ.11፥5) **ሄኖክ እግዚአብሔርን በእምነት የሚያስደስት እንደፈቃዱ ከእርሱ ጋር የሚኖር ሰው ነው፡፡**

ሄኖክ የእግዚአብሔርን ፈቃድ በፍፁም ልብ መታዘዙን በፍፁም ተስፋ በእግዚአብሔር ፊት መመላለሱንና በብዙ ችግሮችና ኃጢያተኞች መካከል መኖሩን ለእግዚአብሔር አልሸሸገም:: እርሱ ስለእምነት ብዙዎች በሚያሳድዱበት ጊዜ ሳይፈራ የእግዚአብሔር ፍርድ መኖሩን ለህዝቡ የሚያስጠነቅቅ ነው፡፡ ሄኖክ ለሰዎች የእግዚአብሔርን ፍርድ "እነሆ እግዚአብሔር እልፍ አላፋት ቅዱሳን መላእክት ጋር ሆኖ በሁሉም ላይ ለመፍረድ ይመጣል ብሎ ተናገራቸው፡፡ (ይሁዳ 1፥14-15)

ሄኖክ ሳይሞት ወደ እግዚአብሔር የሄደ ሰው ነው፡፡ የክፋት ዘመን ከመምጣቱ በፊት እግዚአብሔር ሄኖክን ወሰደ:: "ጻድቅ ይሞታል በልቡም ነገርን የሚያኖር የለም ምህረተኞችም ይወገዳሉ ጽድቅም በክፋት ፊት እንደተወገደ ማንም አያስተውልም ወደ ሰላም ይገባል በቅንነት የሄደ በአልጋው ላይ ያርፋል፡፡" (ኢሳ፡ 57፥1-2) **ይህ ማለት ሄኖክ ሳይታመም ተወሰደ ማለት ነው፡፡ ሄኖክ የመጨረሻ ፍርድ ከመምጣቱ በፊት ወደ እግዚአብሔር እንደ ተወሰደ ኢየሱስ ዳግመኛ በሚመለስበት ጊዜ ያመኑት ሰዎች እንደ ሄኖክ ይወሰዳሉ ማለት ነው፡፡**

እኛ ደግሞ እንደ ሄኖክ ከእግዚአብሔር ጋር አካሄዳችንን አድርገን ከመጨረሻው ከፍርዱ ሰዓት እንድናመልጥ እምነት ሊኖረን ያስፈልጋል፡፡ ስለዚህ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በሚመለስበት ጊዜ እሱን ያላመኑ ሰዎች ስለሚፈረዱ እኛ ያመንን ሰዎች ከፍርድ ስለምናመልጥ ከኢየሱስ ጋር ለዘላለም እንኖራለን፡፡

ምዕራፍ አምስት

ኖኅና የጥፋት ውሃ (ዘፍ፡ 6፥13-24)

የጥፋት ውሃ ከመምጣቱ በፊት

የኖኅ ልደት፡፡ (ዘፍ፡ 5፥28-29)

የኖህ ዘመን ሰዎች ብዙ ኃጢአት ይሠራሉ፡፡ (ዘፍ፡ 6፥1-25)

ኖኅ ጻድቅና ፍጹም ሰው ነው፡፡ (ዘፍ፡ 6፥9)

ኖኅ ሦስት ልጆችን ወለደ፡፡ (ዘፍ፡ 6፥10)

ኖኅ እድሜው 480 ሲሆነው የመርከቡን ስራ ጀምሮ በ120 አመት ቆይታ መርከብን አጠናቀቀ፡፡ (ዘፍ.6፥13-16)

ኖኅና የኖኅ ቤተሰብ በ600 ዓመት ላይ ወደ መርከብ ገቡ፡፡ (ዘፍ፡ 7፥1-9)

የጥፋት ውሃ ከወረደ ወይም ከዘነበ በኃላ

የጥፋት ዝናብ በ600ኛ ዓመት ዘነበ፡፡ (ዘፍ፡ 7፥11,17)

በ601ኛው ዓመት ከኖህ መርከብ ሰዎችና የተለያዩ እንስሳት ዝናቡ ካቋረጠ በኋላ ወጡ፡፡ (ዘፍ፡ 8፥15-19)

በ601ኛው ዓመት ኖህና ቤተሰቡ ከመርከብ ከወጡ በኋላ የምሥጋና መስዋዕት ለእግዚአብሔር አቀረቡ፡፡ (ዘፍ፡ 8፥20,21)

እግዚአብሔር ለኖህ የቀስተ ደመና ቃል ኪዳን ሰጠ፡፡ (ዘፍ፡ 9፥8-17)

የመጠጥ ሁናቴ (ዘፍ፡ 9፥20-27)

ኖኅ በ950ኛው ዓመት ሞተ (ዘፍ፡ 9፥28,29)

ኖኅ ማለት (ዘፍ፡ 5፥29) "ይህ ልጅ እግዚአብሔር በረገማት ምድር ላይ ከብርቱ ሥራችን ያሳርፈናል" ማለት ነው፡፡ እንደስያሜው ኖኅ የሰው ችግርን የሚያሳርፍ ሰው ሆኖ አደገ፡፡ ኖኅ የኖረበት ዘመን ሰዎች ኃጢአትን የሚያደርጉበት ነው፡፡ እግዚአብሔር በምድር ላይ ያሉ ሰዎች ሁሉ ምን ያህል ዐመፀኞች እንደሆኑና ሐሳባቸውም ዘወትር ክፉት ብቻ እንደሆነ ተመለከተ፡፡ ስለዚህ ሰዎችን በመፍጠሩና ከምድር ላይ እንዲኖሩ በማድረጉ አዘነ፤ እጅግም ተቆጣ፡፡ (ዘፍ፡ 6፥5-6)

ደግሞ ምድር በሰዎች የዐመፅ ሥራ ስለተሞላች የሰውን ዘር ለማጥፋት ወስኛለው አለ፡፡ (ዘፍ፡ 6÷13) እግዚአብሔር የሰውን ኃጢአትና ክፋት ይፈርዳል፡፡

ኖኅ በዘመኑ ጻድቅና ፍጹም ሰው ነው፡፡ ይህ ማለት ኖኅ በእግዚአብሔር ላይ በፍጹም ታምኖ ይኖራል ማለት ነው፡፡ ኖህ ከእግዚአብሔር ሞገስን የተቀበለ (ዘፍ፡ 6÷8) ደግሞ ጻድቅና ፍጹም (ዘፍ፡ 6÷9) በእግዚአብሔርም መንገድ የሚሄድ (ቁ.9) ፍርዱንም አውቆ መርከብን ያዘጋጀና (ዕብ፡ 11÷7) ስለ ጽድቅ የሚሰብክ ሰው ነው፡፡ (2ጴጥ፡ 2÷5) የኖኅ ዘመን ኃጢአትን የሚሠሩና አመንዛሪዎች በጥላቻ የሚኖሩ ሰዎች የበዙበት ዘመን ነው፡፡

የእግዚአብሔር ፈቃድ ሰዎችን ከፍርድ ማዳን ነው፡፡ ስለዚህ እግዚአብሔር ስለኃጢአተኞች አዝኖ 120 ዓመት ሙሉ የንሰሐ ጊዜ ሰጥቶ ጻድቅ ኖኅ ከእግዚአብሔር ፍርድ እንዲድኑ እንድሰብክ አደረገ፡፡ ነገር ግን ንስሐ የገባ ሰው የለም፡፡ (ማቴ፡ 24÷38-39)

እግዚአብሔር ለኖኅ መርከብን እንድያዘጋጅ ትዕዛዝ ሰጠ፡፡ የኖኅ መርከብ ማለት የመዳን ጀልባ ማለት ነው፡፡ ደግሞም ቤተክርስቲያን ለዘላለም ኢየሱስ ክርስቶስ በስጋ በኩል በመስቀል ላይ ያደረገው የደህንነትን መንገድ የምትሰብክ ናት፡፡ ኖኅ በመርከብ ውስጥ አታክልቶችን ለመስዋዕት የሚሆኑ እንስሳትን ሰብስቦ ይዟል ይህ የሚገልፀው ቤተክርስቲያን የዘላለም ምግብ ሰብስባ የያዘች መሆኑን ነው፡፡

ኖኅ በመርከብ ውስጥ ያስቀመጣቸው ሁለት ወሳኝ ነገሮች

አታክልቶች የዚህ ትርጉም የዘላለም ህይወት የሚሰጥ ማለት ነው፡፡

ለመስዋዕት የሚሆኑ እንስሳት የዚህ ትርጉም ኢየሱስ ስለ አለም ሁሉ ኃጢያት ሰዎችን ለማዳን የመጣ ማለት ነው፡፡

የመርከቡን በር እግዚአብሔር ራሱ ዘጋ፡፡ እንደዚሁም የቤተክርስቲያን በር የሚዘጋና የሚከፍት እርሱ ነው፡፡ የኖህ መርከብ መሪና የንፋስ መቆጣጠርያ የሌለው ጀልባ ነው፡፡ ምክንያቱም የመርከብ መሪ እግዚአብሔር ነውና፡፡ ደግሞም ቤተክርስቲያን እግዚአብሔርን በፍጹም ልብ በማመን በእግዚአብሔር መመራትና መታዘዝ አለባት፡፡

ኖኅ በዕድሜው መጨረሻ አካባቢ የወይን ጠጅ ስለጠጣ ራቁቱ ተጋልጦ ነበር፡፡ ይህ የሚያሳየው ሰው ሁሉ ኃጢያተኛ መሆኑን ነው፡፡ እኛ ደግሞ ሁልጊዜ ከእግዚአብሔር ቀድመን እንዳንወጣና ሰይጣንም ወደ እኛ እንዳይገባ ልንጠነቀቅ ያስፈልጋል፡፡ (1ጴጥ፡ 5÷8)

ምዕራፍ ስድስት

የእምነት አያት አብርሃም (ዘፍ፡ 12፥1-4)

አብርሃም በኡር ከለዳውያን ተወለደ፡፡ (ዘፍ፡ 11፥26-27)

ይስሐቅ ከመወለዱ በፊት

እግዚአብሔር ለአብርሃም ከሀገርህ ከዘመዶችህ ከአባትህ ቤት እኔ ወደማሳይህ ቦታ ውጣ የሚል ተልዕኮ ሰጠ፡፡ (ዘፍ፡ 12፥1-9፤ የሐዋ፡ 7፥3)

አብርሃም ከኡር ከለዳውያን ወደ ካራን ሄደ፡፡ (ዘፍ፡ 11፥31)

የአብርሃም አባት ታራ መሞት፡፡ (ዘፍ፡ 11፥32)

አብርሃም ከካራን በ75 **ዓመቱ ወደ ከነዓን ሄደ፡፡** (ዘፍ፡ 12፥1-4)

አብርሃም ከሎጥ ተለየ፡፡ (ዘፍ፡ 13፥1-3)

አብርሃም በ84 **ዓመቱ የአጎቱን ልጅ ሎጥን ለማዳን ሠራዊቱን ይዞ ወጣ፡፡** (ዘፍ፡ 14፥13-16)

አብርሃም የቾቦ ክዳን አደረገ፡፡ (ዘፍ፡ 15፥1-16)

አብርሃም በ86 **ዓመቱ እስማኤልን ወለደ፡፡** (ዘፍ፡ 16፥1-6)

አብርሃም በ99 **ዓመቱ የግርዘትን ኪዳን አደረገ፡፡** (ዘፍ፡17፥1-14)

አብርሃም በ100 **ዓመቱ ይስሐቅን ወለደ፡፡** (ዘፍ፡ 21፥1-7)

አብርሃም ከአቤሜለክ ጋር ቃል ኪዳን አደረገ:: (ዘፍ፡ 21፥22-24)

አብርሃም በሞሮ ተራራ ላይ ለእግዚአብሔር መስዋዕት አቀረበ፡፡ (ዘፍ፡ 22፥1-19)

የአብርሃም እድሜው 137 **ሲሆን ሚስቱ ሣራ ሞተች፡፡** (ዘፍ፡ 23፥1-20)

የአብርሃም እድሜው 140 **ሲሆን ልጅ ይስሐቅ ሚስት አገባ፡፡** (ዘፍ፡ 24፥1-64)

አብርሃም በ175 **ዓመቱ መሞትና መቀበሩ፡፡** (ዘፍ፡ 25፥7-10)

አብራም ማለት ታላቅ አባት ማለት ሲሆን የሁለተኛ አብርሃም የብዙ ሕዝብ አያት ማለት ነው፡፡ አብርሃም የእስራኤል ሰዎች አያትና ለሁሉ ክርስቲየኖች የእምነት አያት ማለት ነው፡፡ (ሮሜ፡ 4፥11) በአብርሃም ዘመን ብዙ ሰዎች ጣኦት አምላኪዎች ነበሩ፡፡ ነገር ግን አብርሃም ብቻውን እግዚአብሔርን የሚያመልክ ሰው ነው፡፡ (ያዕ፡ 2፥23) ላይ አብርሃም የእግዚአብሔር ወዳጅ ተብሏል፡፡ እግዚአብሔር አብርሃምን ሲጠራ በእምነት ተቀብሎ ወዴት እንደሚሄድ ሳያወቅ ታዘዘ፡፡ (ዕብ፡ 1፥8)

አብርሃም እግዚአብሔርን አምኖ በፍጹም ለመከተል ታዛዥ ሆነ፡፡ ስለዚህ አብርሃም የእምነት አያት ሆነ፡፡ በእምነትም ኖረ፡፡ ነገር ግን የማይታዘዝ ሰው ሥር እያለው ቅርንጫፎቹ የደረቀ ዛፍ ይመስላል፡፡ ፍሬ የሌላት ዛፍ ኢየሱስ እንደረገማት ይደርቃል፡፡ (ያዕ፡ 2፥17,26) እምነት እያለ ነገር ግን ሥራ ከሌለ የሞተ ነው፡፡ ይህ ማለት የሞተ እምነት ማለት ነው፡፡ አንድ ሰው ጥሪውን ተቀብለው ሁል ጊዜ ለመታዘዝ ውሳኔ ማድረግ አለበት፡፡ ለመታዘዝ ዋና ነገሩ ወይም ቁልፉ እምነት ነው፡፡

ያለ እምነት መታዘዝ አይቻልም፡፡ እግዚአብሔር አብርሃምን ለመፈተን ይስሐቅን ሰዋው ብሎ ነበር፡፡ አብርሃም ይስሐቅን ለእግዚአብሔር ሰጠ፡፡ አብርሃም ይህንን በማድረጉ የእምነት ምንጭ ሆነ፡፡ (ዘፍ፡ 22፥12) አብርሃም የጥሩ ሰው አያትና የክርስቶስ አያት ነው፡፡ (ማቴ፡ 1፥1) ለሁሉም ክርስቲያኖች የእምነት ምንጭ ነው፡፡ (ዕብ፡ 11፥8-9)

አብርሃም ሁሉንም ነገር በኡር ከለዳዊያን ትቶ የእምነትን መንገድ ሲሄድ እግዚአብሔር የበረከትን ተስፋ ሰጠ፡፡ (ዘፍ፡ 12፥2-3)

እግዚአብሔር በረከትን የሚሰጠው ደረጃ በደረጃ ነው፡፡

> መጀመሪያ የሚያምኑ ሰዎች በረከትን ይቀበላሉ፡፡ እግዚአብሔር የተናገረውን እናንተ ምትባርኩትን እኔ እባርካለሁ አለ፡፡
>
> በረከትን ለመከፋፈል እምነት ያስፈልጋል፡፡ እግዚአብሔር ሲናገር “አንተ የበረከት ምንጭ ትሆናለህ” አለ፡፡
>
> ሌሎች ሰዎች ካንተ በረከትን ይቀበላሉ፡፡ እግዚአብሔር ሲናገር “ካንተ በረከትን ይቀበላሉ” አለ፡፡

እግዚአብሔር ራብተኞችን መርጦ ብዙ እምነትን ሰጠ፡፡

(ያዕ፡ 2፥5)

እምነት የብዙ መዝገብ ቢሮ ቁልፍ ነው፡፡ ስለዚህ እምነት በረከትን ለመቀበል ምንጭ ነው፡፡

አብርሃም በመንገዱ የሚመጡ እንግዶች ሰዎች ናቸው ብሎ ወደ ቤቱ ጋብዞ ሲያስተናግድ በድንገት መላእክትን አገለገላቸው፡፡ (ዕብ፡ 13፥2) **እኛ ደግሞ እንግዶችን እያገለገልን የእግዚአብሔርን ፀጋና በረከት ለመቀበል እርግጠኞች ልንሆን ያስፈልጋል፡፡** (ዘፍ.11፥1-21)

ምዕራፍ ሰባት

መልካም ሴት የሆነችው ሣራ (ዘፍ፡ 17፥15-19)

ይስሐቅን ከመውለዷ በፊት

ሣራ በኡር ከለዳውያን ተወለደች፡፡ (ዘፍ፡ 11፥28-29)

ሣራ አብርሃምን አገባች፡፡ (ዘፍ፡ 11፥29)

ሣራ ከአብርሃም ጋር በ65 **ዓመቷ ወደ ከነዓን ተጓዘች፡፡** (ዘፍ፡ 12፥4-5)

የሣራ በግብፅ ሀገር ጭንቀት፡፡ (ዘፍ፡ 12፥10-16)

የሳራ ዕድሜ 76 **ሲሆን አገልጋዮዋን አጋርን ለአብርሃም ሰጥታ እስማኤል እንዲወለድ አደረገች፡፡** (ዘፍ፡ 16፥1-16)

እግዚአብሔር ለሣራ በ89 **ዓመቷ ልጅ እንደሚሰጣት ትንቢት ተናገረ፡፡** (ዘፍ፡ 17፥15-22)

በገራራ ሀገር ሣራ በእንግድነት ተቀመጠች፡፡ (ዘፍ፡ 20፥1-18)

ሣራ በ90 **ዓመቷ ይስሐቅን ወለደች፡፡** (ዘፍ፡ 21፥1-7)

ሣራ በ127 **ዓመቷ መሞትና መቀበር፡፡** (ዘፍ፡ 23፥1-20)

የዕብራውያን መጽሐፍ ፀሐፊ በጣም ኃይለኛ አማኝ የሆነችውን ሣራን እንዲህ በማለት ያመሰግናታል፡፡ (ዕብ፡ 11፥11) **“ሣራም ተስፋ የሰጣት እግዚአብሔር ታማኝ መሆኑን ስላወቀች ምንም እንኳ በእድሜ በመግፋቷ መውለድ የማትችል ብትሆን የመፀነስን ኃይል ያገኘችው በእምነት ነው፡፡”** (**1ኛ ጴጥ፡** 3፥6)

ላይ ሣራ አብርሃምን ጌታዬ ብላ እንደታዘዘች ይናገራል፡፡ ነገር ግን የእግዚአብሔር ተስፋ የዘገየ ስለሚመስላት አገልጋዮዋን አጋርን ለአብርሃም ሰጥታ እስማኤል እንዲወለድ አደረገች፡፡ (ዘፍ፡ 16፥1-3) **ሳራ የእግዚአብሔርን ተስፋ እስከ መጨረሻ ድረስ ሳትጠብቅ አጋርን ለአብረሃም በመስጠቷ ኃጢያት ሰራች፡፡ ከዚህ የተነሳ ለእስማኤል መወለድ ምክንያት ሆነች፡፡**

እግዚአብሔር ለሣራ ሁለት ዓይነት ፀጋ ሰጣት፡፡

1ኛ/ **የማይቀየር ፀጋ**

2ኛ/ በ90 **ዓመቷ ሣራ ይስሐቅን እንድትወልድ የሚያደርግ ፀጋ ተቀበለች፡፡** (**ዘፍ፡** 18፥10፤ **ሮሜ፡** 9፥7)

ይህም እግዚአብሔር የሰጠው የተስፋ ቃል “የዛሬ ዓመት በዚህ ጊዜ መጣለሁ ሣራም ወንድ ልጅ ትወልዳለች” የሚል ነበር፡፡ ሣራ አጋርንና እስማኤልን ከቤቷ አሰናበተች፡፡ (**ዘፍ፡** 21፥8-14) **ይህ ማለት በመጽሐፍ ቅዱስ ዳግመኛ ያልተወለዱ ሰዎችና ዳግመኛ ከተወለዱ ከመንፈሳዊ ሰዎች ጋር የሰማይን በረከት አይቀበሉም ማለት ነው፡፡** (**ገላ፡** 4፥28-31)

ምዕራፍ ስምንት

የዋህ ልጅ ይስሐቅ (ዘፍ፡ 26፥23-33)

በህፃንነት ጊዜ

ይስሐቅ እንደ ተስፋ ቃል ተወለደ፡፡ (ዘፍ፡ 21፥1-7)

የይስሐቅ በዓል፡፡ (ዘፍ፡ 21፥8)

በወጣትነት ጊዜ

አብርሃም ይስሐቅን ለመስዋዕት አቀረበ፡፡ (ዘፍ፡ 22፥1-19)

በጎልማሳነት ጊዜ

ይስሐቅ ዕድሜው 37 **ዓመት ሲሆን እናቱ ሣራ ሞተች፡፡** (ዘፍ፡ 23፥ 1-20)

ይስሐቅ በ40**ኛው ዓመት ርብቃን አገባ፡፡** (ዘፍ፡ 24፥1-64)

ይስሐቅ በ60**ኛው ዓመት መንትያዎችን ዔሳውንንና ያዕቆብን ወለደ፡፡** (ዘፍ፡ 25፥21-26)

የይስሐቅ አባት አብርሃም የይስሐቅ ዕድሜ 75 **ሲሆን ሞተ፡፡** (ዘፍ፡ 25፥7-10)

ይስሐቅ ከእግዚአብሔር ጋር ቃል ኪዳን አደረገ፡፡ (ዘፍ፡ 26፥1-5)

ይስሐቅ ከአቤሜለክ ጋር ቃል ኪዳን አደረገ፡፡ (ዘፍ፡ 26፥26-33)

በሽማግሌነት ጊዜ

ይስሐቅ በ133 **ዓመት ያዕቆብ የመጀመሪያ ልጅ እንዲሆን ባረከ፡፡** (ዘፍ፡ 27፥20-30)

ያዕቆብ ወደ ሐራን (መሰጸጦምያ) መሄድና መመለስ፡፡ (ዘፍ፡ 28፥1-5፤ ምዕ፡ 31፥33፤ ምዕ፡ 33፥17)

ያዕቆብ በ180 **ዓመቱ ሞተ** (ዘፍ.35፥28-29)

ይስሐቅ በዘፍጥረት 26፥25 **ላይ እንደተፃፈው ቃል መሠረት ለእግዚአብሔር መሰዊያ ሠርቶ ሰገደ፡፡ ይህ ማለት የይስሐቅ የሃይማኖት ሁኔታን የሚገልጽ ነው፡፡ ድንኳኑን ተከለ ማለት የቤተሰብን ሕይወት የሚገልጽ ነው፡፡ ይስሐቅ አንድ ሚስት ርብቃን ብቻ አግብቶ ጽድቅ አደረገ፡፡ ከጉድጓድ ውሃ መቅዳት ማለት የሥራ ሕይወትን የሚያሳይ**

ነው፡፡ የውሃ ጉድጓድ አምስት ጊዜ ቆፈረ፡፡ ሦስቱን ጉድጓዶች ሌሎች ሰዎች ተከራክረው ወሰዱ፡፡ የዚህ ትርጉም ከሌሎች ሰዎች ጋር ጦርነት ወይም ጥላቻን ሳይፈልግ በሠላም የሚኖር ሰው ማለት ነው፡፡ ይስሐቅ ራሃብ በፀናበት ዓመት በራሱ ፈቃድ ወደ ግብፅ አገር ሲሄድ እግዚአብሔር ወደ ግብፅ መሄዱን አቋርጦ ወደ ገራራ ምድር እንዲሄድ አዘዘው፡፡ የገራራ አገር ከወንድሞቹ ቤት ሚስት ለማግባት ሄዷል ብላ የዋሸችበት ሀገር ነው፡፡

ዔሳውና ያዕቆብ ልጆቹ ሲሆኑ ይስሐቅ ዔሳውን ሲወድድ ርብቃ ደግሞ ያዕቆብን ትወደዋለች፡፡ ይስሐቅ የሚታዘዝ ሰው ነው፡፡ የአባቱን የአብርሃምን ፈቃድ ተከትሎ በሞርዮ ተራራ ላይ መስዋዕት ለመሆን የታዘዘ ሰው ነው፡፡ ይስሐቅ ሚስት እንዲያገባ የአባቱ የአብርሃም ፈቃድ ነው፡፡ ይስሐቅ የሚታዘዝና ለቤተሰቦቹም የሚጠነቀቅ ደግሞም እምነት የሚጣልበት ሰው ነው፡፡ ይስሐቅ በሄደበት ቦታ ሁሉ ለእግዚአብሔር መስዋዕት ያቀርባል፡፡ አቤሜለክ እግዚአብሔር ከይስሐቅ ጋር መኖሩን አውቆ ወደ ይስሐቅ መጥቶ ከአንተ ጋር ቃል ኪዳን እናድርግ ብሎ ጠየቀው፡፡ (ዘፍ፡ 26፥26-28)

ደግሞም ይስሐቅ የዋህ ሰው ስለሆነ የተባረኩ ሰዎች ወደ እርሱ ሲመጡ እነርሱን በክፋ ጦርነት አልገጠማቸውም፡፡ ምክንያቱም እርሱ የዋህ ሰው ነውና፡፡ (ማቴ፡ 5፥5) ላይ “የዋሆች ብፁዓን ናቸው ምድርን ይወርሳሉና” ይላልና፡፡ እንደዚህ ቃል የዋህ ለሆነው ለይስሐቅ ሰፊ ምድር አለው፡፡ ይስሐቅ ትጉ ሰው ወይም ሠራተኛ ነው፡፡ ይስሐቅ የውሃ ጉድጓዶች አምስት ጊዜ ቆፍሮ የመንጋዎችን ሕይወት እየጠበቀ በረከቶችን የሚቀበል ሰው ነው፡፡ ይስሐቅ አባቱ ያዘዘውን ትዕዛዝ ፈጽሞ ከእግዚአብሔር የዘላለም ሕይወትንና ፀጋን የተቀበለ ሰው ነው፡፡ እኛ ደግሞ እንደ ይስሐቅ የእግዚአብሔርን ቃልና ፈቃድ ታዝዘን የዘላለምን ሕይወትና የእግዚአብሔርን ፀጋ ልንቀበል ያስፈልጋል፡፡ (1ኛ ጴጥ፡ 5፥5,6)

ምዕራፍ ዘጠኝ

እስራኤል የሆነው ያዕቆብ (ዘፍ፡ 32፥21-30)

ያዕቆብ በከነአን በነበረበት ጊዜ

የያዕቆብ መወለድ፡፡ (ዘፍ፡ 25፥21-26)

የያዕቆብ አባት ይስሐቅ ያዕቆብን ባረከ፡፡ (ዘፍ፡ 27፥20-30)

ያዕቆብ በሀራን በነበረበት ጊዜ

ያዕቆብ በ77 **ዓመቱ ከወንድሙ ከዔሳው ፊት ወደ ሐራን ሸሸ፡፡** (ዘፍ፡ 28፥1-5)

ያዕቆብ በተኛበት ቦታ በቤቴል የመሰላል ሕልም አየ፡፡ (ዘፍ፡ 28፥10-22)

ያዕቆብ ወደ ሀራን ደረሰ፡፡ (ዘፍ፡ 29፥1)

ያዕቆብ ሚስት አግብቶ ወንድ ልጆችን ወለደ፡፡ (ዘፍ፡ 29፥16-30፥24)

ያዕቆብ ከሀራን ተመልሶ በከነአን ሲኖር

ያዕቆብ በ97 **ዓመቱ ወደ ከነዓን ተመለሰ፡፡** (ዘፍ፡ 31፥4-20)

ያዕቆብ በያቦቅ ወንዝ ማዶ ፀለየ፡፡ (ዘፍ፡ 32፥22-32)

ያዕቆብ በሰኬም ኖረ፡፡ (ዘፍ፡ 34፥1-4)

የያዕቆብ ልጆች ስምኦንና ሌዊ ሰዎችን ገደሉ፡፡ (ዘፍ፡ 34፥25)

ያዕቆብ ወደ ቤቴል ተጓዘ፡፡ (ዘፍ፡ 35፥1-8)

እግዚአብሔር ለያዕቆብ ቃል ኪዳን ሰጠ፡፡ (ዘፍ፡ 35፥9-15)

የያዕቆብ እድሜ በ120 **ሲሆን አባቱ ይስሀቅ ሞተ፡፡** (ዘፍ፡ 35፥28-29)

ያዕቆብ ዕድሜው 130 **ሲሆን ወደ ግብጽ ሄደ፡፡** (ዘፍ፡ 46፥1-7)

ያዕቆብ ዕድሜው 147 **ሲሆን ኤፍሬምና ምናሴን ባረካቸው፡፡** (ዘፍ፡ 48፥8-22)

ያዕቆብ (እስራኤል) **በ**147 **ዓመቱ** 12**ቱን ልጆቹን ጠርቶ ባረካቸው፡፡** (ዘፍ፡ 49፥1-28)

ያዕቆብ (እስራኤል) በ147 ዓመቱ በግብጽ ሀገር ከመሞቱ በፊት ለልጆቹ የራሱስን አስክሬን ወደ ከነአን እንዲወስዱ አዘዛቸው፡፡ (ዘፍ፡ 49÷33)

የይስሐቅ ሚስት ርብቃ ልጅ ስላልወለደች ወደ እግዚአብሔር ጸለየች፡፡ እግዚአብሔርም የርብቃን ጸሎት ሰምቶ ሜንታ ልጆችን ሰጣት፡፡ በመጀመሪያ የተወለደው ልጅ ፀጉራምና ቆዳው ቀይ ስለሆነ ዔሳው ተብሎ ተጠራ፡፡ ሁለተኛ ወንድሙ የእግሩን ተረከዝ ይዞ ስለተወለደ ያዕቆብ ተብሎ ተጠራ፡፡ ሁለቱም ካደጉ በኋላ የእነርሱ ሥራ እንዲህ ነበረ፡፡ ዔሳው አደን የሚያድን ሲሆን ወደ ጫካ በመሄድ ለአባቱ ለይስሐቅ የአጋዘን ሥጋ አዘጋጅቶ ስለሚያቀርብ አባቱ እርሱን ይወደዋል፡፡ የያዕቆብ ሥራ ደግሞ ወጥ ማዘጋጀት ስለሆነ ያዕቆብ በድንኳን ውስጥ ከርብቃ ጋር ወጥ በማዘጋጀት ስለሚረዳት እናቱ ደግሞ ያዕቆብን ትወደዋለች፡፡

አንድ ቀን ዔሳው ተርቦ ከጫካ በሚመለስበት ጊዜ ያዕቆብ ቀይ ወጥ አዘጋጅቶ ስለነበር ዔሳው ያዕቆብን "ቶሎ በል በጣም ርቦኛልና ከዚህ ቀይ ወጥ አብላኝ" ብሎ ለመነ፡፡ ያዕቆብ ዔሳውን መልሶ "በመጀመሪያ ብኩርናህን ሽጥልኝ" ብሎ ጠየቀው፡፡ በኩር ልጅ ማለት በቤት ውስጥ የሚገኘውን ዕቃዎችንና የእግዚአብሔርን በረከት የሚቀበል ሰው ማለት ነው፡፡ ዔሳው እነዚህን በረከቶች ሳይፈልግ ለጊዜያዊ ጥቅም ብኩርናውን ለያዕቆብ ሸጠ፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ (በዕብ፡ 12÷16) ላይ "ለአንድ ጊዜ መብል ሲል ብኩርናውን እንደሸጠው እንደ ኤሳው ማንም ሴሰኛ ወይም እግዚ/ር የማያከብር ሆኖ እንዳይገኝ ተጠንቀቁ ይላል"፡፡

ያዕቆብ ዔሳውን ፈርቶ የርብቃ ወንድሞች ወደሚኖሩበት በሐራን መካከል ባለው በቤቴል ድንጋዩን ተንተርሶ ተኛ፡፡ በዚህን ጊዜ ያዕቆብ ብቸኛና ተስፋ የቆርጠ ሰው ነበረ፡፡ እግዚአብሔር ግን ለያቆብ ተስፋ ሰጠ፡፡ (ዘፍ፡ 28÷13-18) ያዕቆብ በተኛበት ቦታ የእግዚ/ር መልአክ በመሰላል ላይ ሲወርዱና ሲወጡ እግዚአብሔር አብ በመሰላሉ ጫፍ ላይ የሚመለከተውን ራዕይ አየ፡፡

ያዕቆብ እግዚአብሔር ከራሱ ጋር ወደ ሁሉ ቦታ እንደሚሄድ አስተዋለ፡፡ ያዕቆብ 20 ዓመት ሙሉ በሐራን በሚኖርበት ጊዜ የርብቃ ወንድም ላባን ሲያግዝ የላባ ፀባይ ጥሩ እንዳይደለ ተማረ፡፡ ያዕቆብ በቤቴል እግዚአብሔርን በሀራን ደግሞ ሰውን አውቀዋል፡፡ ያዕቆብ የሐራን ኑሮውን ጨርሶ ወደ አገሩ ጉዞውን ቀጠለ፡፡ ነገር ግን እርሱ ያለመፍትሔ ቀረ፡፡ ይህ ማለት ስለ ወንድሙ ስለ ዔሳው ችግር ነው፡፡ ያዕቆብ በያቦቅ ወንዝ ማዶ ከመላዕክት ጋር ታግሎ አሸነፈ ይህ የሚያሳየው የእርሱ የህይወት ለውጥ ነው፡፡ (ዘፍ.32÷24)

ከዚህ በፊት የነበረው የያዕቆብ ህይወት ማታለል ነበረ:: በዚያን ጊዜ የወንድሙን የኤሳውን ብኩርና ወስዶ ነበር ነገር ግን ከመላዕክት ጋር ታግሎ ካሸነፈ በኃላ የሚታዘዝና እግዚአብሔርን የሚፈራ ሰው ሆነ፡፡ ያዕቆብ የእርሱን ወንድም ዔሳውንና አባቱን ይስሐቅን አታልሎ ስለነበር እርሱን የርብቃ ወንድም ላባ 10 ጊዜ አታለለ፡፡ (ዘፍ፡ 31፥7,41)

ስለዚህ እኛ በኑሮአችን ውስጥ ሁልጊዜ ጥሩ ነገር እየሠራን በጽድቅ ኑሮ መኖር እንዳብን ክፍሉ ያስተምራል፡፡ (ገላ፡ 6፥7-10) ያዕቆብ በራሱ ሥራ ሳይሆን በእግዚአብሔር ጥበቃ ተቀበለ፡፡ ይህ ማለት እግዚአብሔር አንድ ጊዜ የመረጠውን ሰው እስከ መጨረሻ ይወዳል ማለት ነው፡፡ እኛ ክርስቲያኖች እግዚ/ር አንድ ጊዜ ስለመረጠንና እስከ መጨረሻ ስለሚወደን ከሙሉ ልብ ልናመሰግን ይገባናል፡፡ (ሮሜ 8፥28-30፤ ኤፌ.1፥4-5)

ያዕቆብ ወንድሙን አታልሎ ስለነበር አሁን በያቦቅ ወንዝ ማዶ ኤሳውን ለመገናኘት በሚሄድበት ጊዜ ወደ እግዚአብሔር ፀለዮ ከእግዚብሔር መልስ ተቀበለ፡፡ ለእኛ ችግሮች በሚኖሩበት ጊዜ ወደ እግዚአብሔር ፀልየን እንደ ያዕቆብ ምላሽ መቀበል አለብን፡፡ (ዘፍ፡ 32፥9-12፤ 24-32)

ምዕራፍ አስር

ባለ ራዕዩ ዮሴፍ (ዘፍ፡ 39፥1-6)

በህፃንነት ጊዜ

ዮሴፍ ለያዕቆብ 11ኛ ልጅ ሆኖ የተወለደ ነው፡፡ (ዘፍ፡ 30፥22-24)

ዮሴፍ በ17 ዓመቱ ሕልም (ራዕይ) አየ፡፡ (ዘፍ፡ 37፥5-11)

ዮሴፍ በ17 ዓመቱ ወደ ግብፅ ባሪያ ሆኖ ተሸጠ፡፡ (ዘፍ፡ 37፥25-36)

ዮሴፍ በጵጥፋራ ቤት ባሪያ ሆነ፡፡ (39፥1-6)

ዮሴፍን በ27 ዓመቱ የጵጥፋራ ሚስት ፈተነች፡፡ (ዘፍ፡ 39፥7-18)

ዮሴፍ ወደ ወህኒ ቤት ተጣለ፡፡ (ዘፍ፡ 39፥19-23)

ዮሴፍ በ28 ዓመቱ በወህኒ ቤት ውስጥ የፈርኦን 2 መሪዎች ሕልም ተረጐመ፡፡ (ዘፍ፡ 40፥1-23)

በጎልማሳነት ጊዜ

ዮሴፍ በ30 ዓመቱ የንጉሥን ሕልም ተረጐመ፡፡ (ዘፍ፡ 41፥1-24)

ዮሴፍ በ30 ዓመቱ የግብፅ ጠቅላይ ሚንስተር ሆነ፡፡ (ዘፍ፡ 41፥37-40)

ዮሴፍ በ31 ዓመቱ በግብፅ አገር ላይ 7 ዓመት ጥጋብና 7 ዓመት የረሃብ ዓመት እንደሚሆን ተናገረ፡፡ (ዘፍ፡ 41፥47-42፥2)

ዮሴፍ ከወንድሞቹ ጋር እንደገና ተገናኘ፡፡ (ዘፍ፡ 42፥3-25)

ዮሴፍ ዕድሜው 39 ዓመት ሲሆን ያዕቆብን ከቤተሰቦቹ ጋር ወደ ግብፅ አስመጣ፡፡ (ዘፍ 46፥1-7፤ 29,30)

የዮሴፍ ዕድሜ 56 ሲሆን አባቱ ያዕቆብ ሞተ፡፡ (ዘፍ፡ 49፥33)

ዮሴፍ በ110 ዓመቱ ሞተ፡፡ (ዘፍ፡ 50፥26)

ለያዕቆብ አስራ ሁለት ልጆች አሉ፡፡ ከልጆቹ መካከል ዮሴፍን በጣም ይወድዳል፡፡ ምክንያቱም ያዕቆብ በስተርጅናው የወለደው ስለሆነና በጣም ከሚወድዳት ከራሔል ስለተወለደ ነው፡፡ የዮሴፍ ወንድሞች ዮሴፍን ጠሉት ምክንያቱም አባታቸው ያዕቆብ እርሱን በጣም ስለሚወድደውና ዮሴፍ ሁለት ጊዜ ሕልም አይቶ ስለተናገራቸው ነው፡፡

አንድ ጊዜ በሜዳ በእርሻ ቦታ ንዶአቸውን ሲያስሩ የእናንተ የአስራ አንዱ ንዶአችሁ ለኔ ንዶ ሰገዱ ብሎ ተናገራቸው፡፡ ሁለተኛው ሕልም ደግሞ ፀሐይና ጨረቃ አስራ አንዱ ኮከቦች ለእኔ ሰገዱ ብሎ ተናገራቸው፡፡

አንድ ቀን ወንድሞቹን እንድያይ ዮሴፍን ወደ ወንድሞቹ ጋ አባቱ ስንቅ አስይዞ ደህንነታቸውን እንዲጠይቅ ላከው፡፡ ነገር ግን ዮሴፍ ወንድሞቹ ጋ ሲደርስ ወንድሞቹ እርሱን ለመግደል ሲያስቡ የመጀመሪያው ልጅ ሮቤል ከለከላቸው፡፡ ከዚህ የተነሣ ዮሴፍን ለእስማኤላዊያን ነጋዴዎች በ20 ብር ሸጡት፡፡ የሚዳማዊያን ነጋዴዎች ዮሴፍን ለግብፅ ንጉሥ ለፈርኦን ባለሥልጣን ለዘበኞች አለቃ ለሆነው ለጴጥፋራ መልሶ ሸጡት፡፡ ዮሴፍ በጴጥፋራ ቤት በባሪነት የሚኖር ሰው ሆነ፡፡ ነገር ግን እግዚአብሔር ከዮሴፍ ጋር ስለነበር በጴጥፋራ ቤት የባሪያዎች አለቃ ሆነ፡፡ (ዘፍ፡ 39፥2-3,21-23)

ደግሞም እግዚአብሔር ዮሴፍ ታማኝ ስለሆነ በጴጥፋራ ቤት ሞገስን ሰጠ፡፡ ከዮሴፍ የተነሣ የጴጥፋሪ ቤት በውጭም በውስጥም ተባረከ፡፡ የጴጥፋራ ሚስት ዮሴፍን ከእርሷ ጋር አብሮ እንዲተኛ ፈተነችው፡፡

ዮሴፍ እግዚአብሔርን ከልቡ ስለሚያምን ይህንን ድርጊት ለማድረግ ጠላ፡፡ በዚህ ምክንያት የጴጥፋራ ሚስት ከእርሷ ጋር ዮሴፍ ለመተኛት ፍቃደኛ አለመሆኑን አውቃ የውሸት ክስ በዮሴፍ ላይ መሥርታ ዮሴፍ ወደ ወህኒ ቤት እንዲገባ አስደረገች፡፡ ነገር ግን እግዚአብሔር ለዮሴፍ ታላቅ ፀጋንና ጥበብን ስለሰጠ በወህኒ ቤት የፈርኦን ሁለት ሹማምንቶችን ህልም ተረጎመ፡፡ ከ2 ዓመት በኃላም የፈርኦንን ህልም ተረጎመ፡፡ የንጉሱ የፈርኦን ህልም ትርጉም ዮሴፍ እንዲህ ነው በማለት ተረጎመ 7 ዓመት የጥጋብና 7 ዓመት የረሀብ ዓመት ይመጣል አለ፡፡ ከጥቂት ዓመት በኃላ ዮሴፍ የግብፅ ጠቅላይ ሚኒስቴር ሆነ፡፡

ዮሴፍ በግብፅ ሀገር በጥጋብ ዓመት (በ7 ዓመት ቆይታ) እህል ሁሉ በመጋዘን እንዲከማች አደረገ፡፡

በ7 ዓመት በረሀቡ በግብፅ አገር እህል መኖሩን ያዕቆብ ሰምቶ ልጆቹን ወደ ግብፅ ልኮ እህል እንዲገዙ አደረጋቸው፡፡ ዮሴፍም ለመጡት ወንድሞቹ “እኔ የእናንተ ወንድም ነኝ” ብሎ ራሱን ገለጸላቸው፡፡ በተጨማሪ “የእግዚአብሔር ታላቅ ፈቃዱን እንድትማሩ አስቀድሞ ሕይወትን ለማዳን እኔን ላከ፡፡ ስለዚህ ምንም አትዘኑ” አለ፡፡ (ዘፍ፡ 45፥5-8) ለዮሴፍ የሥራ ሁሉ ባለቤት እግዚአብሔር ሆነ፡፡ (ዘፍ፡ 50፥19-21)

ዮሴፍ በደስታ ወይም በሐዘን ሁልጊዜ የእግዚአብሔርን ፈቃድ እየታዘዘ በእምነት የሚኖር ሰው ነው፡፡ ዮሴፍ በወጣትነት ዘመኑ እንዳየው ሕልም ኖረ፡፡ (ዘፍ፡ 37፥6,7,9) በመጨረሻም ውጤቱ የግብፅ ጠቅላይ ሚኒስቴር ሆነ፡፡ እንደዚሁም እኛ በእግዚአብሔር ቃል ሕልማችንን ይዘን የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለመፈጸም

በሕይወታችን እንድንኖር ያስፈልጋል፡፡ (ምሳሌ 29÷18) **ላይ በቅንነት የሚሄድ ይድናል፡፡ በጠማማነት የሚሄድ ግን ወዲያው ይወድቃል፡፡**

ዮሴፍ በጵጥፋራ ቤትና በወህኒ ቤት ውስጥ ለ13 **ዓመት የኖረ ሰው ነው፡፡ ነገር ግን ዮሴፍ እግዚአብሔርን ሳያሳዝን ከእግዚብሔር ጋር የሄደ ሰው ነው፡፡ በመጨረሻም ውጤቱ ዮሴፍ ነገሮችን ሁሉ ታግሶ በእምነት ስለጠበቀ የግብፅ ጠቅላይ ሚኒስተር ሆነ፡፡ እኛ ደግሞ ወደ እኛ በሚመጡ ችግሮች እግዚአብሔርን እንዳንበድል ከዮሴፍ ሕይወት ልምድ ልንማር ያስፈልጋል፡፡** (መዝ፡ 105÷17-22፤ ሮሜ፡ 8÷17)

ዮሴፍ ጠቅላይ ሚኒስቴር በሆነ ጊዜ ራሱን የሸጡትን ወንድሞቹን ሲያገኝ የእነርሱን ስህተት ይቅር አለ፡፡ እኛ ደግሞ እንደዚሁ ራሳችንን የበደሉትን ሰዎች ኃጢአት ይቅር ልንል ያስፈልጋል፡፡ (ሉቃ፡ 6÷37)

ዮሴፍ በጵጥፋራ ሚስት ተፈተነ፡፡ ነገር ግን እግዚአብሔርን በጽድቅ ልብ ስለሚያመልክ ይህን ድርጊት አልፈጽምም ብሎ እምቢ አለ፡፡ (ዘፍ፡ 39÷7-18) **እኛ ደግሞ ሕይወታችን ከሚያበላሹ ኃጢአት የሆኑብንን ነገሮች ትተን ልንለወጥ ያስፈልጋል፡፡ ዮሴፍ እግዚአብሔርን ሁልጊዜ አስቀድሞ የሚያውቅና ሌሎች ሰዎች እግዚአብሔርን እንዲያውቁ የሚያደርግ ሰው ነው፡፡ እኛ ሌሎች እግዚአብሔርን አውቀው እንዲኖሩ በማድረግ ለእግዚአብሔር ክብርን ልንሰጥ ያስፈልጋል፡፡** (ማቴ፡ 5÷16)

ምዕራፍ አስራ አንድ

የእስራኤል የመጀመሪያ መሪ ሙሴ (ዘጸ፡ 3፥1-12)

በግብፅ በሚኖርበት ጊዜ

የሙሴ መወለድ (ዘጸ፡ 2፥1-4)

ሙሴ የተወለደበት ዓመት ዕድሜያቸው ከ2 **ዓመት በታች ያሉት ወንድ ልጆች በሚሞቱበት ጊዜ ተወለደ፡፡ በዚህ ጊዜ የሙሴ እናት በወንዝ ዳር ስትጥል የፈርኦን ልጅ (ልዕልት) አገኘችው፡፡** (ዘጸ 2፥5-10)

ሙሴ የግብፅ ንጉሥ የፈርኦን የልጅ ልጅ ሆነ፡፡ (ዘጸ፡ 2፥510)

ሙሴ በ40 **ዓመቱ የግብፅን አገር ሰውን ገደለ፡፡** (ዘጸ፡ 2፥11-14)

ሙሴ በሚዲያም አገር ሲኖር

ሙሴ ወደ ምድያም አገር ሸሸ፡፡ (ዘጸ፡ 2፥15)

ሙሴ 40 **ዓመት ሙሉ በካህኑ በአማቱ ቤት ተቀመጠ፡፡** (ዘጸ፡ 2፥16-21)

ሙሴ ሲፓራን አገባ፡፡ (ዘጸ፡ 2፥21)

ሙሴ ጌርሳምንና አልዓዛርን ወለደ፡፡ (ዘጸ፡ 2፥22፤ 18፥3)

ሙሴ በ80 **ዓመቱ ወደ ኮረብ ተራራ ተጠራ፡፡** (ዘጸ፡ 3፥1-4፥17)

ሙሴ ለሁለተኛ ጊዜ በግብፅ ሀገር

ሙሴ በ80 **ዓመቱ ወደ ግብፅ ተመለሰ፡፡** (ዘጸ፡ 4፥18-26)

ሙሴ ከአሮን ጋር እንደገና ተገናኘ፡፡ (ዘጸ፡ 4፥27-31)

ሙሴ ለመጀመሪያ ጊዜ ከፈርኦን ጋር ተገናኘ፡፡ (ዘጸ፡ 5፥1-5)

ሙሴ ሁለተኛ ጊዜ ከፈርኦን ጋር ተገናኘ፡፡ (ዘጸ፡ 7፥1-7)

ሙሴ አሥር መቅሰፍቶችን በግብፅ አገር በፈርኦን ፊት አደረገ፡፡ (ዘጸ፡ 7፥8-12፥36)

ሙሴ በ81 **ዓመት ከራምሴ ጉዞ ጀመረ፡፡** (ዘጸ፡ 12፥37)

ሙሴ ቀይ ባህርን ከፍሎ እስራኤላዊያንን ካሳለፈ በኋላ የፈርኦን ሠራዊት በስተ ኋላቸው ተከትለው ሲመጡ ሰጥመው ቀሩ፡፡ (ዘጸ፡

14፥4-25)

ሙሴ መራራውን ውሃ ወደ ጣፋጭ ቀየረ፡፡ (**ዘጸ፡** 15፥22-26)

ሙሴ በምድረ በዳ መናና ድርጭትን አወረደ፡፡ (**ዘጸ፡** 16፥13-20)

ሙሴ በራፊድም አለቱን መትቶ ውሃ አፈለቀ፡፡ (**ዘጸ፡** 17፥1-7)

ሙሴ ከአማሌቅ ጋር እስራኤል በሚዋጋበት ጊዜ ድልን ከእግዚአብሔር ፀልዮ አገኘ፡፡ (**ዘጸ፡** 7፥8-16)

የምዲያም ካህን ዮቶር ሙሴን ጐበኘ፡፡ (**ዘጸ፡** 18፥1-27)

ሙሴ በሲና ተራራ

ሙሴ እድሜው 81 **ዓመት ሲሆን ወደ ሲና ምድረ በዳ ደረሰ፡፡** (**ዘጸ፡** 19፥1-2)

እግዚአብሔር ለሙሴ ቃል ኪዳን ሰጠ፡፡ (**ዘጸ፡** 19፥7-24፥8)

ሙሴ በሲና ተራራ ላይ ለ40 **ቀንና ሌሊት ከጸለየ በኋላ በደመና ውስጥ የእግዚ/ርን ፅላት (አስርቱን ትዕዛዝ) ተቀበለ፡፡** (**ዘጸ፡** 24፥15-31፥17)

ሙሴ አሥርቱን ትዕዛዛት በሁለት ድንጋዮች ላይ የተጻፈውን ተቀበለ፡፡ (**ዘጸ፡** 31፥18)

ሙሴ ከሲና ተራራ እስከሚመለስ ድረስ ሕዝቡ ወርቅ ሰብስቦ በእሳት አቃጥሎ አምላክ አድርጐ ስያመልኩ አይቶ በጣም ተቆጥቶ ጽላቱን ሰባበረ:: እነርሱ አምላክ አድርጎ የሚያመልኩትን አቃጠለ፡፡ (**ዘጸ፡** 32፥19-24)

ሙሴ ወርቅ ሠርተው አምላክ አድርገው የሚያመልኩ ሰዎችን አስገደላቸው፡፡ (**ዘጸ፡** 32፥25-35)

ሙሴ ከእግዚአብሔር ለሁለተኛ ጊዜ 40 **ቀንና** 40 **ሌሊት ተቀምጦ ጽላቱን ተቀበለ፡፡** (**ዘጸ፡** 34፥1-28)

ሙሴ በ82 **ዓመቱ ድንኳን ሠራ፡፡** (**ዘጸ፡** 36፥1-40፥33)

ሙሴ የአሮንን ልጆች የመስዋዕትን ሥርዓት እንድያደርጉ ሥልጣን ሰጠ፡፡ (**ዘለዋ፡** 8፥1-36)

የመጀመሪያ የሲና ተራራ የሕዝብ ድምር፡፡ (**ዘኁ፡** 1፥1-47)

የ38 **ዓመት የምድረበዳ ጉዞ**

ሙሴ በ82 **ዓመቱ ወደ ፉራን ተጓዘ፡፡** (**ዘኁ፡** 10፥11-12)

ሕዝቡም በእግዚ/ር ላይ ማጉረምረማቸውን እግዚአብሔር ሰምተው ከሰማይ እሳትን አወረደ፡፡ (ዘኍ፡ 11፥1-3)

ሙሴ 70 **ሽማግሌዎችን በእስራኤል ፊት መረጠ፡፡** (ዘኍ፡ 11፥16-25)

ሙሴ ኢትዮጵያዊቷን ሴት አገባ፡፡ (ዘኍ፡ 12፥1-16)

ሙሴ ወደ ከነአን 12**ቱን የእስራኤል ነገዶችን ለስለላ ላካቸው፡፡** (ዘኍ፡ 13፥1-33)

የእስራኤል ሰዎች በምድረ በዳ ለ38 **ዓመት ተዘዋወሩ፡፡** (ዘኍ፡ 14፥1-33፥38)

የሙሴ ዕድሜ 120 **ሲሆን የሌዊ ልጅ፣ የቀዓት ልጅ የይሰዓር ልጅ፣ ቆሬ፣ ከሮቤልም ልጆች፣ የኤልያብ ልጆች፣ ዳታንና አቤሮን እንዲሁም የፋሌት ልጅ አን ተቃወሙ፡፡** (ዘኍ፡ 16፥1-19)

ሙሴ ዓለቱን 2 **ጊዜ መትቶ ውሃ አፈለቀ፡፡** (ዘኍ፡ 20፥1-13)

ሙሴ ከቃደስ ተጉዞ ወደ ሖር ተራራ ሲደርስ የአሮንን ሞት አየ፡፡ (ዘኍ፡ 20፥22-29)

ሙሴ ከናስ እባብ ሠርቶ በእባብ የተነደፉትን ሰዎችን ከመቅሠፍት ፈወሳቸው፡፡ (ዘኍ፡ 21፥4-10)

ሙሴ የአሞራዊያን ንጉሥ ሴዎን አሸነፈ፡፡ (ዘኍ፡ 21፥21-32)

ሙሴ የባሣን ንጉሥ ዐግን ተዋግቶ አሸነፈ፡፡ (ዘኍ፡ 21፥33-35)

የሙሴ የመጨረሻ ስብከትና ሞት

ሙሴ በ120 **ዓመት ሞአብ ሜዳ ደረሰ፡፡** (ዘኍ፡ 22፥1)

ሙሴ ለሁለተኛ ጊዜ ሕዝቡን ቆጠረ፡፡ (ዘኍ፡ 26፥1)

ሙሴ ከእስራኤላዊያን ነገድ መካከል የሰለጵዓድ ሴቶች ልጆች ያቀረባቸውን የአባታቸውን ርስት እንዲቀበሉ ፈቀደ፡፡ (ዘኍ፡ 27፥1-5)

ሙሴ ከራሱ ቀጥሎ ሕዝቡን የሚመራ ሰው ኢያሱን በሕዝቡ ፊት አቆመ፡፡ (ዘኍ፡27፥18-23)

ሙሴ የሚዲያማውያንን ሀገር ወሰደ፡፡ (ዘኍ፡ 31፥1-12)

ሙሴ ለሮቤን፣ለጋድና ለምናሴ ነገዶች ከዮርዳኖስ ወንዝ በምሥራቅ በኩል ያለው ምድር ሰጣቸው፡፡ (ዘኍ፡ 32፥1-42)

ሙሴ ከመሞቱ በፊት 3 **ጊዜ የሰበከው ስብከት፡፡** (ዘዳ፡ 1፥1-30፥20)

ሙሴ በ120 ዓመቱ በናባው ተራራ ላይ ሞተ፡፡ (ዘዳ፡ 34÷1-8)

ሙሴ የብሉይ ኪዳን መጽሐፍት ከጻፉት ሰዎች መካከል ታላቅ ሰው ነው፡፡ ሙሴ የእስራኤል ሕዝብ መሪ፣ ነቢይና የእስራኤል የመጀመሪያ የግንባታ ሰው እንዲሁም የእግዚአብሔርንና የእስራኤልን ሰዎች የሚያገለግል አገልጋይ ነው፡፡ ሙሴ በግብፅ አገር 40 **ዓመት የተማረ ሲሆን በምዲያም አገር በእረኝነት** 40 **ዓመት ሰልጥኗል፡፡ በመጨረሻም** 40 **ዓመቱን በምድረ በዳ እግዚአብሔርንና የእስራኤልን ሰዎች አገለገለ፡፡**

ሙሴ የተወለደው የግብፅ ንጉሥ ከ2 **ዓመት በታች የሆኑ ወንድ ልጆች በሚገልበት ጊዜ ነው፡፡ የሙሴ እናት ሙሴን በናይል ወንዝ አውጥታ ጣለችው፡፡ የግብፅ ንጉሥ ሴት ልጅ ከናይል ወንዝ ሙሴን ወስዳ የሙሴ እናትን እየረዳች ሙሴን እንድታሳድግ አደረገች፡፡ ሙሴ እንደገና ወደ እናቱ ሲመለስ የእግዚአብሔርን ቃል ት/ት (የሕጉን ቃል) እንድማር ዕድል አገኘ፡፡ ደግሞም የንጉሥ የልጅ ልጅ ሆኖ በቤተመንግሥት ውስጥ ጥሩ ት/ት እንዲከታተል ተመቻችቷል፡፡**

ሙሴ የግብፅን ሰው ከገደለ በኋላ ወደ ምዲያም አገር ሸሸ፡፡ በምዲያም አገር ዮቶር አግኝቶ የዮቶርን ልጅ ሲፓራን አገባ፡፡ እግዚአብሔርም በቁጥቋጦ ውስጥ እሳት ሲነድድ ቁጥቋጦ አለመቃጠሉን አይቶ ወደ ቁጥቋጦው ሲቀርብ እዚያው ሙሴን አገኘው፡፡ እግዚአብሔር ሙሴን ወደ ግብፅ ልኮ እስራኤላዊያንን ከግብፅ ጭቆና እንዲያድን አደረገ፡፡ ሙሴ የእግዚአብሔርን በትር በእጁ ይዞ ወደ ግብፅ ሄደ፡፡

የእስራኤል ሰዎችን ለማዳን አሥር መቅሰፍቶችን በግብፅ አገር በፈርኦን ፊት አደረገ፡፡ ከዚያም ቀይ ባህርን ከፍሎ የእስራኤል ሰዎችን አሻግሮ ወደ ከነአን አስገዘ፡፡ የእስራኤል ሰዎች በምድረ በዳ እግዚአብሔርን አልታዘዙም፡፡ ነገር ግን ሙሴ የራሱን ሰዎች በመጠበቅ አገለገለ (ዘጸ፡ 32÷32) **እግዚአብሔር ሙሴን ትሑት አገልጋይ ነው ብሎ ተናገረ፡፡** (ዘኁ፡ 12÷3,7,8) **እግዚአብሔር እንደ ሙሴ ለሚጠራው ሰው ሥልጣንና ችሎታን ይሰጣል፡፡ ስለዚህ ችግሮቻችንን አይተን ሳንፈራ እግዚአብሔር በሚሰጠው ሥልጣንና ችሎታ በእምነት መታዘዝ ያስፈልጋል፡፡** (2ቆሮ፡ 9÷8፤ 1ጢሞ፡ 1÷12)

እግዚአብሔር ሙሴን ሲጠራ ሙሴ "እኔ አልችልም አፈም ኮልታፋ ነኝ" ብሎ ተናገረ፡፡ (ዘጸ፡ 5÷1-23፤ 6÷10-12) **ነገር ግን እግዚአብሔር ሙሴን እንዲረዳው አሮንን በሥልጣንና በችሎታ ሞላው፡፡ ስለዚህ እኛ ደግሞ በችግሮቻችን ጊዜ የእግዚአብሔርን ርዳታ በማመን አዲስ ሥልጣን ልንቀበል ያስፈልጋል፡፡** (መዝ፡ 36(37)÷40) **እግዚአብሔር እኔን ስለምረዳ ሌሎች ሰዎች እኔን አይጐዱም፡፡** (መዝ፡ 27÷(28)÷7፤ ዕብ፡ 13÷6) **ሙሴ እግዚአብሔር የሰጠውን የሥልጣን ቃልና ሁሉንም ሕግ ሰዎች እንዲያደርጉ አስተማራቸው፡፡** (ዘጸ፡ 24÷1-8)

ሙሴ የእግዚአብሔርን ሕግ እስራኤላዊያን እንዲጠብቁ አስተማረ፡፡ እንደዚሁም እኛ ለማያምኑ ሰዎች የእግዚአብሔርን ቃል እንድናስተምርና እንድንሰብክ ያስፈልጋል፡፡ (ሮሜ፡ 10÷14፤ ኤፌ፡ 4÷11)

የእስራኤል ሕዝብ ከግብፅ ከወጡ በኋላ በምድረ በዳ 40 ዓመት በሚኖሩበት ጊዜ “ለምን እኛን ሙሴ ከግብፅ አወጣኸን እዚህ በምድረ በዳ ለምን ታሰቃየናለህ?” ብለው ጮኹ፡፡ ሙሴ ይህን ቃል ሰምቶ “ወደ እግዚአብሔር ቅረቡ” ብሎ ለሕዝቡ ተናገራቸው፡፡ (ዘጸ፡ 16÷9) እንደዚሁም እኛ ችግሮች ሲበዙ ወደ እግዚአብሔር መቅረብ ያስፈልጋል፡፡ (መዝ፡ 41(42)÷5፤ 1ኢጥ፡ 5÷7) በጣም አስፈላጊና ወሳኝ ሰው ሙሴ የሚነጫነጩትን እስራኤላዊያን እግዚአብሔር እንዳይቆጣ የእስራኤል ሕዝብ ኃጢአት ይቅር እንዲላቸው ወደ እግዚብሔር ፀለየ፡፡

የሙሴ ፀሎት ሰለ እኛ ወደ እግዚአብሔር የሚማልደውን ኢየሱስ ክርስቶስን እንድናይ ያሳስበናል፡፡ (ሮሜ 8÷23) ስለዚህ እኛ ሌሎች ሰዎች እንዲድኑ ልንፀልይ ያስፈልጋል፡፡ ሙሴ በቃዴስ ላይ ያደረገው ድርጊት ማለትም ድንጋዩን 2 ጊዜ የመታው ወደ ተስፋይቱ አገር እንዳይገባ አደረገው፡፡ (ዘኁ፡ 20÷1-13) ይህ ማለት በብሉይ ኪዳን ሕግ ወደ እግዚአብሔር መንግሥት አይገባም ማለት ነው፡፡ ብቻ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ወደ እግዚአብሔር መንግሥት መግባት ይቻላል፡፡

(ሮሜ 8÷3፤ ገላ፡ 2÷19፤ ዕብ፡ 7÷19) እኛ በኢየሱስ ደም በኩል ድነናል፡፡ (ሐዋ፡ ሥራ 4÷12፤ 1ቆሮ፡ 1÷18) እስራኤላዊያን በሙሴ በኩል ከግብፅ ባርነት ነፃ ወጡ፡፡ እኛ ደግሞ በክርስቶስ ኢየሱስ በኩል ከኃጢአታችን ነፃ ወጣን፡፡ እስራኤላዊያን በምድረ በዳ 40 ዓመት ተለማመዱ፡፡ እኛ ደግሞ መንፈስ ቅዱስ በእኛ ውስጥ ስለሚኖር የእምነት ስራ ያሰፈልጋል፡፡ (ኤፌ፡ 5÷5)

ምዕራፍ አስራ ሁለት

አረመኔ ጠንቋዩ በለዓም (ዘኍ፡ 22፥21-35)

በለዓም የጥንቆላ ሥራ የሚሠራ ሰው ነው፡፡ (ዘኍ፡ 22፥7)

በለዓምን የሞአብ ንጉሥ ባላቅ አስጠርቶ ተቀበለ፡፡ (ዘኍ፡ 22፥3-6)

በለዓም የባላቅን የመጀመሪያውን ጥሪ እምቢ አለ፡፡ (ዘኍ፡ 22፥13)

በለዓም በባላቅ በሁለተኛ ጥሪ ተስማማ፡፡ (ዘኍ፡ 22፥15-21)

እግዚአብሔር ለበለዓም ማስጠንቀቂያ ሰጠ፡፡ (ዘኍ፡ 22፥34)

ንጉሥ ባላቅ በለአምን በጥሩ አቀባበል አስተናገደ፡፡ (22፥36

በለአም እስራኤላዊያን ባረከ፡፡ (ዘኍ፡ 23፥1-24፥25)

እስራኤላዊያንን ለማሰናከል ባላቅ ያመጣው የበለአም ት/ት (ራዕ፡ 2፥14)

እስራኤላውያን በለዓምን በሰይፍ ገደሉት፡፡ (ዘኍ፡ 31፥8)

በለአም ነቢይ ሲሆን ባላቅ ደግሞ የሞአብ ንጉሥ ነው፡፡ ንጉሡ እስራኤልን አለማሸነፉን አውቆ እስራኤላዊያንን እንዲረግም መልዕክተኞችን ወደ በለአም ላከ፡፡ ነገር ግን በለአም የእግዚአብሔርን ፈቃድ አውቆ እስራኤልን ሊረግም አልሄደም፡፡ (ዘኍ፡ 22፥15-18) በለአም በንጉሥ ባላቅ ፊት በሚሄድበት ጊዜ እግዚብሔር የሚሰጠውን ቃል ይናገር ነበር፡፡ (ዘኍ.22፥38)

በለአም በ2ኛ ጊዜ ንጉሥ ባላቅ ሲጠራው እስራኤልን ሊረግም ሲሄድ በመንገድ ላይ የእግዚብሔር መላእክ ሰይፍ ይዞ እንዳይሄድ ከለከለው፡፡ አህያይቱ የእግዚአብሔርን መላአክ ሲይታይ ነገር ግን በለአም የመንፈሳዊ ዓይን ዕውርነት ስለነበረው መላአኩን አላየም፡፡ የሰው መንፈሳዊ ዓይን ሲታወር ሰው ከእንስሳት በታች ይሆናል፡፡ (ኢሳ፡ 1፥3) ላይ "በሬ የገዥውን አህያም የጌታውን ጋጣ አወቀ፡፡ እስራኤል ግን አላወቀም ሕዝቤም አላስተዋለም" ይላል፡፡

እግዚአብሔር አህያዋ በለአምን እንድትገስፅ አደረገ፡፡ (ዘኍ. 22፥28) "እግዚአብሔር የአህያይቱን አፍ ከፈተ፡፡ በለዓምንም ሦስት ጊዜ የመታኸኝ ምን አድርጌብህ ነው? አለችው" እግዚአብሔር የበለአምን ዐይን ከፍቶ መላአኩ በመንገድ ላይ ሰይፍ ይዞ የቆመውን እንዲያይ አደረገ፡፡ በለአምም ዐይኑ ከበራለት በኋላ (ዘኍ፡ 22፥34) ላይ "እኔ የእግዚአብሔር መላአክ በድያለው አንተ በመንገድ ላይ በፊቴ

እንደቆምህብኝ አላውቅሁም፡፡ እንግዲህ አሁን አትውድድ እንደሆነ እመለሳለሁ” አለው፡፡

እኛ በመንፈሳዊ ዕውርነት እየቀጠልን የኃጢአትን መንገድ የሚንሄድ ከሆነ ሊንጠነቀቅ ያስፈልጋል፡፡ በለአም የእግዚአብሔርን ድምፅ ሰምቶ ወደ ባላቅ ሄደ፡፡ (ዘኍ.22፥35) የእግዚብሔር መላአክ በላአምን “ከሰዎች ጋር ሂድ ነገር ግን የምናገርህን ቃል ብቻ ትናገራለህ” አለው፡፡ በለአምም ከባላቅ አለቆች ጋር ሄደ፡፡

በለአም ሦስት ጊዜ ቦታ ቀይሮ እስራኤላዊያንን እንዲረግም ባላቅ ፈለገ፡፡ ነገር ግን በለአም እስራኤላዊያንን ባረካቸው፡፡ በለአም የእስራኤል ልጆች እንዲሰናከሉ ጥሩ ያልሆነው ሥጋ ይበሉ ዘንድና እስራኤላውያን ከሞአባውያን ሴቶች ጋር እንዲያመነዝሩ ለባላቅ ምክር ሰጠ፡፡ (ዘኍ.25፥1-2፤ ራዕ.2፥14) እኛ ከውጭ ለሚመጡ ችግሮች ብዙ ልንፀልይ እንችላለን፡፡ ነገር ግን ከውስጥ የሚነሳው ጦርነት መንፈሳዊ ህይወታችንን ለማበላሸት በጣም አደገኛ ስለሆነ ልንጠነቀቅ ያስፈልጋል፡፡

በለአም የእግዚአብሔርን ፈቃድ የመታዘዝ ልብ አለው፡፡ ነገር ግን ገንዘብን የሚወድድ ልብ ስላለው ገንዘብን ወሰዶ የእስራኤል ልጆች እንዲወድቁ አደረገ፡፡ በዚህ ሁኔታ ከእስራኤል ልጆች መካከል በግምት 10,000 የሚያህሉ ሰዎች ከበለአም ጋር በሰይፍ መቱ፡፡ (ኢያሱ፡ 2፥4-9፤ ሚክ፡ 6፥5፤ ራዕ 2፥14) ስለዚህ እኛ ገንዘብንና ክብር እየፈለግን የእግዚአብሔርን ፈቃድ እንዳንስት ልንጠነቀቅ ያስፈልጋል፡፡ (ሮሜ፡ 13፥14)

በለአም እስራኤልን ከባረከ በኋላ መሲሑ እንደሚመጣ ተነበየ፡፡ (ዘኍ፡ 22፥21-24፥25) እግዚአብሔር እኛን እንደ ዓይኑ ብሌን ይጠብቃል፡፡ (ዘዳ፡ 32፥10፤ 1ጴጥ፡ 1፥5) በለአም ወደ እስራኤል ልጆች አመንዝራ ሴቶችን በማምጣት የእስራኤል ልጆች ኃጢአት እንዲያደርጉ አደረገ፡፡ (ራዕ፡ 2፥14) ስለዚህ እኛ የሰይጣንን ዕቅድ ሳንስት በንጽህ ሕሊና መኖር ያስፈልጋል፡፡ (ቲቶ.1፥15፤ 1ጴጥ፡ 1፥15)

ምዕራፍ አስራ ሶስት

ጠንካራ ሰው ኢያሱ (ኢያ፡ 1፥1-11)

የኢያሱ ልደት (ዘጉ፡ 13፥8)

ኢያሱ በ54 **ዓመት ከግብፅ ወጣ** (ዘጸ፡ 12፥37,41)

ኢያሱ ከእስራኤል ሰዎች መካከል ለጦርነት የተወሰኑትን መርጦ ከአማሌቂዊያን ጋር እንዲዋጉ አዘዘ፡፡ (ዘጸ፡ 17፥8-16)

ኢያሱ የሙሴ ተከታይ ሆነ፡፡ (ዘጸ፡ 33፥11)

ኢያሱ በ55 **ዓመቱ ወደ ከነዓን ሄዶ እንዲሰልሉ** 12 **የእስራኤል ነገዶችን መረጠ፡፡** (ዘጉ፡ 13፥1-8)

ከሰለሉ በኋላ ለኢያሱ መልካም መልስ ያመጡ 2 **ሰዎች፡፡** (ዘጉ፡ 14፥30-38)

ኢያሱ ከሕዝቡ ጋር ለ38 **ዓመት በምድረ በዳ ኖረ፡፡** (ዘጉ፡ 32፥12,13)

ኢያሱ ዕድሜው 94 **ዓመት ሲሆን ከሙሴ በኋላ መሪ ሆነ፡፡** (ዘጉ፡ 27፥15-23)

እግዚአብሔር ከኢያሱ ጋር እንደሚሆን በ95 **ዓመቱ ቃል ኪዳን ገባ፡፡** (ኢያ፡ 1፥5-9)

ኢያሱ ወደ ኢያርኮ የሚሰልሉ ሰዎችን ላካ፡፡ (ኢያ፡ 2፥1-24)

ኢያሱ ሕዝቡን ከዮርዳኖስ ወንዝ አሻገራቸው፡፡ (ኢያ፡ 3፥1-17)

ኢያሱ በጌልገላ 12 **ድንጋዮችን አቆመ፡፡** (ኢያ፡ 4፥5-20)

ኢያሱ በጌልገላ የግርዘትን ሥርዓት ለእስራኤላዊያን አደረገ፡፡ (ኢያ፡ 5፥2-8)

ኢያሱ ከእግዚብሔር ሠራዊት አለቃ ጋር ተገናኘ፡፡ (ኢያ፡ 5፥13-15)

ኢያሱ የኢያሪኮን ግንብ ደምስሶ ከተማውን ወሰደ፡፡ (ኢያ፡ 6፥1-27)

የጋይን ሰዎች በእስራኤል ላይ አደጋ ጣሉ፡፡ (ኢያ፡ 7፥2-7)

ኢያሱ የጋይን ከተማ ወሰደ፡፡ (ኢያ፡ 8፥10-28)

ኢያሱ በጌባል ተራራ ላይ ለእግዚአብሔር መሠዊያ ሠራ፡፡ (**ኢያ፡** 8፥30)

በደቡብ በኩል 6 **ነገሥታት ከኢያሱ ጋር ተዋጉ፡፡** (**ኢያ፡** 9፥1-2)

የገባኦን ሰዎች ከኢያሱ ጋር ተንኰል ቃል ኪዳን ያደረጉትን አገኘ፡፡ (**ኢያ፡** 9፥3-15)

ኢያሱ እነዚያን 6 **ነገሥታትን ስላሸነፈ የኢየሩሳሌም ንጉሥ አዶኒጼዴቅ ከእርሱ ጋር አንድነትን ሊያደርግ ፈለገ፡፡** (**ኢያ፡** 10፥1-27)

ኢያሱ በጸሎት ፀሐይን አቆመ፡፡ (**ኢያ፡** 10፥12-14)

ኢያሱ ደቡባዊ ከነዓንን ያዛት፡፡ (**ኢያ፡** 10፥28-43)

ኢያሱ ሰሜናዊ መንግሥትን ማለትም የአሦርን ንጉሥ ኢያቢስን አሸነፈ፡፡ (**ኢያ፡** 11፥1-15)

ኢያሱ የከነአንን ጠቅላላ ምድር ወሰደ፡፡ (**ኢያ.** 11፥23)

ኢያሱ ለ12**ቱ ነገዶች ርስታቸውን ሰጠ፡፡** (**ኢያ.** 13 **እስከ ምዕ.**21)

ኢያሱ በሴሎ የምሥክር ድንጋይ አቆመ፡፡ (**ኢያ.** 18፥1)

ኢያሱ 6 ***መማጸኛ ከተማዎችን መረጠ፡፡*** (**ኢያ.**20፥1-9)

ኢያሱ የመጨረሻ ስብከትን ሰበከ፡፡ (**ኢያ፡** 23፥1-16)

ኢያሱ በሴኬም ከእስራኤል ሰዎች ጋር ቃል ኪዳን አደረገ፡፡ (**ኢያ፡** 24፥25)

ኢያሱ በ110 **ዓመቱ ተራራማ በሆነው በኤፍሬም ሀገር በገአስ ተራራ በሰሜን ባሉት በተምናሴራ ሞተ፡፡** (**ኢያ፡** 24፥29-31)

አብርሃም ከነዓንን ለመውረስ በእምነት ተቀበለ፡፡ ሙሴ በእምነት ወደ ከነዓን ጉዞውን ጀመረ፡፡ ኢያሱ በእምነት ከነዓንን ወረሰ፡፡ ኢያሱ ከሙሴ ለ40 **ዓመት የመሪነትን ሥራ ስልጠና አገኘ፡፡**

<u>ኢያሱ ከሙሴ የመሪነትን ሥልጠና የወሰዳቸው</u>

ከአማሌቅ ጋር ተዋግቶ በማሸነፍ (**ዘጸ፡** 17፥8)

በሲና ተራራ ሙሴ አሥርቱን ትዕዛዛትን በሚቀበልበት ጊዜ ኢያሱ አብሮ ወደ ተራራው በመሄድ ከእግዚብሔር ጋር ግንኙነትን ማድረግን ሠለጠነ፡፡ (**ዘጸ፡** 24፥13)

ከሲና ተራራ ሲወርዱ የእስራኤል ሕዝብ ወርቅ ሰብስቦ በማቅለጫ እሳት አቅልጦ በሬን ሰርቶ ሲያመልኩ የሚጮኹትን ድምፅ ኢያሱ ሰምቶ የውጊያ ወይም የዝማሬ ድምፅ እንደሆነና እዳልሆነ ለይቶ እንዲያውቅ ከሙሴ ተማረ፡፡ (ዘጸ፡ 32፥17-18)

ኤልዳድና ምዳድ በሰፈር ትንቢት ሲተነብዩ ኢያሱ ሙሴን "ጌታዬ ሆይ ከልክላቸው" ሲለው ሙሴ ግን አልተቃወማቸውም ኢያሱ ከዚህ ሰዎችን እንዴት ይቅር ማለት እንደሚችል የይቅርታን ልብ ተማረ፡፡ (ዘኁ፡ 11፥27-29)

ከእነዚህ ትምህርቶችንና ሥልጠና በኋላ ኢያሱ የሙሴ ተከታይ የመሆኑን ፈቃድ ተቀበለ፡፡ (ዘኁ፡ 27፥15-23) እግዚአብሔር ከሙሴ ጋር እንደሆነ እንዲሁ ከኢያሱ ጋር እንደሚሆን ተናገረ፡፡ (ኢያ፡ 1፥5-8)

<u>ኢያሱ ጠንካራና ጐበዝ ሰው እንዲሆን የፈለገበት</u>

እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር እንዲኖር፣ (ኢያ፡1፥5)

እግዚአብሔር ለእርሱ ተስፋ እንዲሆን፣ (ኢያ፡1፥6)

የእግዚአብሔርን ሕግ ሁሉ ቀንና ሌሊት በመጠበቅ ወደ ቀኝና ወደ ግራ እንዳይል ትክክለኛውን መንገድ ይዞ እንድሄድ፣ (ኢያ፡1፥7,8)

የእግዚአብሔር ትዕዛዝና በሚሄድበት ሁሉ ከእርሱ ጋር መሆኑን በማረጋገጥ "አትፍራ" እያለ እንዲያበረታታ፡፡ (ኢያ፡1፥9)

<u>ኢያሱ ጠንካራና ጐበዝ ሰው የመሆኑ ውጤት</u>

ከእግሩ በታች ዮርዳኖስ ወንዝ ተከፍሎ የእስራኤል ሕዝብ ማሳለፉ፣

የእስራኤል ሕዝብ መለከት ሲነፋ የኢያሪኮ ከተማ ግንብ መውደቅ፣

የኢያሱ ሠራዊት ከነዓንን መውረሱ፣

<u>ኢያሱ ከመሞቱ በፊት የተናገራቸው የኑዛዜ ቃል</u>

የእግዚብሔርን መኖርና እርሱ የሠራቸውን ሥራዎችን ከልባችሁ አትርሱ ብሎ ተናገራቸው፡፡ (ኢያ፡ 23፥15)

ኢያሱ ለሕዝቡ እግዚአብሔር አምላካችሁን ትወድዱ ዘንድ ለራሳችሁ እጅግ ተጠንቀቁ ብሎ ተናገረ፡፡ (ኢያሱ 23፥11) ይህ ማለት ሥራዎችን ሁሉ የሚሠራ እግዚብሔር በፍቅር እንጂ እናንተ አይደላችሁም እያለ መናገሩ ነው፡፡

የእስራኤል ሰዎች ባዕድን የሚያመልኩ ሕዝብ ሳይሆኑ እግዚአብሔርን ብቻ የሚያመልኩ ሕዝብ እንደሆኑ ገለጸላቸው፡፡ (ኢያ፡ 24፥14)

ታላቅ አገሮችና የንብረት ብዛት ሳይመለከቱ እግዚአብሔር ብቻ እንዲያዩ ተናገረ፡፡

ኢያሱ በፍጹም መታዘዝና በታማኝነት እግዚአብሔርን አገለገለ፡፡ እኛ ደግሞ እንደ ኢያሱ በፍጹም መታዘዝና በታማኝነት እግዚአብሔርን ልናገለግል ያስፈልጋል፡፡ (ያዕ፡ 1፥25) **የከንአንን ምድር ሊሰልሉ ከሄዱት አሥሩ ሰዎች ለሙሴ መረጃ ሲያቀርቡ "በዚያን የሚኖሩት ሰዎች ግን ሀያላን ሲሆኑ ከተሞቹም የተመሸጉና ትላልቅ ናቸው፤ ልናሸንፋቸውም አንችልም" በማለት መጥፎ ወሬ ተናገሩ፡፡ ነገር ግን ኢያሱና ካሌብ ያዩትን መረጃ ለሙሴ ሲያቀርቡ እንውጣ ምድራቸውን እንውረስ፤ ማሸነፍም እንችላለን ብለው ተናገሩ፡፡**

<u>ምሳሌ፡</u>- የኢያሪኮን ግንብ ለማፍረስ ጦርና ጋሻ ሳይዙ እግዚአብሔርን በመተማመን የኢያሪኮን ከተማ በእምነት 7ጊዜ በመዞር በታላቅ ዝማሬና ጩኸት የኢያሪኮን ከተማ ግንብ አፈረሱ፡፡ (ኢያ፡ 6፥15-20)

እንደዚህም ሁልጊዜ እግዚአብሔር ከእኛ ጋር እንደሚያደርግ በማወቅ የእግዚአብሔር ተስፋን ልንቀበል ያስፈልጋል፡፡ (ኢያ፡ 1፥5-9) **ኢያሱ ወደ እግዚአብሔር ሲጸልይ ፀሐይ ቆመች፡፡** (ኢያ፡ 10፥12-14) **እኛ ደግሞ እንደ ኢያሱ እግዚአብሔርን አምነን ልንታዘዝና ልንፀልይ ያስፈልጋል፡፡ ኢያሱ ለእስራኤል ህዝብ የከነዓንን ምድር ወርሶ ለየነገዱ አከፋፈለ፡፡** (ኢያ፡ 1፥2፤ ምዕ፡ 11፥23)

ይህ ማለት እኛ በዓለም የሚንሠራቸውን ሥራዎችን ወደ ሰማይ ሄደን የምንቀበለውን ርስት የሚያመለክት ማለት ነው፡፡ ስለዚህ እኛ የዘላለም ሕይወትና ስጦታ እስከ ምንቀበል ሁልጊዜ የእግዚአብሔርን ቃል በእምነት በመታዘዝ የእምነት ወታደሮች ልንሆን ያስፈልጋል፡፡ (ያዕ፡ 2፥5)

ምዕራፍ አስራ አራት

የኢየሱስ የቀድሞ አያት የሆነችው ጋለሞታ ረዓብ (ኢያ፡ 2፥1-21)

ረዓብ በሴተኛ አዳሪነት ሥራ ትኖራለች፡፡ (ኢያ፡ 2፥3-7)

ረዓብ የእስራኤል ሁለት ሰላዮችን ወደ ራሷ ቤት አስገባች፡፡ (ኢያ፡ 2፥3-7)

ረዓብ ሁለት ሰላዮችን ስለሸሸገች ከጥፋት የምትተርፍበትንና ዘመዶችዋን የምታተርፍበትን ቃል ኪዳን ተቀበለች፡፡ (ኢያ፡ 2፥15)

ረዓብ የኢያሪኮ ግንብ ሲወድቅ በቃል ኪዳኑ መሰረት እርሱዋና ቤተሰቦቹዋ ዳኑ፡፡ (ኢያ፡ 6፥25-25)

ረዓብ ከሁለት ሰዎች መካከል አንዱ የሆነውን ሰልሞንን አገባች፣ ከዚያ በኋላ ቦኤዝን ወለደች፡፡ (ማቴ፡ 1፥5)

ሙሴ ከሞተ በኃላ ኢያሱ ኢያሪኮ ከተማ እንዲሰልሉ ሁለት ሰላዮችን ላከ፡፡ (ኢያ፡ 2፥1) **ኢነዚያን የተላኩት ሁለት ሰላዮችን ረዓብ በራሷ ቤት ሸሽጋ ከኢያሪኮ ሰዎች ካተረፈች በኋላ ወደ ተራራው ለ**3 **ቀን እንዲሸሹ ተናገረች፡፡** (ኢያ፡ 2)

ረዓብ የእስራኤልን ሁለት ሰላዮችን አምና ንሰሐ ቃል ተናገረች

እግዚአብሔር ለእስራኤል ሕዝብ ይህን ከተማ እንደሰጠ የዚህ ከተማ ሕዝብ ልብ ሁሉ አውቀዋል አለች፡፡ (ኢያ፡ 2፥9)

ረዓብ እግዚአብሔር ከእስራኤል ሕዝብ ጋር እንደሚሠራ የከተማው ሕዝበ ያውቃሉ አለች፡፡ (ኢያ፡ 2፥10)

የኢያሪኮ ሰዎች የእግዚአብሔርን ታላቅ ሥራ ሰምተው ፈሩ አለች፡፡ (ኢያ፡ 2፥11)

ረዓብ ይህን ሰምተናል ብላ አምላካችሁም እግዚአብሔር በላይ በሰማይ በታችም በምድር እርሱ አምላክ ነውና ከእናንተ የተነሣ ከዚያ ወዲያ ለማንም ነፍስ አልቀረለትም አለች፡፡ (ኢያ፡ 2፥11)

በምድረ በዳ 40 **ዓመት ታአምራትን በሚያዩበት ጊዜ ከእስራኤላዊያን መካከል የማያምኑ ሰዎች ሁሉ ሲሞቱ ነገር ግን ረዓብ ስለ እግዚብሔር ሰምታ በልቧ እምነትን ይዛ**

ራሷንና ቤተሰብቹዋን ከሞት አዳነች፡፡ ደግሞ የኢየሱስ የቀድሞ አያት በመሆን በመዝገብ ላይ ስሙዋን አጻፈች፡፡ (ማቴ.1፥5)

እንደ ረዓብ መዳንን ለኛ የሚሰጥ ትምህርት የሚያስተምረውን የእርሱዋ አያት የሆነውን ኢየሱስ ክርስቶስን የማያምን መዳንን አይቀበልም፡፡ (ዮሐ.1፥12-13) በእግዚአብሔር በመኖር ሥራችንን እንደ እስራኤል ሰዎች ወዲያውኑ በመስራትና እንደ ረአብ ሰምተን የምናውቅበት እምነት በመያዝ አሸናፊዎች ልንሆን ያስፈልጋል፡፡ በፍጥነት ነገሮች በሚመጡበት ጊዜ ረዓብ ጥበብ አግኝታ ሁለት ሰላዮችን ሸሸገቻቸው፡፡ (ኢያ፡ 2፥4-6) ይህን በማድረግ በእግዚአብሔር ፊት ታማኝ ሆነች፡፡ (ኢያ፡ 2፥8-11)

ዛሬ እኛ በልባችን እግዚአብሔርን አምነን በተግባራችን ግን ስለ እግዚአብሔር የማንገልጽ ከሆነ የእኛ እምነት የማይሠራና የሞተ እምነት ነው፡፡ (ያዕ፡ 2፥14-26) ረዓብ የምትኖርበት የኢያሪኮ ከተማ ኃጢአት የበዛባት ከተማ ነበረ፡፡ ነገር ግን ረዓብ እግዚአብሔርን በማመን ያደረገችው ድርጊት እምነቷን ይገልጻል፡፡ (ኢያ፡ 2፥9-11)

ስለዚህ እኛ በእምነታችን በምንተገብረው ነገሮች ላይ ሰነፎች ልንሆን አያስፈልግም፡፡ ረዓብ ለሁለት ሰላዮች ቤተቦቹን እንድታድኑ ብላ ጠየቀች፡፡ (ኢያ፡ 2፥13) ይህ ማለት እኔ ብቻዬ ልዳን ማለት ሳይሆን፡፡ ቤተሰቦቿንና ጐረቤቶቿን የሚያጠቃልል ነው፡፡ እኛ ቤተሰቦቻችንና ጐረቤቶቻችንን ለማዳን እንዴት ሞከርን? እኛ በእምነት በመኖር የእግዚአብሔርን ቃል ለሌሎች ሰዎች ልንሰብክ ያስፈልጋል፡፡ (1ጴጥ፡ 2፥9)

ምዕራፍ አስራ አምስት

የእግዚአብሔርን ተስፋ ያመነው ካሌብ (ኢያ፡ 14፥6-15)

ካሌብ ወደ ከነዓን ሊሰልሉ ከሄዱት ከ12ቱ አንዱ ነው፡፡ ከ12ቱ ሰዎች 10ሩ የተናገሩት "የከነዓን ምድር ጥሩ ምድር ለመኖርም የምትመች ናት ነገር ግን የከነዓን ሰዎች በጣም ትላልቅ ስለሆኑ ደግሞም የኒፎሌም ዘሮች ስለሆኑ መውረስ አንችልም" ብለው ተናገሩ፡፡ (ዘኁ፡ 13፥31-33) ነገር ግን ኢያሱና ካሌብ እግዚአብሔርስ ከወደደን ወተትና ማር ወደምታፈሰው ወደዚያች ምድር ያገባናል እርሱዋንም ይሰጠናል ብለው ተናገሩአቸው፡፡ (ኢያ፡ 14፥8)

እስራኤላዊያን 10ሩ ሰላዮች የተናገሩትን ቃል አምነው 2ቱ ሰላዮች የተናገሩትን የእግዚአብሔርን ተስፋ አላመኑም፡፡ በመጨረሻ የእግዚብሔር የኪዳኑን ቃል ባለማመናቸው ምክንያት 40 ዓመት በምድረ በዳ ተንከራትተው ሁለቱ ሰዎች ማለትም ኢያሱና ካሌብ ሲቀሩ ሞቱ፡፡ ካሌብ የእግዚአብሔርን ቃል በማመን በድፍረት ለእስራኤላዊያን የሰለለውን እውነቱን ተናገረ፡፡ (ኢያ፡ 14፥6-9) እኛ ደግሞ እንደ ካሌብ ደፋሮች በመሆን የጌታን ቃል (ወንጌል) ለሌሎች ሰዎች ልንሰብክ ያስፈልጋል፡፡ (ሐዋ፡ 9፥27,29፤ ኤፌ፡ 3፥12)

ካሌብ ከእግዚአብሔር ታላቅ በረከትን ተቀበለ፡፡ (ኢያ.14፥6-15) ይህ ማለት ሁለቱ የእምነት ሰዎች ኢያሱና ካሌብ ከእስራኤል ልጆች በዕድሜ ታላቅ የሆኑት ብቻቸው የከነዓንን ምድር ወረሱ፡፡ (ኢያ፡ 14፥6-15፣ ምዕ.19፥49 ዘኁ.14፥24)

ስለዚህ እግዚአብሔር ለእኛ የሰጠው ተስፋ ቃል ምንድን ነው? አሁን እኛ የተሰጠን ተስፋ ቃል አምነን መሄድ ያስፈልጋል፡፡ (2ቆሮ፡ 5፥7) ካሌብ በ85 ዓመቱ የኮብሮን ከተማ ወሰደ:: ካሌብ እግዚአብሔርን እስከ መጨረሻ ድረስ እግዚአብሔርን በፍፁም ልብ ተከትሎ አምላኩን አለወጠም፡፡ (ኢያ.14፥6-15) ስለዚህ እኛ እግዚአብሔርን በማመን እስከ መጨረሻ ድረስ የጌታን ሥራ ልናደርግ ያስፈልጋል፡፡ (ኢሳ፡ 40፥20-31፤ ገላ፡ 6፥9) ኢያሱም ለካሌብ የከብሮንን ምድር ሰጠ፡፡ (ኢያ፡ 14፥13)

ምዕራፍ አስራ ስድስት

የእስራኤል እናት ዲቦራ (መሳ፡ 4፥1-10)

የዲቦራ ልደት

ዲቦራ ለፈደትን አገባች፡፡ (መሳ፡ 4፥4)

ዲቦራ መስፍን ከሆነች በኃላ

እስራኤላዊያን ዲቦራ መስፍን እንድትሆን ጠሩ፡፡ (መሳ፡ 4፥4)

ዲቦራ በኤፍሬም አገር እስራኤላዊያንን መራች፡፡ (መሳ፡ 4፥5)

ዲቦራ ለባርቅ ስለ እስራኤል ሕዝብ ሄደህ እንድትዋጋ ብላ ጠራች፡፡ (መሳ፡ 4፥6-7)

ዲቦራና ባራቅ የኢያቢስ ሠራዊት አለቃ የሆነውን ሲሣርን አሸነፉ፡፡ (መሳ፡ 14፥14-24)

ዲቦራ የድል ዝመሬን ዘመረች፡፡ (መሳ፡ 5፥1-31)

ዲቦራ እስራኤላዊያንን ለ40 ዓመት መራች፡፡ (መሳ፡ 5፥31)

ዲቦራ መስፍን ናት መሳፍንት የእስራኤላዊያን ወኪሎች ናቸው፡፡

መሳፍንት በውጊያ ጊዜ የሠራዊቱ መሪ ናቸው፡፡ የእስራኤል መሳፍንት 14 ናቸው፡፡ ነገር ግን ከመሳፍንቱ ውስጥ ሴት የሆነችው አንዲ ዲቦራ ናት፡፡ ኢያሱ ከሞተ በኋላ ሳሙኤል ሳኦልን ንጉሥ አድርጐ እስከ ሚያቆም ድረስ 450 ዓመታትን ፈጀ፡፡ በዚህ ቆይታ እስራኤላውያን እግዚአብሔርን ሰባት ጊዜ ካዱ፡፡ ነገር ግን እግዚአብሔር ሁሉንም ይቅር አላቸው፡፡

እስራኤላዊያን እግዚአብሔርን ከካዱት ከሰባቱ ክህደቶች መካከል አንዱ ዲቦራ የኖረችበት ጊዜ ነው፡፡ እስራኤላውያን እግዚአብሔርን ትተው ባኦልን (ጣኦት) አምላኪዎች ሆኑ፡፡ ከዚህ የተነሣ የመጨረሻ ውጤቱ ከከነዓን ንጉሥ ከኢያቢስ ጋር ጦርነት ተፈጥሮ ብዙዎች በአደጋ ላይ ወደቁ፡፡ በዚህ ጊዜ ዲቦራ በእምነት ከእግዚአብሔር እውቀትና ጥበብ ስለተቀበለች የከነአን ንጉሥ ኢያብስ አሸንፉ ደግሞም የእስራኤል ሰዎች አስተማሪና ለችግሮቻቸው መፍትሄ የምትሰጥ ሴት ሆና የእናትነትን ክብር አገኘች፡፡ (መሳ፡ 5፥7)

እግዚአብሔር ለዲቦራ የከነዓን ንጉሥ የኢያቢስን ሠራዊት አሳልፎ ሰጠ፡፡ ዲቦራ ይህንን ለባራቅ ነገረች፡፡ በዚህን ጊዜ የኢያቢስ አለቃ ሠራዊት በጣም ኃይለኛ ሰረገላዎች በቁጥር 900 የሚሆኑ አሉ፡፡ ነገር ግን የእስራኤል ሠራዊት ጠራቸው በጣም ትንሽ ነበር፡፡ (መሳ፡ 5፥7,8) ነገር ግን እግዚአብሔር ከዲቦራና ከባራቅ ጋር ስለሆነ የኢያቢስን ሠራዊት ድል አደረጉ፡፡ ዲቦራ ሴት በተፈጥሮዋም ደካማ ናት፡፡ ነገር ግን እግዚአብሔር ከዲቦራ ጋር ስለሆነ እውቀትንና፣ ጥበብን እንዲሁም ድፍረትን ሰጥቶ እንድታሸንፍ አደረገ፡፡ (1ቆሮ፡ 1፥27) ዛሬ እግዚአብሔር ከዲቦራ ጋር እንደሆነ በእምነት የሚታዘዝና የሚያደረግ ሰውን ይፈልጋል፡፡ እኛም እንደ ዲቦራ የእግዚአብሔር ቃል ስንታዘዝ እግዚአብሔርን ልንጠቅም እንችላለን፡፡

ዲቦራ የእስራኤል ሰዎች ኃጢያትና ያለማመናቸውን ብዙ ጊዜ ለማዳን መስፍን ሆና ተመረጠች (መሳ.4፥1-4) በመስፍንነት ለ40 ዓመት እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ እስራኤልን መራች፡፡ (መሳ፡ 5፥31) ዲቦራ ሴትነቷን ሳትፈራ በመስፍንነት ቆመች፡፡ እኛ ቤተክርስቲያን እንዲመሩት ለወንዶች ብቻ ስፍራ ስንተው ዛሬም እንደ ዲቦራ ለእግዚአብሔር የሚቀኑ ሴቶች ስላሉ ለሴቶችም የመሪነትን ቦታ መስጠት ያስፈልጋል፡፡ ዲቦራ የከነዓን ንጉሥ ኢያቢስን ካሸነፈች በኋላ የዝማሬ ቅኔ ለእግዚአብሔር ዘመረች፡፡ (መሳ፡ 5፥1-31)

እኛ ደግሞ ኃጢአታችን ለእግዚአብሔር ተናዘን ለእግዚአብሔር የዝማሬ ቅኔ ልንዘምር ያስፈልጋል፡፡ ዲቦራ ራሱዋን መስዋዕት አድርጋ ለስራኤል ሰዎች ችግር መፍትሄ አምጥታ አለማመናቸውን ለመቀየር መድሀኒት ለመሆን ሞከረች (መሳ.4፥5-14 ምዕ.5፥7) እኛ ደግሞ እንደ ዲቦራ ደካሞችን ለመርዳትና በእምነት እንዲሰሩ ለማድረግ ራሳችንን ለእነርሱ አሳልፈን ልንሰጥ ያስፈልጋል፡፡

ምዕራፍ አስራ ስምንት

ናዝራዊ የሆነ ሳምሶን (መሳ፡ 13፥1-7)

የሳምሶን መወለድ አስቀድሞ መልአክ ተነበየ፡፡ (**መሳ፡** 13፥3)

የሳምሶን ልደት፡፡ (**መሳ፡** 13፥24)

ሳምሶን ናዝራዊ ሆኖ አደገ፡፡ (**መሳ፡** 13፥12-14)

ሳምሶንን መንፈስ ቅዱስ በጾርዓና በኤሽታኦል መካከል ባለው በዳን ሰፈር ውስጥ አነቃቃ፡፡ (**መሳ፡** 13፥25)

ሳምሶን የቴምናን ሴት አገባ (**መሳ**.14፥1-4,10)

ሳምሶን የአንበሳ ደቦልን በእጁ ገነጣጠለ፡፡ (**መሳ፡** 14፥5-9)

ሳምሶን ከፍልጥኤም 30 **ሰዎችን ገደለ፡፡** (**መሳ፡** 14፥11-19)

ሳምሶን የፍልጥኤምን የስንዴ መከር በእሳት አቃጠለ፡፡ (**መሳ**.15፥1-5)

የፍልጥኤም ሰዎች የሳምሶን ሚስትና የሚስቱን አባት ስለገደሉ ሳምሶን ወደ እነርሱ ሄዶ እነርሱን ገደላቸው፡፡ (**መሳ፡** 15፥6-8)

ሳምሶን ይሁዳን ወሰደ፡፡ (15፥9-13)

ሳምሶን በአህያ መንጋጋ ከፍልስጥኤማዊያን አንድ ሺህ ሰዎችን ገደለ፡፡ (**መሳ፡** 15፥14-16)

ሳምሶን በምድረ በዳ እጅግ ስለተጠማ እግዚአብሔር ተአምራት እንድያደርግ ጸለየ፡፡ እግዚ/ርም ፀሎቱን ሰምቶ ከአለት ውሃ አፈለቀ ሳምሶንም ጠጣ፡፡ (**መሳ**.15፥18,19)

ሳምሶን ወደ ጋዛ ሄዶ ጋለሞታ ሴት ወደምትኖርበት ቤት ገባ፡፡ (**መሳ፡** 16፥1,2)

ሳምሶን የጋዛ ከተማ በር ተሸክሞ ወደ ከብሮ ተራራ ወሰደ፡፡ (**መሳ፡** 16፥3)

ሳምሶን ደልላን ወደደ፡፡ (**መሳ፡** 16፥4)

ሳምሶን በደልላ ተታለለ፡፡ (**መሳ፡** 16፥5-19)

ሳምሶምንን የፍልሰጥኤም ሰዎች ወሰደው ወደ ወህኒ ጣሉት ከዚህም ሁለቱን ዓይኖችን አውጥተው በወፍጮ ድንጋይ ላይ እህል እንዲፈጭ አደረጉ፡፡ (**መሳ፡**

16፥20,21)

ሳምሶን ሥልጣኑን እንደገና ተቀበለ፡፡ (**መሳ፡** 16፥22-30)

ሳምሶን የፍልስጤም ሰዎች ለአምላካቸው ለዳጎን መስዋዕት ለማቅረብ ከመጡትን ከብዙ ሰዎች ጋር አንድ ላይ ሞተ፡፡ (**መሳ**.16፥28-30)

ሳምሶን በማኑሄ መቃብር ውስጥ ተቀበረ፡፡ (**መሳ፡** 16፥31)

የማኑሔ ሚስት ልጅ የማትወልድ መካን ነበረች፡፡ ነገር ግን የጌታ መላእክ ተገላጦ ልጅ እንደምትወልድ ተነበየ፡፡ ይህ የሚወለደው ልጅ ሳምሶን ነው፡፡ ሳምሶን ለእግዚአብሔር የተለየ ወይም ናዝራዊ ነው፡፡ (**መሳ፡** 13፥5)

<u>ናዝራዊ ማለት ምን ማለት ነው</u>?

በፀጉሩ ላይ ምላጭ የማይገባ (ፀጉሩን የማያስቆርጥ)

የማያሰክር የወይን ጠጅ የማይጠጣ

ርኩሰ ነገርም የማይነካ ለእግዚአብሔር የተለየ ሰው ማለት ነው፡፡

በፀጉሩ ላይ ምላጭ ያለመግባቱ የፀጉሩ ርዝማኔው የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑን የሚያሳውቅ ሲሆን የማይሰክር ወይም የወይን ጠጅ ያለመጠጣቱ ደግሞ ራሱን መቆጣጠር ሲሆን ርኩስ ነገርን ያለመንካቱ ለእግዚአብሔር ራሱን ንጹሕ አድርጎ መቀደስን ይገልፃል፡፡ (**መሳ**. 13፥5-7፤ **ዘኁ፡** 6፥1-21)

ሳምሶን ከመወለዱ በፊት እግዚአብሔር የተናገረውን ተስፋ የናዝራዊነትን ጥሪ ተቀበለ፡፡ ደግሞ መንፈስ ቅዱስ ወደ ሕይወቱ ከገባ በኋላ ታላቅ ሥልጣንና ኃይል የተቀበለ ልዩ ሰው ነው፡፡ ነገር ግን ሳምሶን የናዝራዊነትን ሕግ ሲተው እግዚአብሔር የሰጠው ሥልጣን ከርሱ ተለየ፡፡ (**መሳ**.14፥1-10) **እንደዚሁም የተመረጠ ሰው ፈጽሞ እግዚአብሔርን የማይከተል ከሆነ መጨረሻው ውድቀት ነው፡፡ ስለዚህ እኛ እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝና ቅዱስ መስዋዕት አድርገን ሕይወታችንን ልናቀርብ ያስፈልጋል፡፡** (**ሮሜ፡** 12፥2)

ሳምሶን ታላቅ ጀግና ነው፡፡ ነገር ግን እርሱ የግብረ ሥጋ ግንኙነት በመመኘት ተልዕኮውን ረሳ፡፡ (14፥1-3፤ 16፥1-20) **ዛሬ እኛ የግብረ ሥጋ ግንኙነት ምኞት እንቢ በማለትና እግዚአብሔር ለእኛ የሰጠውን ተልዕኮ ሳንረሳ መፈጸም ያስፈልጋል፡፡** (**ቆላ፡** 3፥1-5፤ 2ጢሞ፡ 2፥22) **ሳምሶንን የፍልስጥኤም ሰዎች ወስደው 2ቱን ዐይኖቹን**

አውጥተው በወፍጮ ድንጋይ ላይ እህል አንዲፈጭ አደረጉት፡፡ በመጨረሻም ሳምሶን ራሱ የሠራባቸውን ኃጢአት ንሰሐ ገብቶ የእግዚአብሔርን ኃይል ተቀበለ፡፡ ከዚያ በኋላ በአንድ ቤት ተሰብስቦ የነበሩት የፍልስጥኤም ሠራዊት አዛዦች በሞሉበት እርሱም የቤቱን መሰሶ በመሸከም ቤቱን በመጣል ብዙ ሰዎችን ገደለ እርሱም በዚያን ጊዜ ሞተ፡፡ (መሳ፡ 16÷28-30)

እግዚአብሔር እምነት የጣለው ሰው ምህረትን ሲለምን ኃጢአትን ሁሉን ይቅር ብሎ ምህረትና ድልን ይሰጣል፡፡ (ኢሳ፡ 55÷7) እኛም ደግሞ ኃጢያታችንን ስንናዘዝ እግዚአብሔር ኃጢያቶቻችንን ይቅር ብሎ ምህረትን ይሰጣል:: ምክንያቱም የእግዚአብሔር ፍቅር ከእኛ ኃጢያት ብዙ ነውና፡፡

ምዕራፍ አስራ ዘጠኝ

ኑኃሚንን የታዘዘችው ሩት (ሩት፡ 1፥6-18)

በሞአብ ምድር ስትኖር

ሩት የመሐሎን ሚስት ናት፡፡ (ሩት፡ 1፥2)

ሩት መሐሎን ከሞተ በኋላ መበልት ሆነች፡፡ (ሩት፡ 1፥5)

ሩት ከባለቤቷ እናት ከኑኃሚን ጋር ለመሄድ ወሰነች፡፡ (ሩት፡ 1፥16-18)

በቤተልሄም አገር ስትኖር

ሩት ወደ ቤተልሔም ተመለሰች፡፡ (ሩት፡ 1፥22)

ሩት ስንዴን ትቃርማለች፡፡ (ሩት፡ 2፥2-23)

ሩትን ቦኤዝ እንደሚያገባ ጠየቀ፡፡ (ሩት፡ 3፥1-18)

ሩት ቦኤዝን አገባች፡፡ (ሩት፡ 4፥13)

ሩት ኢዮቤድን ወለደች፡፡ (ሩት፡ 4፥17)

በይሁዳ ምድር በቤተልሔም ረሀብ ስለነበር አቤሜሌክና ኑኃሚን ከሁለት ልጆች ጋር ወደ ሞአብ ምድር ሄዱ፡፡ በሞአብ ምድር ሲኖሩ አቤሜሌክ ሞተ፡፡ በኋላም ሁለቱ ወንድ ልጆች ከሞአብ አገር ሴቶችን አገቡ እነርሱም ልጅ ሳይወልዱ ሞቱ፡፡ (ሩት፡ 1፥4-5) **እኛ የእግዚአብሔር ልጆች ችግር ወደ እኛ በሚመጣበት ጊዜ ብዙ ኃጢአት ወዳለበት ወደ ዓለም መሄድ ጥቅሙ ውድቀት ነው፡፡ ኑኃሚን እግዚአብሔር የቤተለሔምን ይሁዳን እንዳሰበ ብዙ ምርት እንደሰጠ ሰምታ ወደ አገሯ ተመለሰች፡፡ ኑኃሚን ለኦርፋና ለሩት "ወደ አገሬ እኔ መመለሴ ነውና እናንተ ወደ ቤተሰቦቻችሁ ተመለሱ" ብላ ተናገረች፡፡** (ሩት፡ 1፥8)

ኦርፋ ወደ አገሯ ወደ ሞአብ ስትመለስ ሩት ግን ከኑኃሚን ጋር ወደ ቤተልሔም ለመሄድ ቆራጥ መሆኑዋን ስትገልጽ "ወደምትሄጅበት እሄዳለሁና በምታድሪበትም አድራለሁና እንድተውሽ ከአንቺ ዘንድ እንድመለስ አታስቸግሪኝ ሕዝብሽ ሕዝቤ አምላክሽ አምላኬ ይሆናል፡፡ በምትሞችበት ሥፍራ እሞታለሁ በዚያም እቀበራለሁ፡፡ ከሞት በቀር አንቺንና እኔን አንዳች ቢለየን እግዚአብሔር ይህን ያድርግብኝ እንዲሁም ይጨምርብኝ" አለች፡፡ (ሩት፡ 1፥16-17) **ኑኃሚንና ሩት አብሮ ወደ ቤተልሔም ይሁዳ ተመለሱ፡፡ ነገር ግን በሚመለሱበት ጊዜ ለእነርሱ የሚበላ ምግብ ባለመኖሩ**

ተጨንቀው ነበር፡፡ ሩት እህል በሚሰበሰብበት ጊዜ ወደ ሰው እርሻ ውስጥ በመሄድ ስንዴን እየቃረመች ኑኃሚንን ትረዳ ነበር፡፡

ሩት በምትቃርምበት አካባቢ ባለሥልጣን የሆነ ሰው አንድ ሀብታም ሰው ቦኤዝን አገኘች፡፡ በኋላም እርሱን አገባች፡፡ ሩት ኢዮቤድን ወለደች፡፡ ኢዮቤድ የንጉሥ ዳዊት አያት ነው፡፡ (ሩት፡ 4፥17) ሩት የዓለም ደስታ ሳትከተል እግዚአብሔርን ብቻ ተስፋ በማድረግ ለቤተክርስቲያን ሞዴል ወይም ጥሩ ምሳሌ ሆነች፡፡ (ሮሜ፡ 7፥4፤ ኤፌ፡ 4፥15) ስለዚህ እኛ ክብርን እስከምንቀበል ድረስ ችግሮችንና መከራዎችን በትዕግሥት ማለፍ ያስፈልጋል፡፡ (ሩት፡ 4፥5፤ ኤፌ 6፥1-3)

ሩት ኑኃሚን በጭንቅ እያለች እንዲህ ብላ አፅናናች፡፡ “- - - ህዝብሽ ህዝቤ አምላክሽ አምላኬ ይሆናል“ አለች፡፡ (ሩት፡ 1፥16) እኛ ደግሞ በችግሮቻችን ጊዜ እንደ ሩት በመታገስ እግዚአብሔርን አምነን በእምነት ልናሸንፍ ያስፈልጋል፡፡ (ኤፌ፡ 3፥16፤ ዕብ፡ 5፥12) እግዚአብሔር ሩትን ቦኤዝ እንዲያገባ አደረገ፡፡ ደግሞም ለእኛ ፍቅሩን ሰጥቶናል፡፡ (መዝ፡ (90)ቁ፡ 15፤ ሮሜ፡ 8፥37)

ምዕራፍ ሃያ

ልጆቹን ሳያስተምር የወደቀ ዔሊ (1ኛ ሳሙ፡ 2፥12-17፤ ቁ፡ 22-25)

ከፍርድ በፊት

ዔሊ የመጀመሪያ ካህን ነው፡፡ (1ኛ ሳሙ፡ 1፥9)

ዔሊ በ58 **ዓመቱ መስፍን ሆነ፡፡** (1ኛ ሳሙ፡ 4፥18)

ዔሊ ሳሙኤልን ከራሱ ቀጥሎ ሕዝቡን የሚመራ ካህን አድርጎ አሳደገው፡፡ (1ኛ ሳሙ፡ 3፥1-9)

ዔሊ ከእግዚአብሔር ይልቅ ልጆቹን ወደደ፡፡ (1ኛ ሳሙ፡ 2፥29)

የዔሊ ሁለት ልጆች ክፉ ነገር ስላደረጉ እግዚአብሔር ፈረዳቸው፡፡ (1ኛ ሳሙ፡ 2፥27-36)

ከፍርድ በኃላ

ዔሊ በ98 **ዓመቱ የልጆቹን መሞት ወሬ ሰማ፡፡** (1ኛ ሳሙ፡ 4፥5-11)

ዔሊ ከልጆቹ መሞት የተነሣ ተደናግጦ ከወንበሩ ወድቆ አንገቱ ተሰብሮ ሞተ፡፡ (1ኛ ሳሙ፡ 4፥18)

ዔሊ የመሳፍንት የመጨረሻ በመስፍን ሆኖ ለ40 **አመት ሰርቷል፡፡ ነገር ግን የእርሱ ሥራ ክፉ ነበር፡፡ ዔሊ ካህን ሲሆን ልጆቹ እግዚአብሔርን የማይፈሩና የማያውቁ ናቸው፡፡** (1ኛ.ሳሙ.2፥12) **የዔሊ ልጆች ለእግዚአብሔር የሚሰጠውን መሥዋዕት ከእግዚአብሔር በፊት አስቀድሞ ለራሳቸው የሚወስዱና ከመሰውያው በፊት ጥሬውን ሥጋ ማለትም የሰባውን ለራሳቸው የሚወስዱ ናቸው፡፡** (1ኛ.ሳሙ.2፥17)

ከዚህ የተነሣ እግዚአብሔር በነብያት በኩል የፍርድን ቃል ሰጠ፡፡ እኛ ኃጢአትን ባደረግን ጊዜ የእግዚአብሔርን ምህረት በንሰሐ ልንጠይቅ ያስፈልጋል፡፡

ዔሊ ለልጆቹ ሰለ እግዚአብሔር ትምህርት ባለማስተማሩ ምክንያት ልጆቹ እግዚአብሔርን የሚበድሉ ሆኑ:: ከዚህ የተነሳ የእስራኤል ሰዎች ከእግዚአብሔር ጋር ያላቸው ግንኙነት አቋረጡ፡፡ የሃይማኖትም ሚስጢር ተበላሸ፡፡ (1ኛ ሳሙ፡ 2፥29፤ ምዕ፡ 3፥13፤ ምዕ፡ 4፥12-22) **እኛ ስለሃይማኖታችን ሌሎች ሰዎች ጥሩ ሥራ**

እንዲያደርጉና ከመጥፎ ድርጊታቸው እንዲመለሱ የሚንገልጽ ሰዎች ሊንሆን ያስፈልጋል፡፡

እናንተ ከእግዚአብሔር ይልቅ ልጆቻችሁን ትወዳላችሁ?

እኛ ልጆቻችንን ጥሩ ትምህርት እያስተማርንና ክፉ ነገር ሲያደርጉ አይተን እየተቆጣን የእግዚአብሔርን መፍራት በውስጣቸው እንዲገባ አቅጣጫ የምናሳይ ሰዎች ልንሆን ያስፈልጋል፡፡ ዔሊ ሁለት ልጆቹን ባለማስተማሩ ምክንያት መላው እስራኤል ከፍልስጥኤም ጋር ተዋግቶ እንዲሸነፍ እና የእግዚአብሔር የቃል ኪዳን ታቦት እንዲማረክ ምክንያት ሆኖአል፡፡ (1ኛ.ሳሙ.4፥12-22)

ስለዚህ እኛ በአካባቢያችን ለልጆቻችን ትክክለኛውን ትምህርት እንድናስተምርና የእግዚአብሔርም ነገር ሌሎች ያላመኑ ሰዎች እንዲያምኑ (በሰይጣን ቁጥጥር ላይ ያሉትን ሰዎችን ከሰይጣን መማረክ ያስፈልጋል)፡፡ የዔሊ ዕድሜ በጨመረ ቁጥረ አይኖቹና መንፈሳዊው እይታ ጨልሞ ነበር፡፡ (1ኛ ሳሙ፡ 3፥1-2)

እኛ ደግሞ እርጅና እየመጣ ባለ ጊዜ በመንፈሳዊ ነገር ሰነፎችና ደካሞች ነን? እንደ ንስር ክንፍ በማውጣት ኃይላችንን ልናድስ ያስፈልጋል፡፡ (ኢሳ፡ 40፥31) ይህ ማለት በየቀኑ ከእግዚአብሔር ጋር እየተገናኘን አዲስ የመንፈስ ኃይል በመቀበል እምነታችንን ልናሳድግ ያስፈልጋል ማለት ነው፡፡

ምዕራፍ ሃያ አንድ

አዲስ መንገድ የከፈተው ሳሙኤል (1ኛ ሳሙ፡ 3፥19-21)

ሳሙኤል በሐና ጸሎት የተወለደ ልጅ ነው፡፡ (1ኛ ሳሙ፡ 1፥5-19,20)

ሳሙኤል ጡት መጥባቱን ሲተው ሐና ወደ እግዚአብሔር ቤት አምጥታ ለእግዚአብሔር ሰጠች ከዚያም በኋላ ሳሙኤል በቤተ መቅደሱ አደገ፡፡ (1ኛ ሳሙ፡ 1፥21-28)

ሳሙኤል ዕድሜው 12 **ዓመት ሲሆን የእግዚአብሔር ጥሪ ተቀበለ፡፡** (1ኛ.ሳሙ.3፥1-11)

ሳሙኤል ስለዔሊ ቤተሰብ መበላሸት እግዚአብሔር በራዕይ የተናገረውን መልዕክት ተቀበለ፡፡ (1ኛ ሳሙ፡ 3፥12-18)

ሳሙኤል የእግዚአብሔር ነቢይ ሆነ፡፡ (1ኛ ሳሙ፡ 3፥19-21)

ሳሙኤል የፍልስጥኤም ጣኦትን አጠፋ፡፡ (1ኛ ሳሙ፡ 7፥3-4)

ሳሙኤል በምጽጳ ሁሉንም የእስራኤልን ሰዎች ሰብስቦ ስለ እግዚአብሔር አስተማረ፡፡ (1ኛ ሳሙ፡ 7፥5-11)

ሳሙኤል "አቤንዘር" ብሎ ድንጋይን ተከለ፡፡ (1ኛ ሳሙ፡ 7፥12-14)

ሳሙኤል ከቦታ ወደቦታ እየተዘዋወረ የሚመራ ነቢይ ነው፡፡ (1ኛ ሳሙ፡ 7፥15-17)

ሳሙኤል ሳኦልን ንጉሥ እንዲሆን በዘይት ቀባ፡፡ (1ኛ ሳሙ፡ 10፥1-8)

ሳሙኤል ዳዊት ንጉሥ እንዲሆን በዘይት ቀባ፡፡ (1ኛ ሳሙ፡ 16፥4-13)

ሳሙኤል በአርማቴ ሞተ፡፡ (1ኛ ሳሙ፡ 25፥1)

ሳሙኤል የእምነት እናት ከሆነችው በሐና ጸሎት የተወለደ ልጅ ነው፡፡ ሳሙኤል ጡት እስከሚተው ድረስ ከእናቱ ከሐና እምነትንና ጸሎትን ተማረ፡፡ በኋላም ወደ ቤተመቅደስ ሄዶ በዚያው እምነት አደገ፡፡ ካህኑ ኤሊና ልጆች በእግዚአብሔር ፊት ታላቅ ኃጢያት ሲሰሩ ነገር ግን ሳሙኤል በእግዚአብሔርና በሰዎች ዘንድ ሞገስና ፀጋን ተቀብሎ ያደገ ሰው ነው፡፡ (1ኛ ሳሙ፡ 2፥26) **እግዚአብሔር ወደ ሳሙኤል መጥቶ የነቢይነትን ሥራ ሰጠ፡፡ እስራኤልና የዔሊ ልጆች ከፍልስጥኤም ጋር በሚዋጉበት ጊዜ**

ተስፋ ያደረጉት ታቦት ተማርኮ የዔሊ ሁለት ልጆች ሞቱ፡፡ከዚያም አባታቸው የእስራኤል ታቦት መማረኩንና ልጆቹ መሞታቸውን ሰምቶ በድንጋጤ ከወንበሩ ወድቆ አንገቱ ተሰብሮ ሞተ፡፡

ከዚህም በኋላ የእስራኤል አዲስ መሪ የሆነው ሳሙኤል ተነሣ፡፡ ሳሙኤል በመጀመሪያ ለእስራኤል ሰዎች እምነትን አስተማረ፡፡ ሳሙኤልም የእስራኤልን ቤት ሁሉ “በሙሉ ልባቸው ወደ እግዚአብሔር ተመለሱ እንግዶችን አማልክትንና አስታሮትን ከመካከላችሁ አርቁ ልባችሁንም ወደ እግዚአብሔር አቅኑ እርሱንም ብቻ አምልኩ” ብሎ (በ1ኛ.ሳሙ.7÷3) ላይ ያለውን ቃል አስተማራቸው፡፡

ቀጥሎም ሳሙኤል በምጽጳ የእስራኤል ቤት ሁሉ ሰብስቦ የንሰሐ ጾም ፀሎት አደረገ፡፡ (1ኛ ሳሙ፡ 7÷6) እግዚአብሔር ከእስራኤል ሰዎች ጋር ስለሆነ እስራኤላዊያን ፍልስጥኤማዊያንን አሸነፉ፡፡ (1ኛ ሳሙ፡ 7÷10) የሳሙኤል ዕድሜ በጨመረ ጊዜ 2 ልጆች የእስራኤል መስፍን ሆኖ እንድመሩ አደረገ፡፡ ነገር ግን የሳሙኤል ልጆች የአባታቸውን መንገድ ስላልተከተሉ ሕጉ እንደሚለው አልመሩትም፡፡ (1ኛ ሳሙ፡ 8÷3)

ከዚህ የተነሳ የእስራኤል ሕዝብ ለሳሙኤል ንጉሥ እንደሚያስፈልጋቸው ጮኹ፡፡ ሳሙኤል ለእስራኤል ሕዝብ የንጉሥ ወግ ሁሉንም ሳያስቀር ንጉሥ ሲኖራቸው ችግሮች እንደሚበዛባቸው አስረግጦ አስጠነቀቃቸው፡፡ (1ኛ ሳሙ፡ 8÷7,18) ነገር ግን የእስራኤል ሕዝብ የንጉሥ ወግ ፈልገው ሳሙኤል የሚለውን ቃል እምቢ አሉ፡፡ (1ኛ ሳሙ፡ 8÷20) የእስራኤል ሕዝብ ከእምነት ተሳስተው የእግዚአብሔርን ርዳታ ሳይፈልጉ የእስራኤል ሕዝብ የሚመራ ንጉሥ ፈለጉ፡፡

በዓለም ላይ ብቻውን የሚመራ እግዚአብሔር ነው፡፡ (1ኛ ሳሙ፡ 8÷7) “እግዚአብሔርም ሳሙኤልን አለው፡- በእነርሱ ላይ እንዳልነግሥ እኔን እንጂ አንተን አልናቁምና የሚሉህ ነገርን ሁሉ የሕዝቡን ቃል ስማ፡፡” ሳሙኤል የእምነት ሥራ እንዴት እንደሚሠራ ጸሎት እንዴት እንደሚጸለይ አስተማራቸው፡፡ ነገር ግን ሃይማኖታቸው ስለተበላሸ የእነርሱ እምነታቸው አልተሻሻለም፡፡ ነገር ግን ህዝቡ ስለኃጢያታቸው ወደ እግዚአብሔር ለታዲሶ አልጮኹም፤ የመሰዎያ እቃዎችን የፍልስጥኤም ሰዎች ማርከው የወሰዱትን እንዲመለስ አላደረጉም፡፡

ሳሙኤል ሳኦል ንጉስ እንዲሆን በእስራኤል ሁሉ ፊት ቀባ፡፡ (1ኛ.ሳሙ.10÷1-18) ሳሙኤል በህፃንነት ጊዜ ለእግዚአብሔር ጥሪ ወዲያውኑ ታዘዘ፡፡ እርሱ ከእግዚአብሔር ጋር ተስማምቶ የእስራኤል ህዝብ ለመምራት የቻለ ታላቅ መሪ ነው፡፡ (1ኛ.ሳሙ.3÷1-21) እኛ ደግሞ በእግዚአብሔር ፊት ሁልጊዜ በምንኖርበት በማንኛውም ስፍራ እግዚአብሔር ልንታዘዝ ያስፈልጋል፡፡ (1ኛ.ሳሙ.15÷22)

ሳሙኤል ከፊልስጥኤማውያን ጋር ከመዋጋቱ በፊት በሰይፍና በጦር ሳይታመን በምጽጳ እስራኤላውያንን ሰብስቦ ንሰሃ እንዲገቡና በእግዚአብሔር እንዲታመኑ እንዲታዘዙም አስተማራቸው፡፡ (1ኛ.ሳሙ.7÷6) እኛ ደግሞ በችሮቻችን ጊዜ የዓለምን ሀብት ሳንመኝና ስልጣንን ሳንፈልግ ዓለምን ሁሉ የሚመራ እግዚአብሔር ብቻ መሆኑን ማመን ያስፈልጋል፡፡ (ዘፀ.17÷15) እስራኤላዊያን በእምነታቸው እንዳይወድቁ የእግዚአብሔርን ቃል እንዲታዘዙና እንዲፀልዩ ሳሙኤል ተሀድሶ አመጣ፡፡ (1ኛ.ሳሙ.7÷3-6)

እስካሁን እኛ እየሰራን ያለው ስራ ምንድን ነው? እያንዳንዳችን ከምንፀልይ ፀሎትና የእግዚአብሔርን ቃል ከምናጠና ጥናት የተነሣ ህይወታችን አካባቢያችን እንዲሁም ማህበረሰባችን ጭምር ይቀየራል፡፡

እግዚአብሔር ለሳሙኤል የሰጠው ሶስት ተልዕኮዎች

ካህን

መስፍንን

ነብይ

እነዚህን ሳሙኤል ተቀብሎ በደንብ ሰርቷል፡፡ (1ኛ.ሳሙ.3÷20-21 ምዕ.7÷15-19 ምዕ.9÷9)

ሳሙኤል እግዚአብሔርን ብቻ የሚያምን የሚታዘዝ ለህዝቡም ተከታታይ ፀሎት የሚፀልይ ሰው ነው፡፡ ደግሞም የእስራኤልን ህዝብ በሚመራበት ጊዜ በንፁሕ ልብ እየመራ የኖረ ሰው ነው፡፡

አሁን ጌታ ለኛ የሰጠው ተልዕኮ ምንድን ነው? አንተ እንደ ሳሙኤል በመታዘዝና በመፀለይ በንፁህ ልብ እየኖርክ ትሰራለህ?

ነገር ግን ንጉሥ ሳኦል በእግዚአብሔር ላይ ኃጢአት ስላደረገ የእግዚአብሔር ቃል ስላልታዘዘ ሳሙኤል የፍርድ ቃል ተናገረ፡፡ (1ኛ.ሳሙ.15÷7-23) ለዚህ መጥፎና ኃይለኛ ለሆነው ሰው በድፍረት ፍርድን ተናገረ፡፡ እኛ መጥፎ ነገሮችን ትተን ስህተቶችንና ኃጢአቶችን በሙሉ በእግዚአብሔር ፊት በመናገር ንሰሐ ልንገባ ያስፈልጋል፡፡ (1ኛ.ተሰ፡ 5÷22)

ሳሙኤል ከአንድ ሀገር ወደ ሌላ ሀገር በመሄድ የሚመራ መፍስን ሲሆን የነቢያትን ትምህርት ቤት ከፍቶ የእግዚአብሔርን ቃል ብዙ ሰዎችን ያስተማረ ሰው ነው፡፡ ነገር ግን የእርሱ ሁለት ልጆች ከትምህርቱ ወደቁ፡፡ እኛ በውጪ ስለ ጌታ የምንናገራቸውንና የምናስተምራቸው ማንኛውንም ነገሮች ለቤተሰቦታችን ማስተማርና እንዲተገብሩ ማድረግ አለብን፡፡

ምዕራፍ ሃያ ሁለት

የመጀመሪያ የእስራኤል ንጉሥ ሳኦል (1ኛ ሳሙ፡ 11፥6-15)

ሳኦል ሳሙኤልን ተገናኘ፡፡ (1ኛ ሳሙ፡ 9፥10)

ሳኦል ከሳሙኤል የዘይቱን ቅባት ተቀበለ፡፡ (1ኛ ሳሙ፡ 10፥1)

ሳኦል በምርጫ ንጉሥ ሆነ፡፡ (1ኛ ሳሙ፡ 10፥17-24)

ሳኦል አምናዊያንን በበዜቅ አደጋ ጥሎ አሸነፈ፡፡ (1ኛ.ሳሙ፡ 11፥4-11)

የሳኦልን ንጉሥነት በጌልገላ ላይ በማፅናት ግብዣ አደረገ፡፡ (1ኛ ሳሙ፡ 11፥15)

ሳኦል ለ42 **ዓመታት የእስራኤል ጠላት በሆኑት በፍልስጥኤማዊያን ላይ አደጋ ጥሎ አሸነፈ፡፡** (1ኛ ሳሙ፡ 13፥1-4)

ሳኦል ያልተፈቀደውን የመሰዋዕቱን ሥርዓት ስላደረገ ሳሙኤል ተቆጣ፡፡ (1ኛ ሳሙ፡ 13፥8-15)

ሳኦል በማክማስ ፍልስጥኤማዊያንን ድል አደረገ፡፡ (1ኛ.ሳሙ.13፥16-23)

ሳኦል ሕዝቡ እንዲጾሙ ትዕዛዝ ሰጠ፡፡ (1ኛ.ሳሙ.14፥24-46)

ሳኦል በ60 **ዓመቱ አማሌቃዊያን ድል አድርጎ ሁሉንም አጥፋ ያለውን ትዕዛዝ ሳያጠፋ ምርጥ ምርጡን ማርኮ ወደ ቤቱ አመጣ፡፡** (1ኛ.ሳሙ.15፥1-21)

ሳኦልን የእግዚአብሔር ትዕዛዝ ስላልፈፀመ እግዚአብሔር ንጉስ እንዳይሆን ስለናቀው የእግዚአብሔር መንፈስ ከእርሱ ስለተለየው ክፉ መንፈስ መጥቶ ያሰቃየው ነበር፡፡ (1ኛ.ሳሙ.15፥22-31፣1ኛ ሳሙ፡ 16፥14-23)

ሳኦል ከፍልስጥኤም ሠራዊት ከጐልያድ ጋር እንድገጥም ዳዊትን ላከ፡፡ (1ኛ ሳሙ፡ 17፥31-40)

ሳኦል ዳዊትን ለመግደል ሞከረ፡፡ (1ኛ ሳሙ፡ 18፥6-25)

ሳኦል ለዳዊት የራሱን ልጅ እንዲያገባ በመስጠት አማች ሆነ፡፡ (1ኛ.ሳሙ፡ 18፥17-29)

ሳኦል የአማሌቅ ሰዎችና መሪዎች የሕግ ሰዎችን 85 **ሰዎችን ገደለ፡፡** (1ኛ ሳሙ፡ 22፥9-19)

ሳኦል በ74 **ዓመት የፍልስጥኤማዊያን ጦርነት ስለፈራ እግዚአብሔርም ለእርሱ ስላልመለሰ የመናፍስት ጠሪ ሴት አስጠራና ተገናኘ፡፡** (1ኛ ሳሙ፡ 28፥3-25)

ሳኦል በ80 አመቱ በጊብዓ ተራራ በተካሄደው ጦርነት ሞተ፡፡ (1ኛ ሳሙ፡ 31፥1-13)

ሳኦል የቢንያም ነገድ ነው፡፡ ሳሙኤል ለሳኦል ንጉሥ እንዲሆን የተናገረው ነቢይ ነው፡፡ (1ኛ ሳሙ፡ 9፥17) ሳኦል የሚቃረኑ ሰዎች ሊገዱሉ ስለሚፈልጉ ሳኦል የንጉሥነትን ማዕረግ እምቢ አለ፡፡ (1ኛ ሳሙ፡ 11፥12-13) የእስራኤል ሕዝብ ሳኦልን ለንጉሥነት በሚፈልጉበት ጊዜ የራሱ ወገን አናሳነትን አውቆ ተሸሸገ፡፡ (1ኛ ሳሙ፡ 10፥22)

ሳኦል ንጉሥ በሆነ ጊዜ በትህትና የእግዚአብሔርን ቃል ለማድረግ የሞከረ ሰው ነው፡፡ ነገር ግን ከሁለት ዓመት በኋላ የፍልስጥኤምን ሠራዊት ለመዋጋት በተሰበሰቡ ጊዜ የፍልጥኤምን ሰራዊት ፈርተው ነቢዩ ሳሙኤል እስከሚመጣ ጊዜ ሳይጠብቅ ለራሱ ያልተፈቀደውን የመስዋዕትን ሥርዓት አደረገ፡፡ (1ኛ.ሳሙ.13፥8-10)

ሳኦል የእግዚአብሔርን ርዳታ ሳይጠብቅ በራሱ ሀሳብ የአምልኮ ሥርዓት አደረገ፡፡ እኛም ደግሞ ወደ እግዚአብሔር ከፀለይን በኃላ መልሱ ሲዘገይ በራሳችን ሀሳብ ወደ ሌላ ስፍራ መሄድና ያልተፈቀደውን ማድረግ ውድቀትን እንደሚያመጣ ማወቅ ያስፈልጋል፡፡ ስለዚህ እንደዚህ ዓይነት አስተሳሰብ እንዳናደርግ ልንጠነቀቅ ያስፈልጋል፡፡እግዚአብሔር ሳኦልን አማሌቃውያንን ሁሉ እንስሳትንም ሁሉ እንዲገድል ትዕዛዝ ሰጥቶ ነበር ነገር ግን ሳኦል የአማሌቅን ንጉሥ ዐግን ሳይገድል በሕይወቱ ይዞ በጣም የሰቡ እንስሳትን ማርኮ አመጣ፡፡

ነገር ግን እግዚአብሔር ሳሙኤልን ወደ ሳኦል ልኮ እንዲህ አለ፡፡ “በውኑ የእግዚአብሔር ቃል በመስማት ደስ እንደሚለው እግዚአብሔር በሚቃጠልና በሚታረድ መስዋዕት ደስ ይለዋልን? እነሆ መታዘዝ ከመስዋዕት ማድመጥም የአውራ በግ ስብ ከማቅረብ ይበልጣል፡፡ ዐመፀኝነት እንደ ሟርተኛ ኃጢአት እልከኝነትም ጣዖትንና ተራራንም እንደ ማምለክ ነው፡፡ የእግዚአብሔርን ቃል ንቀሃልና እግዚአብሔር ንጉሥ እንዳትሆን ናቀህ” አለ፡፡ (1ኛ ሳሙ፡ 15፥22-23)

ሳኦል እግዚአብሔርን በመናቁ በመጨረሻ ጊዜ እግዚአብሔር ሳኦልን ናቀ፡፡ ሳኦል በክፉ መንፈስ ስቃይና በተለያዩ ችግሮች ውስጥ ገብቷል፡፡ (1ኛ ሳሙ፡ 18፥10) ሳኦል ጐልያድን ለመግደል ዳዊትን ከላከ በኋላ ዳዊት ጐልያድን ገድሎ ሲመለስ ከሕዝቡ ክብርን ተቀበለ:: ሕዝቡም እንዲህ እያሉ አከበሩ፡፡ “ዳዊት እልፍ ገደለ ሳኦል ሺህ ገደለ” አሉ፡፡ ከዚህ የተነሣ ሳኦል እንቅልፍ ሳይተኛ በችግሮች ውስጥ ገባ፡፡ (1ኛ ሳሙ፡ 18፥7) ሳኦል እግዚአብሔርን ሲያምን መንፈስ ቅዱስ ከእርሱ ጋር ነበር፡፡ ነገር ግን እግዚአብሔርን በናቀ ጊዜ መንፈስ ቅዱስ ከእርሱ ራቀ አድመኝነትና ክፉ መንፈስ ወደርሱ ገባ፡፡ የመንፈስ ቅዱስ ጥበቃ ከእርሱ ተለየ፡፡ (1ኛ ሳሙ፡ 16፥18)

ስለዚህ እኛ በድካም ጊዜ፣በብርቱ ጊዜ፣በልግስና ጊዜ፣በደስታ ጊዜ፣በዝቅተኛነት ጊዜና በከፍተኛነት ጊዜ በትህትና እግዚአብሔርን መጠበቅ ያስፈልጋል፡፡ (ማቴ.10÷33) ሳሙኤል የተናገረውን ሰምቶ ለጠላቶቹ ይቅርታን የሚሰጥና እግዚአብሔርን የሚያመልክ ሰው ነበር፡፡ (1ኛ ሳሙ፡ 9÷1-11÷13) ነገር ግን ሳኦል እግዚአብሔርን ችላ በማለት የራሱን ምኞት ክብር ፈልጐ በቅናት ኃጢአትን አደረገ፡፡ አሁን እኛ የሃይማኖታችን ምስጢር ቅርፁንና ሥልጣን እናሳያለን? (2ኛ ጢሞ፡ 3÷5)

ሳኦል በፍልስጥኤም ውጊያ ጊዜ የእግዚአብሔርን ሥነ ሥርዓት ድንጋይ አቆመ፡፡ (1ኛ ሳሙ፡ 14÷33-35) እግዚአብሔር ሳኦል ያደረገው የመስዋዕት ስርአት አምልኮ አልፈለገም፡፡ እግዚአብሔር የንሰሐ ልብና የተሰበረ ልብ ይፈልጋል፡፡ (ሆሰዕ፡ 6÷6) እኛ ክርስቲያኖች በምናመልክበት ጊዜ የልምድ አምልኮ ቅርጽ ትተን በንሰሐ ልብና በተሰበረ ልብ ወደ እግዚአብሔር በመቅረብ ማምለክ ያስፈልጋል፡፡ ሳኦል እግዚአብሔርን ስለናቀው በመጨረሻ በራሱ በራሱ ሰይፍ ላይ ወድቆ ሞተ፡፡ (1ኛ.ሳሙ.31÷1-13)

ምዕራፍ ሃያ ሶስት

በእግዚአብሔር መንፈስ የተመረጠ ንጉሥ ዳዊት (1ኛ ሳሙ፡ 16፥6-13)

ዳዊት በቤተልሔም ተወለደ፡፡ (2ኛ ሳሙ፡ 5፥4)

ዳዊት የበግ እረኛ ነው፡፡ (1ኛ ሳሙ፡ 16፥11)

ዳዊት የንጉሥነትን ማዕረግ በ15 **ዓመቱ ሳሙኤል ዘይቱን ሲቀባው ተቀበለ፡፡** (1ኛ ሳሙ፡ 16፥6-13)

ዳዊት በንጉሥ ሳኦል ቤት ውስጥ በገናን የሚደረድር ነው፡፡ (1ኛ ሳሙ፡ 16፥14-23)

ዳዊት በ20 **ዓመቱ የፍልስጥኤም ግዙፍ ጐልያድን ገደለ፡፡** (1ኛ ሳሙ፡ 17፥41-54)

ዳዊት ዮናታንን ከልቡ ወዶ ጓደኛ አደረገ፡፡ (1ኛ ሳሙ፡ 18፥1-4)

ዳዊት የንጉሥ ሳኦል የጦር ሠራዊት አለቃ ሆነ፡፡ (1ኛ ሳሙ፡ 18፥13-16)

ዳዊት የሳኦልን ሴት ልጅ የሆነችው ሜልኮልን አገባ፡፡ (1ኛ ሳሙ፡ 18፥17-29)

ሳኢል ዳዊትን እንዲገድል ልጁ ዮናታንን ላከ ነገር ግን ዮናታል ዳዊትን ስለሚወደው እንዲሸሽ አደረገ፡፡ (1ኛ.ሳሙ.19፥1-7)

ዳዊት ከዮናታን 2 **ጊዜ የተስፋ ቃል አገኘ፡፡** (1ኛ ሳሙ፡ 20፥1-42፤ ምዕ፡ 23፥16-18)

ዳዊት ሳኦልን ሁለት ጊዜ አግኝቶ አልገደለም፡፡ (1ኛ ሳሙ፡ 24፥16፤23፥18)

ዳዊት በ23 **ዓመቱ መጀመሪያ የናባል ሚስት የነበረችውን አቢግያንና አክናሆምን አገባ፡፡** (1ኛ ሳሙ፡ 25፥39-42 ምዕ.30፥5)

ዳዊት ንጉሥ ሳኦል እስኪሞት ድረስ በጺቅላግ ተቀመጠ፡፡ (1ሳሙ፡ 27፥1-30፥26)

ዳዊት በከብሮ ላይ በ30 **ዓመቱ የይሁዳ ንጉሥ ሆነ፡፡** (2ኛ.ሳሙ፡ 2፥1-4)

ዳዊት በ35 **ዓመቱ ለመላው እስራኤል ንጉሥ ሆነ፡፡** (2ኛ ሳሙ፡ 5፥1-5)

ዳዊት በ37 ዓመቱ ኢያቡሳዊያንን አሸነፎ ጽዮን ያዘ፡፡ (2ኛ ሳሙ፡ 5÷6-10)

ዳዊት ወደ ኢየሩሳሌም የእግዚአብሔርን ታቦት ይዞ እንዲመጡ ከእስራኤል ሰዎች የተመረጡትን ላከ፡፡ (2ኛ ሳሙ፣ 6÷1-23)

ዳዊት የእግዚአብሔርን ቤተመቅደስ ለመሥራት በልቡ ተዘጋጅቶ በሚነሣበት ጊዜ እግዚአብሔር አልፈቀደም፡፡ (1ኛ ዜና፡ 28÷3)

ዳዊት መጀመሪያ ያሸነፈው ጦርነት፡፡ (8÷1-14)

ዳዊት ሁለተኛ ጊዜ ያሸነፈው ጦርነት፡፡ (10÷1-14)

ዳዊት በ49 ዓመቱ ከኦሪዮ ሚስት ከቤርሳቤህ ጋር ዝሙት ፈጸመ፡፡ (2ኛ ሳሙ፡ 11÷1-27)

ዳዊት እግዚአብሔር ከላከው ከነቢይ ናታን የፍርድ ማስጠንቀቂያ መልዕክት ተቀበለ፡፡ (2ኛ ሳሙ፡ 12÷1-14)

በዳዊት ቤተሰብ ውስጥ ጦርነት ተነሣ፡፡ (2ኛ ሳሙ፡ 13÷1-39)

የዳዊት ዕድሜው 61 ዓመት ሲሆን ልጁ አቤሴሎም ስላመፀ ከፊቱ ሸሸ፡፡ (2ኛ.ሳሙ. 15÷1-19÷8)

ዳዊት ወደ ቤቱ ተመለሰ፡፡ (2ኛ ሳሙ፡ 19÷9-39)

ዳዊት በ67 ዓመት የእስራኤል ሕዝብ እንድቆጠር አደረገ፡፡ (2ኛ ሳሙ፡ 24÷1-25)

ዳዊት ለሰለሞን ንጉሥነቱን ሰጠ፡፡ (1ኛ ነገ፡ 1÷5-53)

ዳዊት በ70 ዓመቱ በከብሮ ከተማ ሞተ፡፡ (1ኛ ነገ፡ 2÷1-11)

ሳሙኤል ከእሰይ ልጆች መካከል ዳዊትን በእግዚአብሔር መንፈስ ተመርቶ ወደ እሴይ ቤት ሄዶ በዘይቱ ቀባው፡፡ ዳዊት የእግዚአብሔርን ልብ ያሳረፈ (ሐዋ፡ 13÷22) ያመነ ብዙ መዘሙሮችን የጻፈና ከጐልያድ ጋር ተዋጋቶ በእግዚአብሔር ስም ያሸነፈ ሰው ነው፡፡ (1ኛ ሳሙ፡ 17÷45-47) ዳዊት እግዚአብሔርን እንደታዘዘ ልጁም ሰለሞን ለእግዚአብሔር እንድታዘዝ ይፈልጋል፡፡ ዳዊት የንስሐ ልብ ያለው ሰው ነው፡፡ ዳዊት ኃጢአትን ባደረገ ጊዜ ነቢዩ ናታን መጥቶ ስለ ኃጢአቱ ስናገር በእግዚአብሔር ፊት በእምባ ወድቆ ንሰሐ የገባ ሰው ነው፡፡ ለዳዊት ችግሮች የተጀመሩት ከኅሊያድ ጋር ውጊያ ባደረገ ቀንና ሳኦል እሱን ለመግደል በፈለገበት ጊዜ ነው፡፡ ሳኦል ለመግደል አጥብቆ ስፈልግ የሳኦል ልጅ ዮናታን የዳዊት ጓደኛ ስለሆነ ከሞት አተረፈው፡፡

ዳዊት የሳኦልን ልጅ ሚልኮልን ወደደ አቢግያ ደግሞ ዳዊትን ከነፍስ መግደል አዳነችው፡፡ እግዚአብሔርም እርሱን ከብዙ ችግሮችና ከመከራዎች ረዳው፡፡ ከዚህ የተነሣ ዳዊት ታላቅ የእምነት ሰው ሆነ፡፡ ዳዊት የመከራ 10 ዓመታትን ካሳለፈ በኋላ ችግሮችን አሸነፎ የይሁዳን ሕዝብ ለ4 ዓመት ተኩል ንጉሥ ሆኖ እየመራ በኋላ የሴሜኑና የደቡብን በአንድ ላይ ለ40 ዓመት መምራት ቻለ፡፡

ዳዊት ለእሴይ የመጨረሻና 8ኛ ልጅ ሲሆን ስራው በግ መጠበቅ ነው፡፡ ዳዊት በልብ ትሑት ስለሆነ እምነትም ስላሌለው የራሱን ሥራ በቅንነት ስለሚያደርግ ለንጉሥነት እግዚአብሔር መረጠ፡፡ እግዚአብሔር ለሰው ልብን ሲመለከት ሰው ግን ፊትን ያያል ስለዚህ እኛ እግዚአብሔር የሚፈልገውን ሥራ እየሠራን በየቀኑ ያንን እያደረግን አትራፎዎች ልንሆን ያስፈልጋል፡፡ (1ኛ ሳሙ፡ 16÷6-13፤ ማቴ፡ 6÷8)

ዳዊት ጐልያድን ለማሸነፍ ጐራዴና ጦር ሳይዝ በእግዚአብሔር ስም አሸንፋለው ብሎ አሸነፈ፡፡ ዳዊት በእግዚአብሔር ስም አሸንፋለሁ ብሎ ስላመነ አሸናፊ ሆነ፡፡ (1ኛ ሳሙ፡ 17÷45-54) ስለዚህ እኛ ችግሮች ተጠናክሮ ወደ እኛ በሚመጡበት ጊዜ አስቀድመን የእግዚአብሔርን ርዳታ ልንፀልይና ወደ እግዚአብሔር በእምነት ደፍረን ልንሄድ ያስፈልጋል፡፡ (1ኛ ሳሙ፡ 26÷24)

ዳዊት ንጉሥ ከሆነ በኋላ ሰንፍና የትዕብት ሃሳብ አድርጎ የአርዮን ሚስት ቤርሳቤህን ወደ ራሱ ቤት በማምጣት ከእርሷ ጋር አመነዘረ፡፡ በመቀጠልም የእስራኤል ሕዝብ ቁጥር ለማወቅ ያለ እግዚአብሔር ፈቃድ አስቆጠረ፡፡ በእግዚአብሔር ላይ ኃጢአት አደረገ፡፡ (2ኛ ሳሙ፡ 11÷1-27፤ 24÷1-25) ዳዊት በትህትና ልብ በሚኖርበት ጊዜ ምንም ስህተት አላደረገም፡፡ ስለዚህ እኛ ኢየሱስ ክርስቶስን የምንከተል ራሳችንን በትህትና ልብ ልንጠብቅ ያስፈልጋል፡፡ (ምሳሌ፡- 29÷23፤ ማቴ፡ 11÷29)

ዳዊት ራሱን ለመግደል የሚፈልገውን ሳኦልን ለመግደል ቢፈልግ ሁለት ጊዜ ምቹ ሁኔታዎችን አግኝቶ አልገደለውም፡፡ (1ኛ ሳሙ፡ 24ና26) ምክንያቱም በሳኦል ላይ የእግዚአብሔር ቅባት ስላለው እንዴት እገላለሁ ብሎ ነው፡፡ ዳዊት በፍጹም ልብ እግዚአብሔርን የሚያምንና፣የቃሉንም ሥልጣን አውቆ የሚከተል ሰው ነው፡፡ እኛ ክርስቲያኖች የእግዚአብሄር ቅባት በመጋቢዎች በወንጌላዊያንንና በቤተክርስቲያን መሪዎች ላይ ስላለ እነርሱ የሚናገሩትን የእግዚአብሔርን ቃል ልንታዘዝ ያስፈልጋል፡፡ (1ኛ ቆሮ፡ 16÷16,1ኛ ተሰ፡ 5÷13)

ዳዊት ብዙ ጊዜ መልካም ሥራ በሚያደርግበት ጊዜ ችግሮች ሲመጡ ስለችግሮቹ የእግዚአብሔርን ርዳታ ይቀበላል፡፡ እኛ ደግሞ እግዚአብሔርን ሳናሳዝን እስከ መጨረሻ ትግስተኛ ልንሆን ያስፈልጋል፡፡ (ዮሐ.16÷33፤ ራዕ.21÷7) ዳዊት የኦሪዮን ሚስት በመውሰድ ስህተት (ኃጢአት) አደረገ፡፡ (2ኛ ሳሙ፡ 11÷1-27) ስለዚህ እኛ በእግዚአብሔር ፊት ራሳችንን ልንመረምርና የሥጋ ሥራዎችን በመሰቀል ላይ መስቀል ያስፈልጋል፡፡ (2ኛ ቆሮ፡ 4÷16፤ ገላቲ፡ 6÷14)

ዳዊት የእስራኤልን ሕዝብ እንዲቆጠር በማድረጉ እግዚአብሔርን አልታዘዘም፡፡ ነገር ግን በኋላ በእግዚአብሔር ፊት በፍጹም ልብ ንሰሐ ገብቶ ለእግዚአብሔር መታሰቢያ በማቆም እግዚአብሔርን አመለከ፡፡ (2ኛ ሳሙ፡ 24÷1-25) እኛ ደግሞ ስህተትን ባደረግን ጊዜ ከእምነት ልብ ንሰሐ በመግባት ወደ እግዚ/ር ልንመለስ ያስፈልጋል፡፡ (ሉቃ. 19÷8)

ዳዊት ራሱ ንጉሥ ሆኖ የእስራኤልም ባለሥልጣንና ኃላፊ የከፍተኛነትን ማዕረግ ይዞ በእግዚአብሔር ፊት ራሱን ዝቅ አድርጐ ንሰሐ ገባ፡፡ (መዘ.41÷11፤ 50÷1-19) የእግዚአብሔርን ፀጋ የተቀበሉ ብዙዎች ሲሆኑ የእግዚአብሔር ፀጋ የሚያውቁ ጥቂቶች ናቸውአሁን አንተ እስካሁን ድረስ የእግዚአብሔርን ፀጋ በማወቅ እያመሰግንህ ትኖራለህ? (1ኛ ተሰ፡ 5÷18)

ምዕራፍ ሃያ አራት

ጥበበኛው ንጉሥ ሰለሞን (1ኛ ነገ፡ 3፥4-15)

የሰለሞን ልደት (2ኛ ሳሙ፡ 12፥24)

ሰለሞን የኢየሩሳሌምን ቤተመቅደስ አደሰ፡፡ (1ኛ ዜና፡ 3፥5)

ሰለሞን የነቢዩ ናታን ትምህርት በእምነት ተቀበለ፡፡ (2ኛ ሳሙ፡ 12፥25)

ሰለሞን በ20 **ዓመቱ የንጉሥነትን ማዕረግ ተቀበለ፡፡** (1ኛ ነገ፡ 1፥43-47)

ሰለሞን ያሸፈተውን አዶኒያስን ይቅር አለ፡፡ (1ኛ ነገ፡ 1፥49-53)

ሰለሞን የአባቱን የዳዊትን ሞት አየ፡፡ (1ኛ ነገ፡ 2፥10-12)

ሰለሞን የእግዚአብሔርን ቤተመቅደስ ለመሥራት ከዳዊት የመጨረሻ ቃል ተቀበለ፡፡ (1ኛ ዜና፡ 22፥6-19)

ሰለሞን የንጉሥነትን ሥልጣን አጠናከረ፡፡ (1ኛ ነገ፡ 2፥25-46)

ሰለሞን የፈርኦንን ልጅ አገባ፡፡ (1ኛ ነገ፡ 3፥1)

ሰለሞን በገባዖን ዋና ኮረብታ መስገጃ ላይ 1000 **የሚቃጠል መስዋዕት አቀረበ፡፡** (1ኛ ነገ፡ 3፥4)

ሰለሞን ከእግዚአብሔር ጥበብን ተቀበለ፡፡ (1ኛ ነገ፡ 3፥5-15)

ሰለሞን ለጋለሞቶች ሴቶች ትክክለኛውን ፍርድ ፈረደ፡፡ (1ኛ ነገ፡ 3፥16-28)

ሰለሞን የሠራዊቱን ሥልጣን አጠናከረ፡፡ (1ኛ ነገ፡ 4፥26)

ሰለሞን በ7 **ዓመት ቆይታ ቤተመንግሥቱን አሠራ፡፡** (1ኛ ነገ፡ 5ና6)

ሰለሞን ዕድሜው 31 **ዓመት ሲሆን የቃል ኪዳን ታቦት ከዳዊት ከተማ ከጽዮን ወደ ኢየሩሳሌም አስገባ፡፡** (1ኛ ነገ፡ 8፥1-66)

ሰለሞን በ13 **ዓመት ቆይታ የራሱን መንግሥት አሠራ፡፡** (1ኛ ነገ፡ 7፥1ና9፥1)

ሰለሞን የሳባ ንግሥት ነጋዴ ከሆነችው ስጦታን ተቀበለ፡፡ (1ኛ ነገ፡ 10፥11-29)

ኢትዮጵያዊቷ ሳባ ንግሥት ሰለሞንን ጐበኘች፡፡ (1ኛ ነገ፡ 10፥1-13)

ሰለሞን ብዙ የፈረንጅ አገር ሴቶችን አገባ፡፡ (1ኛ ነገ፡ 11፥4-8)

ሰለሞን ከእግዚአብሔር ፈቃድ ስለወጣ ማስጠንቀቂያውን ተቀበለ፡፡ (1ኛ ነገ፡ 11፥9-13)

ሰለሞን እግዚአብሔርን ስላልታዘዘ እግዚአብሔር በሰለሞን ላይ የኤዶምያስን ሰው ሃዳድን፣ የኤልዳድን ልጅ ሬዞንን፣ የኤፍሬማዊው የናባጥ ልጅ ኢዮርብዓምን ጠላት አድርጎ አሳመፀ፡፡ (1ኛ ነገ፡ 11፥14,23,26-40)

ሰለሞን በ60 ዓመቱ ሞተ፡፡ (1ኛ ነገ፡ 11፥43)

ሰለሞን ከአባቱ ከዳዊት ከእናቱ ደግሞ ከቤርሳቤህ ተወልዶ በነቢይ ናታንና በሕግ መሪ በሳዳቅ ረዳትነት በ21 ዓመቱ ንጉሥ ሆኖ የእስራኤልን ህዝብ ለ40 ዓመታት መራቸው፡፡ ሰለሞን በገባኦን 1000 የሚቃጠል መስዋዕት ለእግዚአብሔር አቀረበ፡፡ እርሱ ጥሩ ዝናና ገንዘብን ሳይፈልግ ከእግዚአብሔር ሕዝቡን የሚያስተዳድርበትን ጥበብና እውቀትን ፈለገ፡፡ እግዚአብሔርም ለሰለሞን የለመነውንና ከዚያም አትረፍርፎ ጥበብና እውቀት ሞገስም ሰጠ፡፡ ሰለሞን ልዩ ጥበብን በፈቃዱ አደረገ፡፡ (1ኛ ነገ፡ 3፥16-28)

ሰለሞን 3000 ምሳሌዎችንና 1005 (አንድ ሺህ አምስት) መዝሙሮችን ጻፈ፡፡፡ (1ኛ ነገ፡ 4፥32) ሰለሞን በሕይወቱ እያለ የምሳሌ፡- የመኃልልዬ መኃልይና የመክበብን መጽሐፎችን ጻፈ፡፡ (1ኛ ነገ፡ 4፥32) ሰሎሞን ባለጠጋ በመሆን ኖረዋል፡፡ (1ኛ ነገ፡ 4፥22-28) ነገር ግን ኢየሱስ በማቴ፡ 6፥29 ላይ እንደተናገረው ምንም ባለጠጋ ቢሆንም “ነገር ግን እላችኋለሁ ሰሎሞንስ እንኳ በክብሩ ሁሉ ከእነዚህ አበባዎች እንደ አንዱ አልለበሰም” ብሎ ተናገረ፡፡ ይህ ማለት በዓለም ላይ ያለው ክብሩ ጥሩ እንዳይደለ መግለጹ ነው፡፡

የሳባ ንግሥትና ብዙ ሰዎች ከሰሎሞን ጋር ለመገናኘት መጥተው እጅግ ብዙ ወርቅና ብር ሰጡ፡፡ (1ኛ፡ ነገ፡ 10፥1-29) ሰሎሞን በሕይወቱ “በፈረስ ታጅቦ ንጉሥ መሆኑን አትፈልግ ብዙ ሚስቶችን ለራስህ አትያዝ ወርቅና ብር ለራስህ ብዙ አትፈልግ ተብሎ (ዘዳ፡ 17፥14-17) ላይ የተጻፈውን እነዚህን ሦስት ነገሮችን እግዚአብሔር በቃሉ በኩል የተናገረውን የእግዚአብሔርን ሕግ በመተላለፍ ኃጢአት አደረገ፡፡ (1ኛ ነገ፡ 10፥26-29፤ 11፥3-4)

በመጨረሻም ሰሎሞን በአጭር ጊዜ ሞተ፡፡ ትልቅ በሕዝብ ገንዘብ ለራሱ በ7 ዓመቱ ቤተመንግሥት አሰራ፡፡ ደግሞም በአሥራ ሦስት ዓመት ተሰርቶ እንዲጠናቀቅ

በማድረጉ የእስራኤል ሰዎችን በማድከሙ የሰሜኑና የደቡቡ እስራኤል እንዲከፋፈል ምክንያት ሆነ በዚህ ምክንያት እግዚአብሔር ተቆጣው፡፡

እግዚ/ር ሰሎሞንን “እኔ ላንተ ምን እንድሰጥህ ትፈልጋለህ” ብሎ ሲጠይቅ ሰለሞን የእስራኤልን ሕዝብ የሚመራበትን ጥበብ እፈልጋለሁ አለ፡፡ (1ኛ.ነገ. 3፥2-15) እግዚአብሔር እንደፈቃዱ ለሚኖሩት ሰዎች ብዙ ፀጋ ይሰጣቸዋል፡፡ እኛ ደግሞ በመጀመሪያ ወደ እግዚአብሔር በመሄድ ከእግዚአብሔር ጋር የጥሞና ጊዜ በማሳለፍ ተስፋ በማድረግ የእግዚአብሔርን ፈቃድ በመከተል ሥራዎቻችንን ልንሰራ ያስፈልጋል፡፡ (ያዕ፡ 4፥3) ሰሎሞን ይህንን የእግዚአብሔርን ፈቃድ አውቆ ሲፀልይ እግዚአብሔር እርሱ ያልለመነውን ጥበብና ክብር ባለጠግነትም ሁሉ ሰጠ፡፡ እኛም ደግሞ ብዙ ፀጋንና ጥበብን ከእግዚ/ር ቢንለምን እንደ ሰለሞን ተጨማሪ ነገሮችን ጌታ ሊሰጥ ይችላል፡፡

ሰሎሞን በዚያን ጊዜ እጅግ ጥበበኛ ሰው ነው፡፡ ምክንያቱም እግዚአብሔር ለሰሎሞን ጥበብን ሰጥቷልና፡፡ (ያዕ፡ 1፥5) እግዚአብሔር በፍጹም ልብ ለሚፈልጉ ሰዎች እነርሱ ሳያውቁ ትልቅ ሥራ የሚሠሩበት ሚስጥራዊ ሀይል ይሰጣል፡፡ (ትኤር፡ 33፥2,3) ስለዚህ እኛ እንደ ሰሎሞን ወደ እግዚአብሔር በመፀለይ እግዚአብሔር የሰጠውን ሥራ በደንብ ለመሥራት ሥልጣንና ኃይል ችሎታም ልንቀበል ያስፈልጋል፡፡

ሰሎሞን ንጉሥ ከሆነ በኋላ የመጀመሪያው ሥራ ቤተመቅደሱን መገንባቱ ነው፡፡ (1ኛ ነገ፡ 6፥1) ሰሎሞን አስቀድሞ የእግዚአብሔርን መንግሥትና ጽድቅ ለመፈለግ አቋም ወሰደ፡፡ እርሱ በጣም በሚያምሩና በውድ ዕቃዎች የእግዚአብሔርን ቤተመቅደስ እንደሠራ ሁሉ እኛም ለእግዚአብሔር ጊዜያችንን ገንዘባችንና እውቀታችንን በመሥጠት የእግዚአብሔርን ቤት ሥራ መሥራት ያስፈልጋል፡፡ እኛ ከማንኛውም ነገር አስቀድመን የእግዚአብሔር ቤት ሥራ ለመሥራት ፍላጐት ሊኖረን ያስፈልጋል፡፡ (ማቴ፡ 6፥33)

ሰሎሞን በመጨረሻ ጊዜ በብዙ ነገሮች ተሳሳተ፡፡ ሰሎሞን ብዙ የፈረንጅ ሴቶችን በማግባትና ጣኦትን በተራራ ላይ በማምለክ ኃጢአት ሰራ፡፡ (1ኛ.ነገ፡ 11፥1-8) ሰሎሞን ክብርን ፈልጐ የራሱን ደስታና የተመኘውን ወሰደ፡፡ እንደዚሁም እኛ ተልዕኮአችንን ረስተን ከእግዚአብሔር ክብር ይልቅ ምኞታችንን ወስደናልን? እኛ ለጥቂት ጊዜም እግዚ/ርን እንዳንተው ልባችንን በደንብ ልንጠብቅ ያስፈልጋል፡፡ (ምሳሌ 4፥23)

ምዕራፍ ሃያ አምስት

ሕያው እግዚአብሔርን የገለጠው ኤልያስ (1ኛ ነገ፡ 18፥16-24)

ኤልያስ ለንጉሥ አክዓብ ዝናብ እንደማይዘንብ ተነበየ፡፡ (1ኛ ነገ፡ 17፥1)

ኤልያስ በካራት ፋፋቴ ውስጥ ተሸሽጐ የሚኖር ሰው ነው፡፡ (1ኛ.ነገ፡ 17፥3-17)

ኤልያስ በሲዶና አጠገብ ባለችው በሲራኘታ መበለት ቤት ተቀመጠ፡፡ (1ኛ ነገ፡ 17፥8-16)

ኤልያስ የመበልቱን ልጅ ከሞት አስነሣ፡፡ (1ኛ ነገ፡ 17፥17-24)

ኤልያስ ንጉሡን አክዓብን ከአባአል ነቢያት ጋር ለመግጠም ጠየቀ፡፡ (1ኛ ነገ፡ 18፥19-24)

ኤልያስ የባአል ነቢያቶችን 450 **ሰዎች ገጥሞ አሸነፎ** (1ኛ ነገ፡ 18፥25-40)

ኤልያስ ዝናብን ከሰማይ አዘነበ፡፡ (1ኛ ነገ፡ 18፡41-45)

ኤልያስ ከአክዓበ ሚስት ከኤልዛቤል ዛቻ የተነሣ ወደ ኮረብ ተራራ ሸሸ፡፡ (1ኛ.ነገ. 19፥1-8)

ኤልያስ የእግዚአብሔር አስታራቂ በመሆን የእግዚአብሔርን ሥራ ሰራ (1ኛ ነገ፡ 19፥9-14)

ኤልሳዕ የኤልያስ አገልጋይ ነው፡፡ (1ኛ ነገ፡ 19፥19-21)

ኤልያስ የሶርያ ንጉሥ አክአብ እንደሚደመሰስ ተነበየ፡፡ (1ኛ ነገ፡ 21፥17-26)

ኤልያስ የሰማሪያ ንጉሥ አካዝያስ እንደሚሞት ተነበየ፡፡ (2ኛ ነገ፡ 1፥3,4)

ኤልያስ ኢዮራም የደቡባዊ ይሁዳ ንጉሥ እንደሚሆን ፈቃድ ተናገረ፡፡ (2ኛ ዜና፡ 21፥12-15)

ኤልያስ ኤልሳን ወራሽ አድርጎ አቆመ፡፡ (2ኛ ነገ፡ 2፥1-11)

ኤልያስ ወደ ሰማይ ዐረገ፡፡ (2ኛ ነገ፡ 2፥15)

ሰሎሞን ከሞተ በኋላ የሰሎሞን ልጅ ሮብአም ንጉሥ ሆነ፡፡ ለሴሜኑ ለአሥር ነገዶች ለእስራኤል ሕዝብ መሪ ሆነ፡፡ በእስራኤል ልጆች ላይ ከአመፀ በኋላ አክአብ ንጉሥ ሆነ፡፡ ነገር ግን በእግዚአብሔር ዓይን ፊት እርሱ ክፋ ሥራ አደረገ፡፡ (1ኛ ነገ፡ 16÷30) በናቦጥ ልጅ በኢዮርብዓም ኃጢአት መሄዱ ታናሽ ነገር መስለው የሲዶናውያንንም ንጉሥ የኤትበአልን ልጅ ኤልዛቤልን አገባ፡፡ ከዚያም በኋላ ለባአል በተራራ ላይ መስገጃ ዐፀድ በማቆም ባአልን አመለከ፡፡ (1ኛ ነገ፡ 16÷31)

ለኤልዛቤል የባአል 450 ነብያቶችና 400 የማምለኪያ አፀድን (የኤሻራ) ነቢያት የሚኖሩ ሲሆን ከእስራኤል ሰዎችም መካከል ለኤልዛቤል ባአል መስዋዕት የሚሰጡ አሉ፡፡ ኤልዛቤል ብዙ የእግዚአብሔር ነቢያትን አስገደለች፡፡ (1ኛ.ነገ.18÷19-ቁ. 4) እግዚአብሔር ይህንን መከራ አይቶ ስለ እስራኤል ሕዝብ ኤልያስን ላከ፡፡ ኤልያስም ለአክዓብ 3 ዓመት ከ6 ወር ዝናብ እንደማይዘንብ አስጠነቀቀ:: ኤልያስ ለአክዓብ የባአል 450 ነቢያት 400 የአፀድን ነቢያት በቀሪሜሎስ ተራራ ላይ ከራሱ ጋር እንድገጥሙ ጠየቀ፡፡

የግጥምያ አሸናፊ የሚሆነው የመስዋዕቱን ሥጋ ምንም እሳት ሳይጨመር ከሰማይ እሳት ወርዶ መስዋዕቱን የሚበላ ፀሎቱንም በእሳት የሚመልስ እርሱ አምላክ ይሁን በማለት ተናገረ፡፡

850 የባአል ነብያቶችንና የማምለኪያ አፀድን ነብያቶች ከጠዋቱ 1 ሰዓት እስከ 6 ሰዓት ድረስ ወደ አምላኮቻቸው ሲፀልዩ ከሰማይ እሳት መውረድ አልቻለም፡፡ (1ኛ.ነገ.18÷25-29) ኤልያስ በተራው ከሰዓት በኋላ ፈርሶ የነበረውን መሰዊያ አድሶ የአብርሃም የይስሃቅ የያዕቆብ አምላክ በማለት ፀልዮ ከሰማይ እሳትን አወረደ፡፡ ከሰማይ የወረደው እሳት መስዋዕትን ሁሉ በላ ውሃውንም ላሰ፡፡ (1ኛ.ነገ.18÷30-38)

ይህንን ታምራት ያዩት ሰዎች እግዚአብሔርን አምላክ መሆኑ አምነው የባአል ነቢያትንና አፀዶችን ሁሉ ማለትም 450 የባአል ነቢያትንና 400 የአፀድን ነቢያቶችን ገደሉ፡፡ (1ኛ.ነገ.18÷39-40)

በቀርሜሎስ ተራራ በተደረገው ግጥሚያ ኤልያስ አሸነፈ፡፡ በኋላ ለ3 ዓመት ተኩል የተቋረጠው ዝናብ በምድር ላይ እንዲዘንብ አደረገ፡፡ ነገር ግን ከዚህ ድርጊት በኋላ የአካአብ ሚስት ኤልዛቤል ኤልያስን ለመግደል ስለፈለገች ከእርሷ ዛቻ የተነሣ ወደ ኮረብ ተራራ ሸሸ፡፡ ኤልያስ የኤልዛቤልን ዛቻ ሰምቶ ወደ እግዚአብሔር እንዲህ ሲል ፀለየ፡፡ “ይበቃኛል አሁንም አቤቱ እኔ ከአባቶች አልበልጥምና ነፍሴን ውሰድ” ብሎ እንዲሞት ለመነ፡፡ (1ኛ ነገ፡ 19÷4)

እግዚአብሔር ለኤልያስ መልስ የሰጣቸው መንገዶች

ለባአል ነቢያት በጉልበታቸው ያልተበረከኩና በከንፈራቸው ያልሳሙ 7 ሺ ሰዎች አሉ ብሎ ተናገረ፡፡ (1ኛ ነገ፡ 19÷18)

እርሱ ኃይል እንዲያገኝ በቁራዎች አማካይነት ምግብ ሰጠ፡፡ (1ኛ ነገ፡ 19፥7)

እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር በትንሽ ዝምታ ድምፅ ተገናኘ፡፡ (1ኛ ነገ፡ 19፥12)

በመጨረሻ እርሱ ከኤልሳዕ በፊት በሰረገላው እሳት ተነጥቆ ወደ ሰማይ እንደሚሄድ ተናገረ፡፡ (2ኛ ነገ፡ 2፥11)

ኤልያስ እንደ እኛ ሥጋ ለባሽ ነው፡፡ (ያዕቆ፡ 5፥17,18) **ነገር ግን በእምነት ኤልያስ ከሰማይ እሳትን አውርዶ መስዋዕቱን እንዲበላ ሲፀልይ ከሰማይ እሳት ወርዶ መሰዋዕቱን በላ፤ ደግሞም ለ**3 **ዓመት ተኩል በምድር ላይ ያልዘነበው ዝናብ እንዲዘንብ አደረገ፡፡** (1ኛ ነገ፡ 18፥33-41) **እንደዚሁም የእግዚአብሔርን ታላቅ ሥራ በፀሎት በኩል እንደሚደረግ ልንገነዘብ ያስፈልጋል፡፡**

ስለዚህ እኛ ደግሞ በመካራችንና በደስታችን ጊዜ ሁልጊዜ በፍጹም እምነት መፀለይ ያስፈልጋል፡፡ (1ኛ ተሰ፡5፥17,18) **ታላቅ ነቢይ የሆነው ኤልያስ የኤልዛቤልን ዛቻ ሰምቶ በመፍራት ራሱን አብረክርኮ ተጨንቆ ነበር፡፡** (1ኛ ነገ፡ 19፥1-4) **ነገር ግን እግዚአብሔር ለኤልያስ ሥልጣንና ታላቅ ኃይል ሰጥቶ አበረታታ፡፡**

እኛ ችግሮችና መከራዎች በሚመጡ ጊዜ እግዚአብሔር ከእኛ ጋር እንደሚኖር ማወቅ ያስፈልጋል፡፡ (ሮሜ፡ 8፥28) **ኤልያስ እግዚአብሔርን ትተው ባአልን ያመለኩትን ማንኛውም ሰው የከፍተኛ ማዕረግ ያለው ሰው ቢሆን፣የዝቅተኛ ማዕረግ ያለው ሰው ቢሆን፣ሁሉንም ስለ ኃጢአታቸው ወቀሰ፡፡** (አ/መ/ት/1ኛ.ነገ፡ 21፥20-26 **ወይንም በ**54 **እትም** 1ኛ.ነገ.20፥20-26)

ኤልያስ የእግዚአብሔርን ቃል በፍጹም ልብ በማመንና በመታዘዝ ጠንክሮ እውነቱን ተናገረ፡፡ እኛ ደግሞ የእግዚአብሔርን ቃል በፍጹም ልብ በማመንና በመታዘዝ ለሁሉም ሰዎች የጌታን ወንጌል ልናስተምር ይገባናል፡፡ (ኢሳ፡ 44፥8)

ምዕራፍ ሃያ ስድስት

ሁለት እጥፍ መንፈስን የፈለገው ኤልሳዕ (2 **ነገ፡** 2፥7-14)

ኤልሳዕ ከኤልያስ ጋር ከመገናኘት በፊት

ኤልሳዕ ገበሬ ነው፡፡ (1ኛ **ነገ፡** 19፥19)

ኤልሳዕ ከኤልያስ ጋር ከተገናኘ በኃላ

ኤልሳዕ የኤልያስ ደቀ መዛሙርት ነው፡፡ (1ኛ **ነገ፡** 19፥20-21)

ኤልሳዕ ከኤልያስ ቀጥሎ የሚተነብይ ነቢይ ነው፡፡ (2ኛ **ነገ፡** 2፥2-11)

ኤልሳዕ ኤልያስ በእሳት ሰረገላ ወደ ሰማይ ሲያርግ አይተዋል፡፡ (2ኛ **ነገ፡** 2፥11-13)

ኤልሳዕ የመጀመሪያ ታአምራት አደረገ፡፡ (2ላይ ኛ **ነገ፡** 2፥14)

በኤልሳዕ ላይ የእግዚአብሔር መንፈስ እንዳረፈ ነቢያቶች ተሰማሙ፡፡ (2ኛ **ነገ፡** 2፥15)

ኤልሳዕ የሚሳለቁ ልጆችን ረገማቸው፡፡ (2ኛ **ነገ፡** 2፥23,24)

ኤልሳዕ የኢያሪኮ መራራውን ውሃ አጣፈጠ፡፡ (2ኛ **ነገ፡** 2፥19-22)

ኤልሳዕ ለአንዲት ድሃ መብልት ጥቂቱን ዘይት ብዙ አደረገ፡፡ (2ኛ **ነገ፡** 4፥1-7)

ኤልሳዕ የሱናማዊትን ልጅ ከሞት አስነሣ፡፡ (2ኛ **ነገ፡** 4፥17-37)

ኤልሳዕ በወጡ ውስጥ ያለውን መርዝ ወደ መልካምነት ለወጠ፡፡ (2ኛ **ነገ፡** 4፥38-41)

ኤልሳዕ በ20 **በገብስ እንጀራ** 100 **ሰዎችን መገበ፡፡** (2ኛ **ነገ፡** 4፥42-44)

ኤልሳዕ ለምጻሙን ንዕማንን ፈወሰ፡፡ (2ኛ **ነገ፡** 5፥1-19)

ኤልሳዕ በወንዝ ውሃ ውስጥ የተጣለውን መጥረቢያ በውሃ ላይ እንድንሳፈፍ በማድረግ ታአምራት አደረገ፡፡ (2ኛ **ነገ፡** 6፥1-7)

ኤልሳዕ ራሱን ለመያዝ የመጡትን የሶሪያ ጦር ሠራዊቶችን ዐይን እንድታወሩ ካደረገ በኋላ ወደ ሰማሪያ ወሰዳቸው፡፡ (2ኛ **ነገ፡** 6፥10-23)

ኤልሳዕ የሰማሪያ ከተማ ከመቅሰፍት እንደሚተርፍ ተነበየ፡፡ (2ኛ **ነገ፡** 7፥1-20)

ኤልሳዕ የደማስቆ ንጉሥ ወልዴ አዴር (ቤንሃዳድ) እንደሚሞት ተነበየ፡፡ (2ኛ ነገ፡ 8፥7-10)

ኤልሳዕ ኢዩ ንጉሥ እንድሆን ቀባ፡፡ (2ኛ ነገ፡ 9፥1)

ኤልሳዕ ለእስራኤል ንጉሥ ለዮአስ እስራኤል እንደሚያሸንፍ ተነበየ፡፡ (2ኛ ነገ፡ 13፥14-19)

የኤልሳዕ መሞት፡፡ (2ኛ ነገ፡ 13፥20)

ኤልሳዕ ኤልያስ በአውሎ ነፋስ በሠረገላው ላይ ወደ ሰማይ ሲሄድ አይቶ ከእግዚአብሔር በኤልያስ ላይ የነበረውን እጥፍ መንፈስ ተቅበሎ ያደረጋቸው <u>ሥራዎች፡-</u>

በኢያሪኮ ከተማ ውስጥ የነበረው ውሃ ምንጭ ክፉ ከመሆኑ የተነሣ የምድርቱን ፍሬ የሚያጨናግረውን በምንጩ ውስጥ ጨው በመጨመር የምድሪቱን ፍሬ ጭንገፋና ሞት ከለከለ፡፡ (2ኛ ነገ፡ 2፥20-22)

ከነቢያት ወገን አንዱ ለሆነው ሚስት ባለዕዳው መጥቶ ልጆቹን ስለ ዕዳው ለመውሰድ ስለሚፈልግ የነቢዩ ሚስት መጥታ በኤልሳዕ ፊት ስላለቀሰች ኤልሳዕ በቤቷ ውስጥ ያላትን ጥቂት ዘይት አትረፍርፎ ዕዳዋን እንድትከፍልና ልጆቿም እንድቀሩ አደረገ፡፡ (2ኛ ነገ፡ 4፥6-7)

የሱናማዊቱ ልጅ ከሞት አስነሣ፡፡ (2ኛ ነገ፡ 4፥32-37)

መራራውን ወጥ አጣፈጠው፡፡ (2ኛ ነገ፡ 4፥40-41)

በ20 በገብስ እንጀራ 100 ሰዎች መገበ፡፡ (2ኛ ነገ፡ 4፥42-44)

የጦር አዛዥ (ጀኔራል) የሆነውን የንዕማን ለምጽ ፈወሰ፡፡ (2ኛ ነገ፡ 5፥14-19)

ከነቢያት ወገን ከሆነው ከአንድ መጥረቢያ በውሃ ውስጥ የጠፋውን በውሃ ላይ እንዲንሳፈፍ አደረገ፡፡ (2ኛ ነገ፡ 6፥6-7)

የሞአብ አደጋ ጣዮች በሚመጡበት ጊዜ የእስራኤል ሰዎች የሞተው በኤልሳዕ መቃብር አጠገብ ልቀብሩ ሲሉ አደጋ ጣዮች ስለመጡ በኤልሳዕ መቃብር ላይ ረሳውን ሰጥሉ ሰውየው ዳነ፡፡ (2ኛ ነገ፡ 13፥21)

አንድ ቀን የሶርያ ንጉሥ እስራኤልን ለመውጋት በምስጢር ወደ እስራኤል ሕዝብ በሚመጣበት ጊዜ እግዚአብሔር ለነቢዩ ኤልሳዕ አስቀድሞ የሚመጣውን ስላሳወቀ

ኤልሳዕ ለእስራኤል ንጉሥ አሳወቀ፡፡ ከዚህ የተነሣ ኤልሳዕ የሚኖርበትን ዳይታን ከበቡ፡፡ (2 ነገ፡ 6÷14) የኤልሳዕ አገልጋይ የአራም ሠራዊት በዙሪያ ከብበው “ጌታዬ ሆይ ምን እናደርጋለን?” ብሎ ጠራ፡፡ ኤልሳዕም “አትፍራ ከእኛ ጋር ያሉት ከእነርሱ ጋር ካሉት ይበልጣልና” ብሎ (2 ነገ፡ 6÷16) ስለጭንቀቱ በእግዚአብሔር ላይ ያለው የእምነት አቋም ነገረው፡፡

እኛ ደግሞ ስለኃጢያት ስለችግሮች ብዛት ስለሰይጣን ፈተና ሳንጨነቅ የእግዚአብሔር መልአክ እኛን ለመርዳት በዙሪያችን መኖራቸውን ማመን አለብን፡፡ ኤልሳዕም ስለ ሎሌው አይን እንዲከፈት ፀለየ፡፡ ዓይኑም ተከፈተ (2.ነገ፡ 6÷17) በዚህ ጊዜ የኤልሳዕ ሌሎው ዓይን ተከፍቶ በዙሪያው ያሉትን የእግዚአብሔር መላእክትን ካየ በኋላ መፍራቱን ተወው፡

እኛ በዓለም ላሉት ችግሮች ሳንወድቅ እግዚአብሔርን በማመን ችግሮቻችንን ሊናሸንፍ ያስፈልጋል፡፡ አንዳንድ ሁከቶች በሚኖሩበት ጊዜ እግዚአብሔርን በመተማመን በእምነት የሚናሸንፍ ሰዎች መሆን አለብን፡፡ የእኛ መንፈሳዊ ዓይኖች ተከፍቶ የሕያው እግዚአብሔርን ሥራ ሊያዩ ያስፈልጋል፡፡

ኤልሳዕ ኤልያስ ሲጠራ ወዲያውኑ እርሱን ተከተለው (1ነገ፡ 19÷20፤ 2 ነገ፡ 2÷1-11) ኢየሱስ 12 ደቀመዛሙርቱን ሲጠራቸው ሁሉንም ነገር ትተው ኢየሱስን ተከተሉ፡፡ እኛ ደግሞ እግዚአብሔርን ለማገልገል ወዲያውኑ እምነን ልንከተል ያስፈልጋል፡፡ ሁለት እጥፍ መንፈስ የተቀበለው ኤልሳዕ የነቢይነትን ተልዕኮ ለመሥራት በእምነት በእግዚአብሔርና በሰው ዘንድ ተስማማ፡፡ (2 ነገ፡ 2÷14-15፤ 4÷9፤ 6÷17)

እኛ ደግሞ የእግዚአብሔርን ቃል ለመፈጸም በመታዘዝ ልንሠራ ያስፈልጋል፡፡ ኤልሳዕ ብዙ ሥልጣን ላለው የአራም ንጉሥ የሠራዊቱ አዛዥ የሆነው ንዕማንን ከለምጽ ፈወሰ፡፡ (2.ነገ 5÷1-14) ይህ ሰው ጠላቶችን በመውደድ የእግዚአብሔርን ቃል ታዘዘ፡፡ (ማቴ፡ 6÷44)

እኛ ደግሞ እኛን የሚጠሉት ሰዎችን በእግዚአብሔር ፍቅር ልንወድድ ያስፈልጋል፡፡ ኤልሳዕ የእስራኤል ሰዎች በሚጨነቁበት ጊዜ እግዚአብሔር እንዲጠብቃቸው ወደ እግዚአብሔር ፀለየ፡፡ (2.ነገ፡ 6÷8-23) እኛም ሀገራችንን እግዚአብሔር ሁልጊዜ እንዲጠብቅና እንድመራ ልንፀልይ ያስፈልጋል፡

ምዕራፍ ሃያ ሰባት

እግዚአብሔርን ያመነ ሕዝቅያስ (2 **ነገ፡** 18፥1-8)

ሕዝቅያስ የንጉሥ እንደራሴ ሆነ፡፡ (2ኛ **ነገ፡** 18፥2)

ሕዝቅያስ በ25 **ዓመቱ ንጉሥ ሆነ፡፡** (2ኛ **ነገ**፥18፥2)

ሕዝቅያስ የእግዚአብሔርን ቤተመቅደስ ጠግኖ ሃይማኖትን አሻሻለ፡፡ (2ኛ **ዜና፡** 29፥3-36)

በከረብታዎች ላይ ያሉት የጣኦት መስገጃዎችን አስወገደ፡፡ (2ኛ **ነገ፡** 18፥4)

ሕዝቅያስ የፋሲካ በዓል አደረገ፡፡ (2ኛ **ዜና፡** 31፥1)

ሕዝቅያስ የፍልስጥኤምን ምድር ማርኮ ስለወሰደ ፍልስጥኤማውያን በእስራኤል10**ሩ ነገዶች ላይ ሁለት ጊዜ አደጋ በመጣል ያሉበትን ዙሪያ ከበው ስለያዙ ሕዝቅያስ በደለኛ እኔ ነኝ በማለት የፍልስጥኤማውያን ሰራዊት እንዲመለሱ ተናገረ፡፡** (2ኛ.ነገ. 18፥9 - ምዕ.19፥34)

ሕዝቅያስ ኩሬውንና መስኖ ሰርቶ ወደ ከተማው ውሃ እንዲመጣ አደረገ፡፡ (2ኛ **ነገ፡** 20፥20)

ሕዝቅያስ በጣም በፀና ታመመ፡፡ (2ኛ **ነገ፡** 20፥1)

ሕዝቅያስ እግዚአብሔር ከሞት እንዲፈወስ አጥብቆ ሲፀለይ እግዚአብሔርም ለሕዝቅያስ 15 **ዓመት ጨመረ፡፡** (2ኛ **ነገ፡** 20፥2-11)

ሕዝቅያስ ዕድሜ ስለተጨመረ የምስጋና ቃል ጻፈ፡፡(**ኢሳ፡** 38፥9-22)

ሕዝቅያስ ከባቢሎን ወደ ይሁዳ ለመጡት ሰዎች የግምጃ ቤቱን ጠቅላላ ንብረት አሳየ፡፡ (2ኛ **ነገ፡** 20፥12-15)

ኢሳይያስ ደባባዊ ይሁዳ እንደምትማረክ ተነበየ፡፡ (2ኛ **ነገ፡** 20፥16-21)

ሕዝቅያስ በ54 **ዓመቱ ሞተ፡፡** (2ኛ **ነገ፡** 20፥20,21)

ሕዝቅያስ በ25 **ዓመት ንጉሥ ከሆነ በኋላ ለ**29 **ዓመታት መራ፡፡ የሕዝቅያስ አባት አሃዝ በሚመራበት ጊዜ ኤዶምና ፍልስጥኤም ስለተዋጉ የሃይማኖትን ሁኔታ አደነጋገረ፡፡ ነቢዩ ኢሳይያስ ለንጉሥ አሀዝ የእግዚአብሔርን ቃል በእምነት ሲናገር አልታዘዘም፡፡ ነገር ግን ሕዝቅያስ ንጉሥ ከሆነ በኋላ የፓለቲካና የሃይማኖት ሁኔታ**

ማሻሻል አደረገ፡፡ በኮረብታዎች ላይ ያሉትን የጣኦት መስገጃዎትን አስወገደ፡፡ ሐውልቶችንም ቀለጣጠመ፣ የማምለኪያ አፀዶችንም ቆረጠ፡፡ ደግሞ በምድረ በዳ ሙሴ ያሰራውን የናሐስንም እባብ እስከዚያ ድረስ እስራኤላውያን ስለሚያመልኩ ሙሴ ለሰራው ለነሀስ እባብ እጣን ስለሚያጠኑለት ሕዝቅያስ ሰበረው፡፡ (2ኛ ነገ፡ 18፥4)

ሕዝቅያስ ቤተመንግሥትን ካፀዳ በኃላ (2ኛ.ዜና.29፥15) ከሰሜኑ እስራኤል ጋር የፋሲካን በዓል አደረገ፡፡ በመጨረሻው በኢየሩሳሌም ታላቅ ደስታ በማድረግ ተደሰቱ፡፡ ሕዝቅያስ ከእግዚአብሔር ጋር የሚኖር ሰው ነው፡፡ እግዚአብሔርም ከእርሱ ጋር ስላለ የሚያደርገውንም ነገር ለእግዚአብሔር ደስታ ያደርጋል፡፡ ይህ ሁሉ ያደረገው በእግዚአብሔር ላይ ባለው እምነት ነው፡፡ (ዕብ፡ 11፥5-6)

የሕዝቅያስ ስም ትርጉም “እግዚአብሔር ሥልጣኑን ይሰጣል” ማለት ነው፡፡ ሕዝቅያስ እንደ ስሙ እግዚአብሔርን በሰጠው ሥልጣን ሃይማኖትን፣ ፓሌትካንና ጦርነትን አደረገ፡፡ ከዚህ የተነሣ ሕዝቅያስ እግዚአብሔር ወደ ማንኛውም ስፍራ ሲሄድ ሠላምን ሰጠ፡፡ (2ኛ.ነገ.18፥7)

ሕዝቅያስ እግዚአብሔርን ለማየት የሚመኝ ሰው ነው፡፡ ይህ የሚያሳየው በእግዚአብሔር ፊት አለመሸሸጉንና ተንኰል የሌለበት ሰው መሆኑን ነው፡፡ እግዚአብሔር የልቡን ታማኝነት እንዲሁም ምኞቱን አይቶ ተደስቷል፡፡ (1ኛ ዜና፡ 29፥17) ሕዝቅያስ በእግዚአብሔር ላይ እምነቱን አደረገ፡፡ አሥሩን ጠላቶች እግዚአብሔርን ለመስደብና ራሱን ልያፈዙ ደብዳቤ በላኩ ጊዜ ወደ እግዚአብሔር ቤት በመግባት እግዚአብሔርን ፀለዮ ጦርነቱን አሸነፈ፡፡

ሕዝቅያስ ወደ ሞት የሚያደርስ ሕመም ሲታመም ነቢዩ ኢሳይያስ ወደ እርሱ በመሄድ እንደሚሞት ተናገረ፡፡ በዚያን ጊዜ ሕዝቅያስ ወደ እግዚአብሔር በፀና ፀለየ፡፡ እግዚአብሔርም የሕዝቅያስ ፀሎት ሰምቶ በዕድሜው ላይ 15 ዓመት ጨመረ፡፡ (2ኛ.ነገ.20፥1-6) ነገር ግን ሕዝቅያስ ልብ ስለታበየ ከእግዚአብሔር ዘንድ ስለተደረገው ነገር ተገቢ ምላሽ አልሰጠም፡፡ ከዚህም የተነሳ በይሁዳና በኢየሩሳሌም ላይ የእግዚአብሔር ቁጣ ወረደ፡፡ (2ኛ.ዜና.32፥24-25) እኛ ደግሞ እንደ ሕዝቅያስ እንዳንታበይ ሀሳባችንን ልንመረምር ያስፈልጋል፡፡

ሕዝቅያስ የአባቱን የአሃዝን ምግባረ ብልሹ ፖለቲካ አልተከተለም፡፡ ሕዝቅያስ በመጀመሪያ የሃይማኖት ማሻሻል አደረገ፡፡ እኛ ደግሞ ዓለምን ሳንከተል በንጹሕ ሕሊና የጌታ ልጅ በመሆን እምነታችን በአቋም ልንገልጽ ያስፈልጋል፡፡(ሮሜ፡ 12፥2) ሕዝቅያስ የባቢሎን ንጉሥ ወደ እርሱ ለላካቸው መልዕክተኞች በትዕቢት ተሞልቶ የጦር ሠራዊት ዕቃ የሚቀመጥበት ቦታና ቤተመዛግብትን ሁሉ ጠቅላላውን አሳያቸው፡፡ (2ኛ.ነገ. 12፥13)

እነዚህ የቤተመንግስት ወርቅንና ብር ሌሎች ንብረቶችን ያዩ የባብሎን ሰዎች ያንን የተመለከቱትን ለመውሰድ ከይሁዳ ጋር ጦርነት አድርገው ሁሉንም ሳያስቀሩ ወደ ባብሎን ይዘው ሄዱ፡፡ (2ኛ.ነገ.25፥13-15) **እኛ እምነት በሚኖረበት ጊዜ አስቀድመን የእግዚአብሔርን መንግሥትና ጽድቅ ልንፈልግ ያስፈልጋል፡፡ እኛ ፈተና እንዳይወስደን በደንብ በትህትና የእግዚአብሔርን ጽድቅ ልንጠይቅ ያስፈልጋል፡፡**(ማቴ፡ 6፥33)

ምዕራፍ ሃያ ስምንት

የሃይማኖትን ተሃድሶ ያደረገው ኢዮስያስ (2ኛ.ነገ.22፥1-11)

ኢዮስያስ የእግዚአብሔር ሰው እንደተነበየ የተወለደ ሰው ነው፡፡ (1ኛ.ነገ.13፥1-2)

ኢዮስያስ አባቱ አሞፅ ከሞተ በኋላ በአባቱ ፋንታ በ8ኛው ዓመት ነገሠ፡፡ (2ኛ.ነገ. 21፥23-24)

ኢዮስያስ በ20ኛው ዓመት የመጀመሪያ የሃይማኖት ተሃድሶ አደረገ፡፡ (2ኛ ዜና፡ 34፥3)

ኢዮስያስ በ26ኛው ዓመት ቤተመቅደሱን ጠገነ (አበጀ)፡፡ (2ኛ ነገ፡ 22፥3-6)

ኢዮስያስ የሕግ መጽሐፍ አግኝቶ ታላቅ የንሰሐ ጊዜ አደረገ፡፡ (2ኛ ነገ፡ 22፥8-13)

ኢዮስያስ ከይሁዳና ከኢየሩሳሌም ሰዎች ጋር የሕጉ መጽሐፍ ሰምቶ ለመፈጸም ቃል ኪዳን አደረገ፡፡ (2ኛ ነገ፡ 23፥1-3)

ኢዮስያስ ታላቅ የሃይማኖት ተሃድሶ አደረገ፡፡ (2ኛ ነገ፡ 23፥4-15)

ኢዮስያስ የፋሲካን በዓል ጠበቀ፡፡ (2ኛ ነገ፡ 23፥23)

ኢዮስያስ በአሦር ጦርነት ጊዜ በመጊዶ ሞተ፡፡ (2ኛ ነገ፡ 23፥29)

ኢዮስያስ በኢየሩሳሌም መቃብር ሥፍራ ተቀበረ፡፡ (2ኛ ነገ፡ 23፥30)

ኢዮስያስ በ8ኛ ዓመት ንጉሥ ከሆነ በኋላ ይሁዳን ለ31 ዓመት መራ፡፡ እርሱ ንጉሥ ከሆነ በ18ኛው ዓመቱ 1 ቤተ መቅደስን ሰርቶ የጨረሰ ታላቅ ቄስ ነው፡፡ ካህኑ ኬልቅያስ በእግዚአብሔር ቤተመቅደስ የሕግ መጽሐፍ አገኘ፡፡ ፀሐፊውም ሰፋን በንጉሱ ኢዮስያስ ፊት የሕጉን መጽሐፍ ወስዶ አነበበ፡፡ (2ኛ ነገ፡ 22፥8-13)

ንጉሥ ኢዮስያስ የሕጉን መጽሐፍ ሰምቶ ልብሱን አውልቆ ቀደደ የእግዚአብሔርንም ፈቃድ ለማወቅ ወሰነ፡፡ በዚህ ጊዜ ሴት ነቢይ ሕልዳና የይሁዳ ሰዎች ምግባረ ብልሹ እንደሆኑ ተነበየች፡፡ (2ኛ ነገ፡ 22፥14-15) **ንጉሡ ኢዮስያስ ሰዎችን ወደ እግዚአብሔር ቤተመቅደስ ጠርቶ አንድ ላይ በመሆን የሕጉን መጽሐፍ እንደ ዐውዱ ፍጹም እንድያደርጉ ቃል ኪዳን አደረገ፡፡ ንጉሥ ኢዮስያስ የእግዚአብሔር ማዕከል፣የመፅሀፍ ቅዱስ ማዕከልና የቤተክርስቲያን ማዕከል በመሆን ተሀድሶን አደረገ፡፡**

ኢዮስያስ የሃማኖት ተሃድሶ ካደረገ በኋላ በሁሉም ሥፍራ ያሉትን ጣኦቶችን ሁሉ በሰሜኑ እስራኤል በንጉሥ ኢዮርብዓም ጊዜ የነበሩትን ጣኦታትን ሁሉ አጠፋ፡፡ (2ኛ ነገ፡ 23÷10-23) ንጉሥ ኢዮስያስ የፋስካ በዓል እንድጠብቁ አዘዘ፡፡ (2ኛ ነገ፡ 23÷21፤ ዘዳ፡ 16÷1-8)

እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ የፋስካን ሕግ የጠበቁ፡- ንጉሥ ዳዊት፣ ሕዝቅያስና ኢዮስያስ ብቻ ናቸው፡፡ ኢዮስያስ የሃይማኖት ተሐድሶን ያደረገው ከፍጽም ልብ ነው፡፡ (2ኛ ነገ፡ 23÷25)ነገር ግን ኢዮስያስ በ38ኛው ዓመት በመግዶ ጦርነት ጊዜ ሞተ፡፡ ምክንያቱም ኢዮስያስ ጻድቅ ሰው ስለሆነ የይሁዳ ሰዎች ለእግዚአብሔር የማይታዘዙና ትዕቢተኞች ስለሆኑ እግዚአብሔር እንዚያን ኃጢአተኞች ከመፍረድ አስቀድሞ ንጉሡን በሞት ወሰደው፡፡

ንጉሡ ኢዮስያስ የ8 ዓመት ልጅ ሆኖ እያለ ያባቱን የአሞፅን ክፋት አልሰራም፡፡ (2ኛ.ዜና.33÷21-25) በዚህ ፋንታ እግዚአብሔርን ብቻ አገለገለ፡፡ (2ኛ ዜና፡ 34÷1-7) ንጉሡ ኢዮስያስ በመጀመሪያ ያደረገው የእግዚአብሔርን ቤተመቅደስ አደሰ፡፡ ከዚያም በኃላ ፌንጅች የሚያመልኩትን ጣኦት አምልኮ አጠፋ፡፡ በሁሉም አገሮች የእግዚአብሔርን ሕግ አወጀ፡፡

እኛ ደግሞ ዓለምን ሳንከተል የእግዚአብሔርን በጎ ፈቃድ አውቀን ልንኖር ያስፈልጋል፡፡ (ሮሜ፡ 12÷2) ንጉሡ ኢዮስያስ እንደ ቃሉ በመታዘዝ ኖረ፡፡ (2ኛ ነገ፡ 23÷21-25) እኛ ደግሞ እንደ ኢዮስያስ ከልባችን የእግዚአብሔርን ሕግ ፈቅደን ልንታዘዝ ያስፈልጋል፡፡ (ያዕ፡ 2÷14)

ኢዮስያስ ራሱ ንሰሐ ከገባ በኋላ የፌንጅን ጣኦት ለሚያመልኩ ሰዎች ያንን አስወግዶ የእምነትን ተሃድሶ አደረገ፡፡ (2ኛ ነገ፡ 22÷11-13) እኛ ደግሞ አስቀድመን ራሳችንን በቃሉ ፊት በማየት ልንለውጥ ያስፈልጋል፡፡ (ዕብ፡ 4÷12)

ምዕራፍ ሃያ ዘጠኝ

ሁለት ጊዜ እስራኤላዊያንን ያስተማረው ዕዝራ (ዕዝ፡ 7፥5-26)

ወደ ኢየሩሳሌም ከመመለሳቸው በፊት

ዕዝራ እስራኤላዊያንን የባቢሎን ንጉሥ ማርኮ የወሰዳቸውን ወደ ሀገራቸው ለመመለስ ፈቃድ የወሰደ የሕጉንም መፅሐፍ አምኖ የሚያስተምር አስተማሪ ነው፡፡ (ዘካ፡ 7፥6-11,26)

የይሁዳ ሰዎች ከባቢሎን ወደ ኢየሩሳሌም መመለስ ጀመሩ፡፡ (ዕዝ፡ 8፥1)

ዕዝራ ሌዋውያንን በሙሉ በአጎዋ ወንዝ ዳር ሰብስቦ አስተማረ፡፡ (ዕዝ፡ 8፥15-20)

የይሁዳ ሰዎች በሰላም እንዲመለሱ ዕዝራ የጾም ጸሎት አደረገ፡፡ (ዕዝ፡ 8፥21)

ወደ ኢየሩሳሌም ከተመለሱ በኃላ

የይሁዳ ሰዎች በሰላም ወደ ኢየሩሳሌም ደረሱ፡፡ (ዕዝ፡ 8፥32)

ዕዝራ የቤተመቅደሱን ዕቃዎችን ቆጠረ፡፡ (ዕዝ፡ 8፥33)

የእስራኤል ሰዎች ለእግዚአብሔር የሚቃጠል መስዋዕት አቀረቡ፡፡ (ዕዝ፡ 8፥35)

ዕዝራ ተሐድሶ አደረገ፡፡ (ዕዝ፡ 9-10)

ዕዝራ የሕግ መጽሐፍ አስተማረ፡፡ (ነህ፡ 8፥2-5)

ዕዝራ የይሁዳ ሰዎች እንዲመለሱ የመራና (ዕዝ፡ 7፥6) **የሕጉን ቃል የሚያስተምር ካህን ነው፡፡** (ዕዝ፡ 7፥6-10) **እርሱም ለሰዎች ሕጉን ካስተማረ በኋላ ሰዎችም በማስተዋል ንስሐ ለመግባት ተነሱ፡፡** (ዕዝ.10፤ነህ.8) **ዕዝራ የይሁዳ ሰዎች በሚመለሱበት ጊዜ የባሳ ንጉሥ ርዳታ ሳይፈልግ በእግዚአብሔር ርዳታ ሕዝቡን የመለሰ ካህን ነው፡፡** (ዕዝ፡ 8፥21-23) **ሕዝቡ ወደ ኢየሩሳሌም እንዲመለሱ ዕዝራ በትህትና ወደ እግዚአብሔር የፀለየ ሰው ነው፡፡ ደግሞም ከተመለሱ በኋላ ችግሮች በሚኖሩበት ጊዜ ጾም ፀሎት ያወጀ ሰው ነው፡፡** (ዕዝ፡ 8፥21-23፤ 9፥3-15፤ 1፥1-15) **ዕዝራ የሕዝቡን ስህተት የራሱ ስህተት አድርጐ በሐዘን ተቀብሎ በእግዚአብሔር ፊት ንሰሐ የገባ ሰው ነው፡፡** (ዕዝ 9፥1-15)

ዕዝራ የባሳን ንጉሥ በቅንነት አገለገለ፡፡ ከኋላም የባሳ ንጉሥ የይሁዳ ሰዎችን ይዞ ወደ አገራቸው ወደ ኢየሩሳሌም እንዲሄድ ፈቃድ ሰጠ፡፡ በዚህን ጊዜ ዕዝራ ሕዝቡን መራቸው፡፡ (ዕዝ፡ 7÷6-28) እንደዚሁም እግዚአብሔር በቅንነት ለተዘጋጁ በትህትና የራሱን ሥራ እንዲሠሩ ተስፋ ይሰጣል፡፡ (ማቴ፡ 25÷21) ዕዝራ የሙሴን ሕግ የሚያስተምር አስተማሪና በእግዚአብሔር ፊት በእምነት የሚኖር ሰው ነው፡፡ (ዕዝ፡ 8÷21-23፤ 9÷3-15)

እኛ ደግሞ የእግዚአብሔርን ቃል ከመስበካችን በፊት በቃሉ ፊት ራሳችንን ልንመረምር ያስፈልጋል፡፡ ዕዝራ የይሁዳ ሰዎችን ወደ ኢየሩሳሌም ሲመራ በራሱ ጥበብና በጦር ሠራዊት ጉልበት አልተመካም፡፡ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ በጾም ፀሎት ከእግዚአብሔር ርዳታውን ጠየቀ፡፡ እግዚአብሔር የፀሎቱን ምላሽ በመስጠት የይሁዳ ሰዎችን በሰላም ወደ ሀገራቸው መለሳቸው፡፡ (ዕዝ፡ 8÷21-34) እኛ ደግሞ እንደ ዕዝራ በእኛ ጥበብና በጦር ሠራዊት ሳንመካ በእግዚብሔር ኃይል ልንታመን ያስፈልጋል፡፡ (ምሳሌ 16÷1)

ዕዝራ ሕዝቡ በእግዚአብሔር ፊት ኃጢአት ባደረጉ ጊዜ ራሱ ኃጢአት እንዳደረገ በመቁጠር ልብሱን በመቅደድ ጾም ፀሎት አደረገ፡፡ እኛ ደግሞ የጎረቤቶቻችን ሐዘን እንደ ራሳችን በመቀበል አብረን የምንፀልይ ሰዎች መሆን ያስፈልጋል፡፡ (ዕዝ፡ 9÷5፤ ማቴ፡ 7÷1-5)

ዕዝራ የእስራኤል ሰዎችን የፈረንጅ ሰዎችን ስላገቡት ሰምተው ንሰሐ ከጠየቀ በኋላ የፈንጅ ሴቶችን ወደ ቤተሰቦቻቸው እንዲመለሱ አደረገ፡፡ (ዕዝ፡ 10÷3) እኛ ደግሞ በእግዚአብሔር ፊት ኃጢያተኞች መሆናችንን ወዲያውኑ በማወቅ በኃጢያተኞች መካከል መኖራችንን ሳንዘነጋ ስለኃጢያታችንና ስለኃጢያታቸው እግዚአብሔርን ንሰሐ ልንጠይቅ ያስፈልጋል፡፡

ምዕራፍ ሰላሳ

የኢየሩሳሌምን ቅጥር የገነባ ነህምያ (ነህ፡ 2፥11-20)

ኢየሩሳሌም ከመገንባቱ በፊት

ነህምያ በንጉሡ በአርጠክስስ ፊት ጠጅ አሳላፊ ነው፡፡ (**ነህ**፡ 1፥11)

ነህምያ የኢየሩሳሌም ቅጥር መፍረስ ሰምቶ በጾም ፀሎት ፀለየ (**ነህ**፡ 1፥2-11)

ንጉሥ አርጠክስስ ነህምያ ወደ ኢየሩሳሌም እንዲሄድ ፈቃድ ሰጠ፡፡ (**ነህ**፡ 2፥1-8)

የመጀመሪያ ከምርኮ መመለስ

የይሁዳ ሰዎች ከምርኮ መመለስ፡፡ (**ነህ**፡ 2፥11)

ነህምያ የኢየሩሳሌምን ቅጥር እንደገና የመሥራት መጽናናት፡፡ (**ነህ**፡ 2፥12-20)

የኢየረሳሌምን ቅጥር እንደገና ሥራ ተጀምሮ በተቃውሞ ምክንያት መቋረጥ፡፡ (**ነህ**፡ 4፥1-23)

ነህምያ የይሁዳ ሰዎችን ወደ ተሐድሶ የመራ ሰው ነው፡፡ (**ነህ**፡ 5፥1-19)

የኢየሩሳሌም ቅጥር እንደገና ተጀምሮ ተጨረሰ፡፡ (**ነህ**፡ 6፥1-19)

የኢየሩሳሌም ቅጥር ከተገነባ በኃላ

ነህምያ የኢየሩሳሌም ቅጥር በሚሠሩበት ጊዜ ዘበኞችን አዘጋጅቶ አቆመ፡፡ (**ነህ**፡ 7፥1-4)

ነህምያ በመጀመሪያ ከምርኮ የተመለሱትን ሰዎች ቆጠራቸው፡፡ (**ነህ**፡ 7፥5-23)

ነህምያ ሕዝቡን ወደ ንሰሐ መራ፡፡ (**ነህ**፡ 8-10)

ነህምያ የሃይማኖትን ሂደት አስተካከለ፡፡ (**ነህ**፡ 11-12)

ነህምያ ወደ ፔሪሽያ ተመለሰ፡፡ (**ነህ**፡ 13፥6,7)

በሁለተኛ ዙር የተመለሱ የይሁዳ ሰዎች፡፡ (**ነህ**፡ 13፥6,7)

በመጨረሻም ሕዝቡ ሁሉ ወደ ተሐድሶ መራ፡፡ (**ነህ**፡ 13፥1-31)

ነህምያ በንጉሡ ባሳ ቤት ጠጅ አሳላፊዎች አለቃ ሆኖ በሚኖርበት ጊዜ የኢየሩሳሌም ቅጥር መፍረሱን ከሰማ በኋላ ወደ ንጉሡ መጥቶ የአባቶቻችን መቃብር ፈርሷልና እኔ ሄጄ የኢየሩሳሌምን ቅጥር እሠራለሁና ፈቃድ ይሰጠኝ በማለት ፈቃድ ከወሰደ በኋላ ወደ ኢየሩሳሌም ሄደ፡፡ ነህምያ ወደ ኢየሩሳሌም ከደረሰ በኋላ መሪዎችንና ሕዝብን ሁሉ በሥልጣን ሰበሰበ፡፡ ከዚያም በኋላ የኢየሩሳሌም ቅጥር ግንባታ ሥራ ተጀምሮ ወደ ፍጻሜም ደረሰ፡፡ በዚህ በመበረታታት ቁልፍ ሚና ተጫወተ፡፡ ደግሞ ጽኑ ተልዕኮ መኖሩን አሳየ፡፡ ይህ የኢየሩሳሌም ቅጥር ተገንብቶ የሚጠናቀቀው በእግዚአብሔር ፈቃድና የእግዚአብሔርን ፈቃድ በሚያምን ሰው ነው፡፡ (ነህ፡ 2÷20)

ነህምያ እግዚአብሔርን በፍጹም ልብ የታዘዘ ስለኢየሩሳሌም ቅጥር መፍረስ ከሰማ በኋላ ዖም ፀሎት ያደረገ (ነህ.1÷4) ንጉሡን ፈቃድ ከጠየቀ በኋላ ምላሽ አግኝቶ ሥራውን ሁሉ እግዚአብሔር እንድያከናውን ወደ እግዚአብሔር የፀለየ ሰው ነው፡፡ (ነህ.2÷4)

ነህምያ ተሳዳቢዎች በሚኖሩበት ጊዜ የጠላቶቹን ወሬ ሰምቶ ወደ እግዚአብሔር ፀለየ፡፡ (ነህ፡ 4÷4፤ 8-9) ጠላቶች በሚበዙበት ጊዜ የኢየሩሳሌም ቅጥር ስራ እንዲስተጓጎል ያደርጋሉ፡፡ ነገር ግን ነህምያ በዚህን ጊዜ የኢየሩሳሌም ቅጥር ስራ እንዳይስተጓጎል የህዝቡ እጆች እንዲበረቱ ወደ እግዚአብሔር ፀለየ፡፡ (ነህ.6÷9) አሁን የእኛ ልጆች በሥልጣን እንዲሠሩ ልንፀልይ ይገባናል፡፡ (ነህ፡ 6÷9) ነህምያ በጦርነት ጊዜ ብርቱ ሰው ነው፡፡ እርሱ ወደ እግዚአብሔር ሲፀልይ የተዘጋጁ ጠቢባን የሆኑ ሰዎች ማታ ይጠብቃሉ፡፡ (ነህ.4÷9) የሕዝቡ ግማሽ የኢየሩሳሌምን ቅጥር ሲሰሩ ግማሹ ደግሞ ጦርና ጋሻ ይዞ ጠላትን ይከለከላሉ፡፡ (ነህ.4÷6-20) የመለኮትን ድምፅ በሚሰሙበት ጊዜ ህዝቡ አንድ ላይ በመሆን ጠላቶቻቸውን ለመከላከል በአንድ እጅ ጦርና ጋሻ ይዘው የእግዚአብሔርን ቃል ይማራሉ፡፡ (ነህ፡ 4÷23)

ነህምያ የምሥጋናና የደስታን ጊዜ ሳይረሳ ሰዎችን የሕጉ ቃል እያስተምረ በንሰሐና በልቅሶ ወደ እግዚአብሔር ፊት ቀርባችሁ መበረታታችሁ ለእግዚአብሔር ደስታ ነው አለ፡፡ ከህዝቡም የተወሰኑ ሌሎች ሰዎች ስራ እየሰሩ የምሥጋና መዝሙር ያቀርቡ ነበር፡፡ (ነህ.8÷10፤ ነህ.12÷8፤ ቁ. 27,31,38) የኢየሩሳሌም ቅጥር ተጠግኖ ባለቀ በመጨረሻ ቀን የኢየሩሳሌም የደስታ ድምፅ እስከ ሩቅ ድረስ ተሰማ፡፡ (ነህ፡ 12÷43)

ነህምያ የፌረንጅ ሴቶችን አስወግዶ ሰንበትን እንዲጠብቁ አደረገ፡፡ ለካህናትና ለሌዋዊያን የሚኖሩበት ቦታ ሰጠ፡፡ ከእግዚአብሔር ቃል ውጭ የሚጋቡትን ሴቶች ከለከለ፡፡

ነህምያ ስለኢየሩሳሌም ቅጥር መፍረስ ወሬ ሰምቶ እዳዘነና ስለ ጉዳዩ በእግዚአብሔር ፊት ጾም ፀሎት እንዳደረገ (ነህ፡ 1÷2-11) እኛ ደግሞ ስለ ሀገራችንና ስለ ወንድሞቻችን

በማዘንና በችግሮቻቸው ውስጥ በመግባት እነርሱን መንከባከብ ያስፈልጋል፡፡ (1ጴጥ፡ 3÷8)

ነህምያ የእግዚአብሔርን ቃል ተስፋ ለመፈጸም የጌታን ርዳታን ጠየቀ፡፡ (ነህ፡ 1÷8-11) እኛ እግዚአብሔር እንድያደርግልን የሚንጸልየው የፀሎት ርዕሶች የተኞቹ ናቸው? ነህምያ የኢየሩሳሌምን ቅጥር በሚሠራበት ጊዜ ሴራ ሲበዛ ቅጥሩም እንዳይሠራ በሚያደናቅፉት ጊዜ የእግዚአብሔርን ርዳታ በማመን በ52 ቀናት የቅጥሩን ሥራ ጨረሰ፡፡ (ነህ፡ 4-6) እኛ ደግሞ እንደ ነህምያ በእምነት በዓለቱ ላይ ቆመን የሰጥያንን ሥራ ማሸነፍ ያስፈልጋል፡፡ (1ጴጥ፡ 5÷3,9) ነህምያ ከሁሉ ሥራ በፊት እግዚአብሔርን የምፀልይ ሰውና ሁሉንም ሥራ የፈጸመ ሰው ነው፡፡ (ነህ፡ 4÷7-23)

እኛም እንደ ነህምያ አስቀድመን በመፀለይ ሥራዎቻችንን ለመፈጸም ታማኞች የምንሆን ሰዎች ልንሆን ያስፈልጋል፡፡ (ሉቃ.19÷17) ነህምያ በየስራዎቹ መካከል የእግዚአብሔርን ሕግ ከዕዝራ ጋር ያስተምር ነበር፡፡ ሰዎችም በትምህርቱ ተመስጦ በእውነተኛ ንሰሐ ገብቶ እምነታቸው አደሱ፡፡ (ነህ.8 እስከ ምዕ.10) ነህምያ የእምነት ተሐድሶ በቃሉ በኩል አደረገ፡፡ የጌታ ቃል ብቻ የመንገዳችን ብርሃን ነው፡፡ የእግዚአብሔር ቃል የመንገዱ ብርሃን እንደ ሆነ አንተ አስታውስ! (መዝ፡ 119÷105)

ምዕራፍ ሰላሳ አንድ

የራሷን አገር የወደደችው አስቴር (አስ፡ 4፥12-17)

ሐማ ይሁዳ ሰዎችን ለመግደል ካደረገው ሴራ በፊት

አስቴርን አጐቷ መርድክዮስ አስደጋት፡፡ (አስ፡ 2፥7)

አስቴር ንግሥት ሆነች፡፡ (አስ፡ 2፥8-15)

አስቴርን የባሳ ንጉሥ ሚስት አድርጐ አገባ፡፡ (አስ፡ 2፥16-18)

አስቴር ንጉሡን ለመግደል ሴራ ያደረጉትን ከለከለች፡፡ (አስ፡ 2፥20-23)

ሐማ እስራኤላውያንን ለማጥፋት ካደረገው ሴራ በኃላ

አስቴር ሐማ አይሁድን ለመግደል ሴራ ያደረገውን ሰማች፡፡(አስ፡ 4፥4-8)

አስቴር ለአይሁድ እኔ ወደ ንጉሡ ጣልቃ እገባለው ብላ ቃል ኪዳን ሰጠች፡፡ (አስ.4፥15-17)

አስቴር ሦስት ቀን ጾም ፀሎት አደረገች፡፡ (አስ፡ 4፥15-17)

አስቴር ወደ ንጉሥ አዳራሽ ገባች፡፡ (አስ፡ 5፥1-3)

አስቴር ንጉሡን ለግብዣ ጠራች፡፡ (አስ፡ 5፥4)

አስቴር ለንጉሡ ሁለት ጊዜ ግብዣ አደረገች፡፡ (አስ፡ 5፥5- ምዕ.7፥2)

አስቴር የሐማን ሴራ ገለጸች፡፡ (አስ፡ 7፥3-7)

አስቴር ለመርድክዮስ የሐማን ቤት አወረሰች፡፡ (አስ፡ 8፥1-3)

አስቴር ሐማ በአይሁድ ላይ ያሤራውን ሤራ ለንጉሱ ነገረች፡፡ (አስ፡ 8፥4-6)

አስቴር አይሁዶች ጠላቶቻቸውን እንዲበቀሉ ከንጉሡ ዘንድ ፈቃድ ተቀበለች፡፡ (አስ፡ 8፥9-9፥16)

አስቴር አይሁዶች ጠላቶቻቸውን ካሸነፉ በኋላ አደር በሚባለው ወር አርፈው ታላቅ ግብዣና የደስታ ቀን እንዲያደርጉ አደረገች፡፡ (አስ፡ 9፥17-32)

በመጨረሻ በባቢሎን ታሥረው የሚኖሩት ነገር ግን ወደ ኢየሩሳሌም ሳይመለሱ በባሳ (ፈሪሳዊያን) ዘንድ የቀሩትን አይሁዶችን የባቢሎን ንጉስ በታላቅ አስጨንቋቸው

ነበር፡፡ በዚህን ጊዜ የገለጸችው አስቴር ናት፡፡ አስቴር የቢንያም ነገድ ስትሆን አባቷና እናቷ ከሞቱ በኋላ የአጐቷ የመርድክዮስ ሴት ልጅ ሆነች፡፡ (አስ፡ 2÷7)

ንጉሡ አርጤክስስ የወይን ጠጅ ጠጥቶ ደስ ብሎት የንግሥቲቱ ውበት ለአህዛብ አለቆች እንዲታይ ንግሥት አሲጢንን ቢያስጠራት ንግሥቲቱ ግን እምቢ አለች፡፡ (አስ፡ 1÷16-22) ንጉሡም በንግሥቲቱ በአሰጢን ላይ ስለተቆጣ ከንግሥትናዋ አንድትወርድ አደረገ፡፡ በዚህ ጊዜ ለንጉሡ የሚሆን አዲስ ሚስት ተፈለገ፡፡ በምርጫው አሸናፊ ሆና የተገኘች አስቴር ስለነበር የንጉሥ ሚስት ሆነች፡፡ (አስ፡ 2÷16-18) አስቴር የንጉሥ ሚስት ከሆነች በኋላ አጐቷ መርድክዮስ የባሳ ንጉሥ ከፍተኛ ባለሥልጣን ሆነ፡፡ (አስ፡ 2÷19)

ሐማ ጠቅላይ ሚንስተር በሆነ ጊዜ መርድክዮስ ለሐማ ስላልሰገደ ሐማ አውቆ በሁሉ አገሮች ላይ ያሉትን አይሁዶችን ለማጥፋት ሤራ አደረገ፡፡ አስቴር ሐማ ያሤረውን ሤራ ሰምታ የራሱዋን አገር ከሞት ለማትረፍ ወስና ፆም ጸሎት እንዲያደርጉ ለሕዝቧ በመንገር እሱዋም ፆም ፀሎት አደረገች፡፡ (አስ፡ 4÷4-8,16)

ከፆም ፀሎት በኋላ ወደ ንጉሥ ፊት ገብታ ሐማ ከሁለት ሰዎች ጋር በንጉሡ ላይ ያሤረውን ሤራ ከመርድክዮስ ሰምታ ለንጉሡ ተናገረችው፡፡ (አስ፡ 6÷1-3) ንጉሡም ለመርድክዮስ የተደረገለት ነገር ምንም እንደሌለበት ከተረዳ በኋላ ሐማን ንጉሥ ለሚወደው ሰው ምን ይደረግለት ብሎ ጠየቀ ምላሹንም ከሐማ ሰምቶ ያንኑ የተናገርከውን ፈጥነህ ለመርድክዮስ አድርግ አለው፡፡ ሐማ መርድክዮስን ለመግደል በራሱ ቤት ጉድጓድ ያስቆፈረውን ንጉሱ ሰምቶ ሐማ እዚያው እንዲሰቀል ትዕዛዝ አስተላለፈ፡፡ (አስ፡ 7÷9-10)

አስቴር እርሷን ያሳደገውን መርድክዮስን ታዝዛ ስለአገርዋ ሰዎች ፍቅርና ታማኝነት አደረገች፡፡ (አስ፡ 2÷20፤ 4÷10-17) እኛ ደግሞ በመልካም ጊዜና በክፉ ጊዜ እግዚአብሔርን ሁልጊዜ መታዘዝና መውደድ ያስፈልጋል፡፡ አስቴር የአይሁድን ሕዝብ ለማዳን ታላቅ ሥራ ይዛ ወደ ንጉሡ ፊት ከመግባት በፊት ፆም ፀሎት አደረገች፡፡ (አስ፡ 4÷15-16) እኛ ደግሞ ታላቅ ችግሮች በሚመጡበት ጊዜ አስቀድመን እንደ አስቴር በፆም ፀሎት ልንጠይቅ ያስፈልጋል፡፡ (ምሳሌ፡ 16÷1-3)

አስቴር የራሷን ሕዝብ ለመግደል ሤራ በተደረገበት ጊዜ ለሕይወታቸው እንዲቆሙ ያደረገች ጀግና ሴት ናት፡፡ (አስ፡ 8÷9-14) በሰዶም ከተማ ውስጥ አሥር ጻድቃን ቢኖሩ እግዚአብሔር የሰዶም ከተማ አላጠፋም አለ፡፡ እግዚአብሔር ዛሬም በእምነት ያሉትን አሥር ጻድቃን ሰዎችን ከእኛ መካከል ይፈልጋል፡፡ (ዘፍ፡ 18÷32)

አስቴር ለአገሩዋ ፆምና ፀሎት አስያዘች ዛሬ እኛ ደግሞ ስለአገራችን በእንባ ልንፀልይ ያስፈልጋል፡፡ አስቴር የንጉስ ሚስት ሆና ሀብትና ስልጣን ይዛ የራሷን ክብር ሳትፈልግ

አይሁዶችን ለመታደግ ህይወቷን አሳልፋ ሰጠች፡፡ በዚህም ምክንያት ስለ ሀገV ያላትን ፍቅር ገለፀች፡፡ (አስ.4፥15- ምዕ.5፥4) **እኛ ደግሞ የራሳችንን ክብርና ደስታ ሳንፈልግ ጎረቤቶቻችንና ሀገራችንን ልንወድ ያስፈልጋል፡፡**

ምዕራፍ ሰላሳ ሁለት

የመከራ ሰው ኢዮብ (ኢዮ፡ 42፥1-6)

ፈተናን ከመቀበል በፊት

ለኢዮብ 10 **ልጆች አሉ፡፡** (**ኢዮ፡** 1፥2,3)

ኢዮብ በምሥራቅ ካሉ ሰዎች ይልቅ ባለጠጋ ሰው ነው፡፡ (**ኢዮ፡** 1፥1,2)

ከፈተና በኃላ

እግዚአብሔር ኢዮብን ለሰይጣን ፈቅዶ ስለሰጠ ሰይጣን ኢዮብን ፈተነው፡፡ (**ኢዮ፡** 1፥11,12)

በመጀመሪያ ሰይጥያን ኢዮብን የፈተነው በንብረትና በልጆች ሞት ነው፡፡ (**ኢዮ**.1፥13-19)

በሁለተኛ ጊዜ ሰይጥያን ኢዮብን የፈተነው በሥጋው ላይ ሕመም በማምጣት ነው (**ኢዮ፡** 2፥7,8)

ሰይጥያን በሚስቱ በኩል ኢዮብን ፈተነው፡፡ (**ኢዩ፡** 2፥9)

በወዳጆች በኩል የደረሰ ፈተና፡፡ (**ኢዮ**.**ምዕ**.4 **እስከ ምዕ**.35)

ኢዮብ እስከ መጨረሻ ድረስ እምነትን ጠበቀ፡፡ (**ኢዮ፡** 23፥10)

የኢዮብ ንሰሐ መግባት፡፡ (**ኢዮ፡** 42፥6)

ኢዮብ ከመከራ በፊት ከነበረው ሁለት እጥፍ በረከት ተቀበለ፡፡ (**ኢዮ፡** 42፥10-17)

ኢዮብ ፍፁምና ቅን እግዚአብሔርን የሚፈራ ከክፉ ነገር የራቀ ሰው ነው፡፡ (**ኢዮ፡** 1፥1) **እግዚአብሔር ስለ እርሱ ያመሰገነ ሰው ነው፡፡** (**ኢዮ፡**1፥8) **“እግዚአብሔርም ሰይጣንን በውኑ ባሪያዬን ኢዮብን ተመለከትከውን? በምድር ላይ እንደ እርሱ ፍጹምና ቅን እግዚአብሔርንም የሚፈራ ከክፋትም የራቀ ሰው የለም” አለው፡፡ ኢዮብ ከሞት በኋላ ስለሌላው ሕይወትና ትንሣኤ የሚያምን ሰው ነው፡፡** (**ኢዮ፡** 19፥26)

እግዚአብሔር ኢዮብን ለሰይጣን አሳልፎ ስለ ሰጠ በመከራው የተፈተነ ሰው ነው፡፡ (**ኢዮ**.1፥9) **የኢዮብን ንብረቶቹን፣ ሀብቱን ሌሎች ሰዎች ማርከው ወሰዱ፡፡ ደግሞ** 7 **ወንድ ልጆችና** 3 **ሴት ልጆቹም ወዲያውኑ በአውሎ ንፋስ አደጋ ሞቱ፡፡ ሰውነቱም ከእግር እስከ ራስ ድረስ እጅግ ስለታመመ ለማከክ አቅም አጥቶ በገል የሚያክክ ሰው**

ሆነ፡፡ (ኢዮ.1÷13-15,19) የኢዮብ ሚስት ኢዮብን እግዚአብሔርን ሰድበህ ሙት ብላ ጠላች፡፡

የኢዮብ ወዳጆቹም ኢዮብን አንተ በኃጢአት ምክንያት በእግዚአብሔር ላይ ክፉ ነገር ስላደረክ ነው ይህ ሁሉ የደረሰው ብሎ ወቀሱት፡፡ ኢዮብ የመጀመሪያ መከራ ሲመጣ እግዚአብሔርን እንዲህ በማለት አመሰገነ፡፡ “ራቁቴን ከእናቴ ማህፀን ወጥቻለሁ ራቁቴንም ወደዚያ እመለሳለሁ እግዚአብሔር ሰጠ እግዚአብሔርም ነሣ የእግዚአብሔር ስም የተባረከ ይሁን” (ኢዮ፡ 1÷21) ሚስቱም በምትጠላት ጊዜ እርሱ ግን ከአፉ ክፉ ቃል አላወጣም ነገር ግን ስለሚስቱም “አንቺ ከሰነፎች ሴቶች እንደ አንዲቱ ተናገረሽ ከእግዚአብሔር እጅ መልካሙን ተቀብለን ክፉ ነገርንስ አንቀበልምን? ያለው ሰው ነው፡፡ (ኢዮ፡ 2÷10)

ኢዮብ ሦስቱ ወዳጆቹ መጥተው በተናገሩአቸው ነገር የተነሣ የተወለደበትን ቀን ረገማት፡፡ (ኢዮ፡ 3÷1) ኢዮብ የእግዚአብሔር ጥበቃ ፀጋና ሥልጣንን ተስማምቶ የሚኖርና በትዕግሥት ልብ የሚታዘዝ ሰው ነው፡፡ ስለዚህ ቃል ሐዋሪያው ያዕቆብ ሲናገር “እነሆ በትዕግሥት የጸኑትን ብፁዓን እንላቸዋለን ኢዮብ እንደታገሠ ሰምታችኋል ጌታም እንደፈጸመለት አይታችኋል፡፡ ጌታ እጅግ የሚምር የሚራራም ነውና”አለ፡፡ (ያዕ፡ 5÷11)

ኢዮብ አዲስ የመንፈሳዊ ዐይኖች ተከፍቶ ንሰሐ ከገባ በኃላ ከሰይጣን እሥራት ተፈትቶ (ኢዮ፡ 42÷5) ከመጀመሪያው ሁለት እጥፍ በረከትን ተቀበለ፡፡በሕይወት እያለን መከራና ችግር የማይደርስ ሰው የለም፡፡ ስለዚህ ለእኛ መፍትሔ የሚሆን የችግሮች መጥፋት አይደለም፡፡ እኛ አሁን ችግሮች ሲመጡ ወዴት ነው የምንሄደው? ኢዮብ ታላቅ መከራ ሲደርስ ፍፁም እምነቱን ሳያጠፋ በትዕግስት መከራን አሸነፈ፡፡ (ኢዮ፡ 42÷5)

እኛ እንደ ኢዮብ በመከራና በችግሮች እምነታችንን ሳናጠፋ በትዕግስት በመጠበቅ ሁለት እጥፍ በረከትን ልንቀበል ያስፈልጋል፡፡

ምዕራፍ ሰላሳ ሶስት

ታላቁ ነቢይ ኢሳይያስ (ኢሳ፡ 6፥8-13)

እግዚአብሔር ከመጥራቱ በፊት

ኢሳይያስ ለነቢይነት የተጠራ ሰው ነው፡፡ (ኢሳ፡ 6፥1)

ከጥሪ በኃላ

ኢሳይያስ የአሦርን ንጉሥ የረአሶንን ሀሳብ ተቃወመ፡፡ (ኢሳ፡ 7፥1-25)

ኢሳይያስ የይሁዳንና የእስራኤል መደምሰስ አስቀድሞ ተነበየ፡፡ (ኢሳ፡ 7፥1-25)

ኢሳይያስ ሰለመሲሑ መምጣት (መወለድ) ተነበየ፡፡ (ኢሳ፡ 7፥14፤ 11፥1-10)

ኢሳይያስ ሰለሌሎች አገሮች መደምሰስ ተነበየ፡፡ (ኢሳ፡ 13፥1-23፥18)

ኢሳይያስ ለሦስት ዓመት ራቆት ሆኖ በባዶ እግር የኖረ ሰው ነው፡፡ (ኢሳ፡ 20፥1-6)

ኢሳይያስ ለንጉሡ ሕዝቅያስ ከግብፅ ጋር ህብረትን አታደርግ ብሎ ተናገረ፡፡ (ኢሳ. 30 እስከ ምዕ.31)

ኢሳይያስ በባቢሎን ወህኒ ቤት ለሚኖሩት ደህንነትን ተነበየ፡፡ (ኢሳ. ምዕ.39)

ኢሳይያስ ለአማኞች የሚሰጠውን የወደፊቱን በረከትና ክብር ተነበየ፡፡ (ኢሳ፡ 55፥6-9)

ኢሳይያስ ማለት እግዚአብሔር ያድናል ማለት ነው፡፡ ኢሳይያስ ሆሳዕ ንጉሥ ዮራም፣ ንጉሥ አካዝ፣ ንጉሥ ሕዝቅያስ፣ በሚኖሩበት ጊዜ የሚተነብይ ነቢይ ነው፡፡ ኢሳይያስ ከንጉሣዊ ቤተሰብ የአሞጽ ልጅና በኢየሩሳሌም የምኖር ሰው ነው፡፡ እርሱ የእግዚአብሔርን ጥሪ የተቀበለው የአሦር ንጉሥ ይሁዳን በሚዋጋበት ጊዜ የይሁዳ ንጉሥ ዖዝያን በሞተበት ጊዜ ነው፡፡ (ኢሳ፡ 6፥1)

የንጉሡ የዖዝያን ዘመን የማህበራዊ ቀውስ ያጋጠመበትና የተበላሸበት ዘመን ነው፡፡ በዚህን ጊዜ ለእግዚአብሔር የሚሰጠው የአምልኮ ዕቃዎችና ስግደቶች እግዚአብሔር እንደማይቀበል ኢሳይያስ የተናገረበት ዘመን ነው፡፡ እምነታቸውን እንድያስተካክሉ ተነበየ፡፡ (ኢሳ፡ 1፥10-17) **እግዚአብሔር ለኢሳያስ እንዲህ አለ፡፡ ‘በሬ የገዥውን**

አህያም የጌታውን ጋጣ አወቀ እስራኤል ግን እኔን አላወቀም’ ሕዝቤም አላስተዋለም ብሎ ተናገረ፡፡ (ኢሳ፡ 1÷2-3) ይህ ማለት እግዚአብሔር የእስራኤል ልጆችን አሳደገ፡፡ ነገር ግን የእስራኤል ሕዝብ እግዚአብሔርን እምቢ አሉ ማለት ነው፡፡

እግዚአብሔር ለኢሳይያስ የተናገረው የእስራኤል ከተማ እንደምትደመሰስና በውስጡዋ የሚኖሩ ሰዎች እንደሚጠፉ በእርሻ ውስጥ ሰብል እስከሚጠፉ ድረስ የሰዎች ልብ እንዳያስተውል ጆሮአቸው እንዳይሰማ በዓይናቸው እንዳያዩ አደንድን ብሎ ተናገረ፡፡ (ኢሳ፡ 6÷9-12) ነቢዩ ኢሳይያስ የእስራኤል አገር በሁከት ጊዜ በቤተመቅደስ በሚፀልይበት ጊዜ የእግዚአብሔርን ክብር ቤተመቅደስ ሲሞላ አየ፡፡ ኢሳይያስ በቅዱስ እግዚአብሔር ፊት ራሱ ኃጢአተኛ መሆኑን አውቆ ንሰሐ ሲገባ እግዚአብሔር በጉጠት የወሰደውን ፍም ከንፈሩን ዳሰሶ አነጻ፡፡ (ኢሳ፡ 6÷6-9)

የሰሜኑ እስራኤልና የደቡባዊ ይሁዳ በመከራቸው ጊዜ የግብፅን እርዳታ ሲጠየቁ ኢሳይያስ እግዚአብሔርን ብቻ በመተማመን እንድያደርጉ ተናገራቸው፡፡ ኢሳይያስ የማያምኑ የእስራኤል ሰዎችና የይሁዳ ሰዎች እግዚአብሔርንም የማያገለግሉ እንደሚጠፉ ተናገረ፡፡ (ኢሳ፡ 31÷1-3)

ንጉሥ ሕዝቅያስ በ14 ዓመት የአሦር የራፋስቂስ ኢየሩሳሌምን ለመውጋት በሚመጣበት ጊዜ ኢሳይያስ ለንጉሡ ሕዝቅያስ የተናገረው ቃል “የአሦር ንጉሥ ባሪያዎች ስለሰደቡኝ ስለሰማኸው ቃል አትፍራ እነሆ በላዩ መንፈስን እሰድዳለሁ ወሬንም ይሰማል ወደ ምድሩም ይመለሳል በምድሩም በሰይፍ እንዲወድቅ አደርጋለሁ” ብሎ የእግዚአብሔርን ሀሳብ ተናገረ፡፡ (ኢሳ፡ 37÷5-7)

ኢሳይያስ ራዕይ ያለው ሰውና የወደፊቱንም አይቶ የሚናገር ሰው ነው፡፡ (1ኛ ሳሙ. 9÷9) የእስራኤል ሃይማኖትና የፓለቲካ ሁኔታ ተበላሽቶ በነበረበት በዚያን ጊዜ ኢሳይያስ አሁን ጨለማ ሸፍነዋል ነገር ግን ወደፊት ብርሃን ይሆናል በማለት ተናገረ፡፡ ስለዚህ እናንተ ሕዝቤን አጽናኑ ለኢየሩሳሌም ልብ ተናገሩ የተቀጠረችበት ወራት እንደተፈጸመ ኃጢአትዋም እንደ ተሰረየ ከእግዚአብሔርም እጅ ስለኃጢአትዋ ሁሉ ሁለት እጥፍ እንደተቀበለች ወደ እርስዋ ጩኹ በማለት ተንብየዋል፡፡ (ኢስ፡ 40÷1-2)

ኢሳይያስ በቤተ መቅደስ ውስጥ በሚያመልክበት ጊዜ የነቢይነትን ጥሪ ተቀበለ፡፡ (ኢሳ፡ 6÷1) እርሱ ወዲያወኑ ለእግዚአብሔር ጥሪ ታዘዘ፡፡ (ኢስ፡ 6÷9-13) ዛሬ እኛ ደግሞ እንደ ኢሳይያስ እግዚአብሔርን ልንታዘዝ ያስፈልጋል፡፡ እርሱ እስራኤላዊያን በእግዚአብሔር ፊት ኃጢአት ማድረጋቸውን አይተው በሐዘን ልብና በፍቅር ቀርበው ስህተታቸውን አስጠነቀቀ፡፡ (ኢሳ፡ 1÷2-31፤ 2÷5-11)

ኢሳይያስ ወደፊት የሚመጣውን ደህንነት ተናገራቸው፡፡ (ኢሳ፡ 40÷1-31) **እንደዚሁም እኛ ማህበራዊ ኃጢአቶችን በመወቀስና ንሰሐ እንዲገቡና ተስፋ እንዳላቸው ለሕዝቡ ማሳወቅ ያስፈልጋል፡፡**

ኢሳይያስ ለእግዚአብሔር ጥሪ ወዲያውኑ በመታዘዝ "እነሆኝ እኔን ላከኝ" ብሎ የመለሰ ሰው ነው፡፡ (ኢሳ፡ 6÷8) **ኢሳይያስ ወደፊት ስለሚመጣ መሲሕ ተስፋ ይዞ "መሲሑ ይመጣል ታገሱ" በማለት ስለመሲሑ ሕይወት ይበልጥ የተነበየ ሰው ነው፡፡ እኛ ደግሞ የኢየሱስ የመመለስ ተስፋና ትንሣኤውን በልብ ይዘን እንደ ብልህ አምስት ልጃገረዶች ተዘጋጅተን ልንኖር ያስፈልጋል፡፡** (ማቴ፡ 25÷1-13)

ምዕራፍ ሰላሳ አራት

የዕንባ ነቢይ ኤርምያስ (ኤር፡ 1፥4-10)

ንጉሥ ኢዮስያስ በሚመራበት ጊዜ

ኤርምያስ የነቢይነትን ጥሪ የተቀበለ ሰው ነው፡፡ (**ኤር፡** 1፥4,5)

ኤርምያስ ከንጉሥ ኢዮስያስ ጋር የሃይማሃት ተሐድሶ ያደረገ ሰው ነው፡፡ (**ኤር፡** 11፥1-8)

ንጉሥ ኢዮአቄም በሚመራበት ጊዜ

ኤርምያስ ንጉሡ ኢዮአቄም ክፋ ስላደረገ ወቀሰ፡፡ (**ኤር፡** 22፥18,19)

ኤርምያስ የኢየሩሳሌምን መደምሰስ ተነበየ፡፡ (**ኤር፡** 25፥1-38)

ንጉሥ ሰደቂያስ በሚመራበት ጊዜ

ኤርምያስ የኢየሩሳሌም (የይሁዳ) ንጉሥ ወደ ባቢሎን ፍጹም እንደሚማረኩ ተነበየ፡፡ (**ኤር፡** 38፥14,17,18)

ኤርምያስ የኢየሩሳሌም (ይሁዳ ሰዎች) ወደ ባቢሎን እንደሚማረኩና ከባቢሎን እንደሚመለሱ ተነበየ፡፡ (**ኤር፡** 32፥1-44)

ኤርምያስ አሳልፈው ወደ ወህኒ ቤት አስገቡ፡፡ (**ኤር፡** 37፥4-15)

ኤርምያስ በምድር ወህኒ ቤት አካባቢ ይኖራል፡፡ (**ኤር፡** 37፥16-21)

ኤርምያስን በጭቃ ጉድጉድ ውስጥ ጣሉ፡፡ (**ኤር፡** 38፥1-6)

ኤርምያስ በአቤሜሌክ ርዳታ ከጉድጓድ ወጣ፡፡ (**ኤር፡** 38፥7-13)

ኤርምያስ ኢየሩሳሌም እስከምትደመሰስ ድረስ፣ንጉሡ ሴደቅያስ እስከ ሚነግስና አይሁዶች ተማርከው እስከ ባቢሎን እስከሚሄዱ ድረስ ቆየ፡፡ (**ኤር፡** 52፥4-34)

ኤርምያስ በውጊያ ጊዜ እንደማይሞት ጥንቃቄ ተደረገላት፡፡ (**ኤር፡** 39፥11-14)

ኤርምያስ ከካህኑ ከኤልቅያስ የተወለደ ሲሆን ዕድሜውም 20 **ዓመት ያህል ሲሆን ለነቢይነት አገልግሎት ተጠራ፡፡ ኤርምያስ ንጉሥ ሕዝቅያስ ከሞተ በኋላ ንጉሥ ምናሴ ነግሶ ክፋ ፖለቲካ ሲያራምድ ከንጉሥ ኢዮስያስ ጋር ተሐድሶ አደረገ፡፡ ነገር ግን**

የእስራኤል ሰዎች ብርሃንን ሳያዩ ክፉ መሪ የጨለማ ፖለቲካ እንድቀጥል አደረጉ፡፡ እግዚአብሔርም ስለክፋታቸው አይቶ እንዲህ አለ “ ነቢዩና ካህኑም ረክሰዋልና በቤቴም ውስጥ ክፋታቸውን አግኝቻለሁ” አለ፡፡ (ኤር፡ 23÷11)

በተጨማሪም እግዚአብሔር የተናገረው የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል “ትንቢት የሚናገሩላችሁን የነቢያትን ቃል አትስሙ ከንቱነትን ያስተምሩአችኋል፡፡ ከእግዚአብሔር አፍ ሳይሆን ከገዛ ልባቸው የወጣውን ራዕይ ይናገራሉ” በማለት ሕዝቡን ያሳስባቸዋል፡፡ (ኤር፡ 23÷16)

ኤርምያስ ወደፊት ይሁዳ እንዳትጠፋ ምክንያቱ ለባቢሎን እጅ መስጠት እንዳለበት ስለተነበየ የይሁዳ ሰዎች ኤርምያስን ከሃዲ አድርጐ ተናገሩ፡፡ የይሁዳ መሪዎችና የአገሩ ሕዝብ ኤርምያስን ለመግደል አስጠርቶ አስፈራሩት፡፡ ወዳጆቹ ደግሞ ኤርምያስን ከሕዝቡ ወስደው ወደ ወህኒ ቤት አስገቡት፡፡ ከኤርምያስ ጋር የሚሰራ ሰው ማንም አልነበረም፡፡ ሚስት ያለው ሰው ቢሆን ይጽናና ነበር፡፡ ነገር ግን አስቀድሞ እግዚአብሔር ለኤርምያስ “አንተ ሚስት አታግባ ልጆቹንም አትውለድ” ብሎ ተናግሮ ነበረና፡፡ (ኤር፡ 16÷2-6)

እግዚአብሔር የኤርሚያስ ራዕይ እንደ ብረት ጠንካራ ሆኖ እንዲፈፅም ፈልጎ ይሄንን መልዕክት ለኤርሚያስ ተናግሯል፡፡ (ኤር.1÷15 ምዕ.15÷20) **አስቀድሞ እግዚአብሔር ለኤርምያስ የራሱን ቃል ስለተናገረ ኤርምያስ ተደስቷል፡፡** (ኤር፡ 15÷16) **ይሁን እንጂ ቃሉን ከሰማ በኋላ በኤርምያስ ላይ መከራና ሥቃይ መጣ፡፡** (ኤር፡ 15÷17) **ኤርምያስ ከዚህ ቃል የተነሣ የእግዚአብሔርን ቃል ለመተው ፈለገ፡፡ ነገር ግን የእግዚአብሔር ቃል በኤርምያስ ውስጥ እንደ እሳት ተቀጣጠለ፡፡** (ኤር፡ 20÷9) **የይሁዳ ሕዝብ ኤርምያስን ብዙም ወደዱት፡፡**

ነገር ግን እግዚአብሔር ለኤርምያስ የሚናገረው መልዕክት ሁል ጊዜ የፍርድና የእርግማኔ ቃል ስለሆነ ህዝቡም በኤርምያስ ላይ ቁጣ አነሱ፡፡ ስለዚህ ኤርምያስ የተወለደበትን ቀን ረገመ እግዚአብሔርም ቃሉን እንዳይሰጥ ፈለገ::

እግዚአብሔር ኤርምያስ ስለተናገረው ነገር ንሰሐ እንዲገባ ተናገረ፡፡ ስለተነጫነጨም ወቀሰ፡፡ ኤርምያስ የወቀሳውን ቃል ሰምቶ በእግዚአብሔር ፊት ንሰሐ ገባ፡፡ (ኤር.15÷19)

እግዚአብሔር ደካማና ስልጣን የሌላቸውን ሰዎችን መርጦ የራሱን ሥራ እንዲሰሩ ስልጣንና ሀይልን ይሰጣል፡፡ (1ኛ.ቆሮ.1÷27-29) **እኛም በስጦታችንና በገንዘባችን ሳንመካ ከላይ የሚወርደውን የእግዚአብሔርን ስጦታ ልንፈልግ ያስፈልጋል፡፡**

ኤርምያስ ወደ ባብሎን በባርነት ተማርኮ እንደሚሄድና ብዙ ችግሮች እንደሚደርስባቸው እንደተነበየ የእግዚአብሔርን ሥራ ለሚፈልጉት እግዚአብሔር እንደፈቃዱ ይሰራል፡፡ (ኤር.18÷6) **እኛም ሰዎች ቢሰሙንም ባይሰሙንም**

እግዚአብሔር በውስጣችን ያስቀመጠውን የእግዚአብሔርን መልዕክት የእግዚአብሔር ሀሳብ ለሚተው ሰዎች በድፍረት ልንናገር ያስፈልጋል፡፡

ምዕራፍ ሰላሳ አምስት

ባለ ራዕይ ነቢይ ሕዝቅኤል(ሕዝ፡ 1፥1-3)

የእስራኤል ህዝብ ወደ ባብሎን ተማርኮ በሄዱ ጊዜ

ሕዝቅኤል በባቢሎን ተማርኮ ከተወሰዱት ወገኖች ጋር በኮቦር ወንዝ አጠገብ የሚኖር ሰው ነው፡፡ (ሕዝ፡ 1፥1 ምዕ.3፥15-17)

ኤርሚያስ ወደ ባብሎን ተማርኮ ከሄደ ከ5 አመት ቆይታ በኃላ ጥሪውን ተቀበለ፡፡ (ሕዝ.1፥1-3)

ሕዝቅኤል የመላአኩን ራዕይ አየ፡፡ (ሕዝ.1፥4-28)

ባቢሎን ሁለት ጊዜ የይሁዳ ሰዎች ሲዋጉ ከእነርሱ ጋር ተዋጋ፡፡ (ሕዝ፡ 3፥5-17)

ኢየሩሳሌም እንደምትከበብ ተነበየ (ሕዝ.4፥1፤ 24፥27)

ሕዝቅኤል የከብቶችን ኩበት በእንጨት ፋንታ በእሳት አቀጣጥሎ ምግብ አዘጋጅቶ በላ፡፡ (ሕዝ.4፥4-17)

ሕዝቅኤል የእስራኤልን መዳን ተነበየ፡፡ (ሕዝ፡ 33፥1፤ 48፥35)

ሕዝቅኤል ከሕዝቡ ስደት ደረሰ፡፡ (ሕዝ፡ 3፥25)

ሕዝቅኤል በኢየሩሳሌም ስዕል ቤት [ባዕድ አምልኮ] የሚያደርጉትን ክፉ ነገር አየ፡፡ (ሕዝ፡ 8 እስከ ምዕ.11)

ሕዝቅኤል የወይን ግንድ በእሳት ሲቃጠል አየ፡፡ (ሕዝ፡ 15፥1)

የሕዝቅኤል ሚስት መሞት፡፡ (ሕዝ፡ 24፥16-19)

ሕዝቅኤል ለሌሎች አገሮች ላይ ስለምመጣው ፍርድ ተነበየ፡፡ (ሕዝ፡ 25፥1-32፥32)

ሕዝቅኤል የደረቁ አጥንቶች ራዕይ አየ፡፡ (ሕዝ፡ 37)

ሕዝቅኤል ለ13 ዓመታት ትንቢትን ተንብዮ አቆመ፡፡ (ሕዝ፡ 32፥17፤ 40፥1)

ሕዝቅኤል የሕይወት ውሃ ራዕይ አየ፡፡ (ሕዝ፡ 47)

ሕዝቅኤል የካህኑ ቡዝ ልጅ ነው፡፡ (ሕዝ፡ 1÷3) እርሱ ዮአኪን ወደ ባቢሎን ተማርኮ በተወሰደ ጊዜ አብሮ የተማረከና (ሕዝ፡1÷1) የእግዚአብሔርንም ራዕይ በመንኰራኩር ላይ ተቀምጦ ወደ ሁሉ ቦታ ማንም ሳይከለከል እንደሚሄድ የተመለከተ ሰው ነው፡፡ (ሕዝ፡ 1÷15-25)

የዚህን ትርጉም ሕዝቅኤል እግዚአብሔር በሁሉም ቦታ የሚኖር አምላክ መሆኑን በግልጽ አወቀ፡፡ ሕዝቅኤል የእግዚአብሔርን ቃል አፋን ከፍቶ ሲመገብ እንደ ማር መጣፈጡን ተረዳ፡፡ (ሕዝ፡ 2÷8-3፤ 1÷3) ሕዝቅኤል በመጀመሪያ የእግዚብሔርን ቃል ለመስበክ ተጠራጥሮ ነበር፡፡ ነገር ግን ከኋላ በጣም ደስተኛ ሆነ፡፡

የሕዝቅኤል ጥሪ ሕዝቡ ቢሰሙም ባይሰሙም ለእነርሱ ትንቢት መናገር ነው እንጂ ይህ አለመስማታቸው ወሳኝ ችግር አይደለም፡፡ ትንቢቱን በሰዎች መካከል ሆኖ ስለሚናገር ነው፡፡ (ሕዝ፡ 3÷16-21፤ 33÷32-33)

በዚያን ጊዜ የነበሩት ሰዎች የአያቶቻቸው ኃጢአት ሕዝቡን ሲያጠፋ ግዴታ የሌሉ ሰዎች ናቸው፡፡ ሕዝቅኤል የቅድመ አያቶቹ ኃጢአት ግዴታ ያለውና መዳን እንዳለባቸው የሚያስብ ሰው ነው፡፡ የራሱን ጽድቅ ሳያስብ በኃጢአቶኞች መካከል ስለኃጢአታቸው እየተናገረ የሚሞት ሰው ነው፡፡ (ሕዝ፡ 33÷10-16)

ሕዝቅኤል የእግዚአብሔርን ፈቃድ የሚናገርና ታላቅ ተስፋ ይዞ የእስራኤልን የወደፊት ሁናቴ የተመለከተ ሰው ነው፡፡ ምክንያቱም የእግዚአብሔር መንፈስ ከሞት በኋላ ሕይወት የሚሰጥ አምላክ መሆኑን የሚያምንና ማዳን የምችል በምድርም መኖሩን የሚያምን ነው፡፡ ሕዝቅኤል በቤተመቅደስ ፊት ለፊት ውሃን ሲፈስስ ያየው ራዕይ በሚሄድበት ቦታ እንስሳትና እጽዋት እንደሚያድጉ ለእስራኤልን ትንሣኤ እንደሚኖር ማሳየቱ ነው፡፡ (ሕዝ፡ 47÷1-12)

ሕዝቅኤል አገሩ በሚደመሰስበት ጊዜ የመዳኑ ተስፋን አላጠፋም ምክንያቱም በዓለም ላይ የሚሠራውን ሥራ የምቆጣጠረው እግዚአብሔር መሆኑን ያውቃልና፡፡ (ሕዝ፡ 33÷1፤48÷35)

እኛ ደግሞ እንደ ሕዝቅኤል በመከራችን ጊዜ የእግዚአብሔርን ሥልጣንና ተስፋ መያዝ ያስፈልጋል፡፡ ሕዝቅኤል የእግዚአብሔርን ቃል ለሚሰሙትም ለማይሰሙትም ሁሉ ተነበየ፡፡ (ሕዝ፡ 4÷1-3፤ 5÷1-4፤ 12÷3-5፤ 21÷3,6) ደግሞም ለይሁዳ ሕዝብ የተስፋ ቃል ሰጠ፡፡ (ሕዝ፡ 33÷1-39÷29) እኛ ደግሞ በዓለም ላይ ላሉት ሰዎች የመዳን ተስፋ የምሥራቹን ዜና (ወንጌል) መስከር ያስፈልጋል፡፡

ምዕራፍ ሰላሳ ስድስት

በእምነት መንገድ ብቻ የሄደው ዳንኤል (ዳን፡ 1፥8-21)

ወደ አንበሣ ጉድጓድ ከመጣል በፊት

ዳንኤል በመጀመሪያ ወደ ባቢሎን ተማርኮ የተወሰደ ሰው ነው፡፡ (ዳን፡ 1፥1)

ዳንኤል ለሦስት ዓመት ያህል በባቢሎን በቤተመንግሥት የከለዳዊያን ቋንቋ ትምህርትን ተማረ፡፡ (ዳን፡ 1፥10-21)

ዳንኤል ሁለተኛ ጊዜ የንጉሥ ናቡከደነፃር ሕልም ተረጐመ፡፡ (ዳን፡ 2፥25-45፤ 4፥19-27)

ዳንኤል በግርግዳ ላይ በእግዚአብሔር ጣት የተጻፈውን ጽህፈት ተረጐመ፡፡ (ዳን፡ 5፥1-5 ቁ. 17-28)

ዳንኤል በንጉሥ ዳርዮስ ዘመን ጠቅላይ ሚንስተር ሆነ፡፡ (ዳን፡ 6፥1,2)

በዳንኤል ላይ የባቢሎን መሪዎች ሤራ አድርገው በአንበሣ ጉድጓድ እንድጣል አደረጉ፤ እግዚአብሔር መላአኩን ልኮ የአንበሣ አፍ ስለዘጋ ዳንኤልም ከአንበሣ ጉድጓድ በሠላም ወጣ፡፡ (ዳን፡ 6፥3-27)

ከአንበሣ ጉድጓድ ከወጣ በኃላ

ዳንኤል አራት የአውሬ ራዕይ አየ፡፡ (ዳን፡ 7፥1-28)

የኮርማ በሬና የአውራ ፍየል ራዕይ አየ፡፡ (ዳን፡ 8፥1-27)

ዳንኤል የ490 ቀኖች ራዕይ አየ፡፡ (ዳን፡ 9፥20-27)

ዳንኤል በንጉሥ ቂሮስ ዘመን ታላቅ ጦርነት እንደሚሆን ያንን ራዕይ አየ፡፡ (ዳን፡ 10፥1-12፥13)

ዳንኤል የራሱን መጽሐፍ ጻፈ፡፡ (ዳን፡ 1፥1-12፥13)

ዳንኤል የይሁዳ ንጉሥ ኢዮአቄም በነገሠ በሦስተኛ ዓመት ንጉሥ ናቡካደፃር ወደ ባቢሎን በመጀመሪያ ማርኮ ከወሰደው ከይሁዳ ሰዎች ጋር የተማረከና (ዳን፡ 1፥1) **ከንጉሣዊ ቤተሰብ አንዱ ነው፡፡** (ዳን፡ 1፥1) **ንጉሥ ናቡከደነፃር ከማረካቸው ከወንዶች ልጆች ጋር ዳንኤል ለሦስት ዓመት የከለዳዊያን ቋንቋ ትምህርት ተማረ፡፡** (ዳን፡ 1፥10-21)

የባቢሎን አለቃ የዳንኤልን ስም ቀይሮ ቢልጣሶር አለ፡፡ (ዳን፡ 1÷7) **ዳንኤል አምላኩን ላለማስረከስ ፈልጐ የንጉሥ ቤት መጠጥና ምግብ እምቢ አለ፡፡ እግዚአብሔርም ለዳንኤል በጀንደረቦች አለቃ ፊት ሞገስና ምህረትን ሰጠው፡፡** (ዳን፡ 1÷9)

ዳንኤልም የሚበላው ጥራጥሬና ውሃ ብቻ ከተመገበ ከአሥር ቀን በኋላ ዳንኤልና ወዳጆች በሌሎች ወንድሞች ፊት አምሮ ተውቦ ታየ፡፡ (ዳን፡ 1÷15) **እግዚአብሔር ለዳንኤልና ለወዳጆቹ ጥበብን ሰጥቶ ሁሉንም ትምህርት እንዲያውቁ ችሎታ (እውቀት) ሰጣቸው፡፡ ዳንኤል ሁሉንም ራዕይዎችንና ሕልሞችን ተረጐመ፡፡** (ዳን፡ 1÷17) **እርሱ ከእግዚአብሔር የተቀበለው ጥበብ ከሌሎች አሥር እጥፍ በልጦ ታየ፡፡** (ዳን፡ 1÷20)

ዳንኤል በየቀኑ ሦስት ጊዜ ወደ እግዚአብሔር ይፀልያል፡፡ ሌሎች መሪዎች ዳንኤል ይህን ፀሎት ወደ አምላኩ ስለምፀልይ ይዘው ወደ አንበሣ ጉድጓድ ጣሉት፡፡ እግዚአብሔር ግን የአናቢስትን አፍ ዘግቶ ዳንኤልን አዳነ፡፡ (ዳን፡ 6÷10-20) **የዳንኤል ሦስት ጓደኞች ለወርቁ ምስል አንሰግድም ስላሉ በሚነድደው በእሳቱ እቶን ውስጥ ተጣሉ፡፡ ነገር ግን እግዚአብሔር ከሚነድደው ከእሳቱ እቶን አወጣቸው፡፡** (ዳን፡ 3÷19-30)

ዳንኤል የንጉሡ ናቡከደነፆር ሕልም ሁለት ጊዜ ተረጐመ፡፡ (ዳን፡ 2÷25-45፤ 4÷19-27) **ዳንኤል የንጉሡን ምግብ እምቢ ያለበት ምክንያት ለጣኦት የተሰዋ ምግብ ስለሆነ ለጣኦት የተሰዋውን አያስፈልግም በማለቱ ነው፡፡ ዳንኤል ለጣኦት የተሰዋውን ምግብ በመምብላት የራሱን ሥጋ ስረክሰ እግዚአብሔር ከቶ እንደማይደሰት አውቀዋል፡፡ እኛ ደግሞ እንደ ዳንኤል ልንቀደስ ያስፈልጋል፡፡ ምክንያቱም የእኛ ሥጋ ክርስቶስ በራሱ ደም ያነፃ የእግዚአብሔር ቤተመቅደስ ስለሆነን ነው፡፡** (1ኛ ቆሮ፡ 6÷19-20)

የፀሎት ሰው ዳንኤል በመሪዎች ሴራ ምንም ኃጢአት ሳይኖርበት ወደ አናብስት ጉድጓድ ተጣለ፡፡ ነገር ግን እግዚአብሔር ከዳንኤል ፀጉር አንድም ሳያስነካ በሠላም አሳደረ፡፡ (ዳን፡ 6÷16-23) **ለእኛ የመከራና የችግር ጊዜ ጥቂት ነው፡፡ ከዚያም በኋላ የዘላለም ስጦታ በሰማይና በምድር መኖሩን ልናውቅ ያስፈልጋል፡፡** (2ጢሞ፡ 2÷5፤ ያዕ፡ 1÷12)

ስለዚህ በችግሮችና በመከራዎች መካከል ያለን ክርስቲያኖች የእግዚአብሔርን ጥበቃ ተዘናግተን ከቶ እግዚአብሔርን ማሳዘን የለብንም፡፡ እንደ ዳንኤል የእግዚአብሔርን ፈቃድ በፍጹም አድርገን እስከ ፍፃሜ ድረስ ልንቀጥል ያስፈልጋል፡፡ (ፊል.1÷6)

ዳንኤል የእስራኤል ሰዎች ኃጢአት አይቶ በፆም ፀሎት ወደ እግዚአብሔር ፀለየ፡፡ (ዳን፡ 9÷1-19) **እኛ ደግሞ ለሀገራችንና ለጐረቤቶቻችን መፆም ያስፈልጋል፡፡** (ነህ፡

9∴1-3)

ምዕራፍ ሰላሳ ሰባት

የንሰሐ ጥሪ ያደረገው የፍቅር ነቢይ ሆሴዕ (ሆሰ፡ 1፥2-9)

እግዚአብሔር ከመጥራቱ በፊት

ሆሴዕ የእግዚአብሔርን ጥሪ የተቀበለ ሰው ነው፡፡ (ሆሴ፡ 1፥2)

ከጥሪ በኃላ

ሆሴዕ ስለእግዚአብሔር ጥሪ ምላሽ ጐመርን አገባ፡፡ (ሆሴ፡ 1፥3)

ሆሴዕ ሦስት ልጆችን ወለደ፡፡ (ሆሴ፡ 1፥4-9)

ሆሴዕ የሚወዳትን አመንዛሪቱን ሚስት ከዚህ በኋላ አታመንዝሪ ብሎ ነገራት፡፡ (ሆሴ፡ 3፥1-3)

ሆሴዕ ለሕዝቡ ንሰሐ ግቡ ፍርድ ይመጣል እያለ ተነበየ፡፡ (ሆሴ፡ 4፥14)

ሆሴዕ የራሱን የሆሴዕን መጽሐፍ ጻፈ፡፡ (ሆሴ፡ 1፥1፤ 14፥9)

ሆሴዕ የእግዚአብሔርን ፍቅር አውቆ ለእስራኤል ሰዎች ፍቅርና ርኅራኄ ያሳየ ሰው ነው፡፡ (ሆሴ፡ 1፥3፤ 3፥1-3) **ሆሴዕ ያባረራትን ሚስት ጐመርን ለመውሰድ እምቢ ሳይል እንደገና ሚስት አድርጎ ተቀበለ፡፡** (ሆሴ፡ 3፥1-3) **ሆሴዕ በእስራኤል ሕዝብና በእግዚአብሔር መካከል ሠላምን የሚያመጣ አስታራቂ የሆነ ሰው ነው፡፡ ይህ ማለት ስለ ኃጢአተኞች ስም የሚመጣውን ኢየሱስ ክርስቶስን ይገልጻል ማለት ነው፡፡** (ሆሴ፡ 6፥1-3)

ጐመር ኃጢአትን ያደረጉትን የእስራኤል ሕዝብንና እኛን የምትወክል ሲሆን የሆሴዕ ፍቅር የእግዚአብሔር ፍጹም ፍቅርና የኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀል ላይ ሰዎችን የወደደበትን ፍቅር የሚገልጽ ነው፡፡

ነቢዩ ሆሴዕ አመንዝራይቱን ጐመርን ሚስት አድርጐ ወሰዳት፡፡ ይህ እግዚአብሔር ኃጢአተኞች የሆነን እኛን መርጦ ልጆቹ አድርጎ መቀበሉን ያሳያል፡፡ እኛ የእግዚአብሔር ልጆች ስለሆነን እግዚአብሔርን እናመሰግናለን፡፡ (ሮሜ፡ 5፥8)

ሆሴዕ ለእስራኤል ሰዎች የንሰሐ ስብከት ለረዥም ጊዜ ተናገረ፡፡ እኛ እግዚአብሔር ለነቢያት የሰጠውን የነቢያትን ተልዕኮ ልንረዳ ያስፈልጋል፡፡ ሆሴዕ አመንዝራ የሆነችውን ጐመርን ሚስት አድርጐ መወሰድ ማለት እኛ የእግዚአብሔር ቤተሰቦች ልንፋታ እንደማንችል የሚገልጽ ነው፡፡ (ምሳሌ፡ 5፥9፤ ኤፌ፡ 5፥28,33)

እግዚአብሔር እንደ ጎመር ብዙ ኃጢያት የሰሩትን ለማዳን ታላቅ ፍቅሩን አሳየ፡፡ (ሆሴዕ.3፥1-3) እግዚአብሔር እኛ ኃጢያት ከሰራን በኃላ ንሰሃ እንድንገባ ይፈልጋል፡፡ ከንሰሃ በኃላ እግዚአብሔር ታላቅ ፍቅሩን ይሰጠናል፡፡ ሁል ጊዜ ኃጢያታችንን ሁሉ እግዚአብሔር ይቅር ስለሚለን እግዚአብሔር እናመሰግናለን፡፡

ምዕራፍ ሰላሳ ስምንት

የነኔዌን ከተማ ለማዳን የተመረጠ ነቢይ ዮናስ (ዮና፡ 2፥1-9)

ከንሰሃ ስብከት በፊት

ዮናስ የአሲሮ ከተማ ወደ ሆነው ወደ ነነዌ እንድሄድ ጥሪ ተቀበለ፡፡ (ዮና፡ 1፥1,2)

ዮናስ የተጠራበትን ጥሪ እምቢ በማለት ወደ ተርሰስ ከተማ ለመኮበለል ተነሣ፡፡ (ዮና፡ 1፥3)

ዮናስ ወደ ባህር ውስጥ ከተጣለ በኋላ በታላቅ ዓሣ ነባሪ ሆድ ውሰጥ ገባ፡፡ (ዮና፡1፥17)

ዮናስ በዓሣ ሆድ ውስጥ ሶስት ቀንና ሶስት ለሊት ከቆየ በኃላ የንሰሃ ፀሎት ፀለየ፡፡ (ዮና.2፥1-9)

ከንሰሃ በኃላ

ዮናስ ከዓሣ ነባሪ ሆድ ውስጥ ወጣ፡፡ (ዮና፡ 2፥10)

ዮናስ የነኔዌ ከተማ በ3 **ቀን እንደምትገለበጥ የፍርድ ቃል አወጀ፡፡** (ዮና፡ 3፥1-10)

ዮናስ እግዚአብሔር ነኔዌን ስላልፈረደ ተጠራጠረ፡፡ (ዮና፡ 4፥1-3)

ዮናስ በቅል ተክል በኩል የእግዚአብሔርን ፍቅር ተረዳ፡፡ (ዮና፡ 4፥4-11)

ዮናስ የራሱን መጽሐፍ ጻፈ፡፡ (ዮና፡ 1፥1-4፥11)

ዮናስ ወደ ነኔዌ ከተማ ሄዶ የንሰሐን ስብከት እንዲሰብክ ከእግዚአብሔር ጥሪ የተቀበለ ሰው ሲሆን እግዚብሔርን ሳይታዘዝ ወደ ተርሰስ ከተማ ለመሄድ በመርከብ ውስጥ ገባ፡፡ (ዮና፡1፥2,3) **ዮናስ የፈረንጅ አገር የሆነችው ነኔዌ ለወንጌል ሥራ ጥሩ እንዳልሆነች በራሱ ሀሳብ ተረድቶ የእስራኤል ሰዎች ወደ ሚኖሩባት ወደ ተርሰስ ከተማ ለመሄድ አሰበ፡፡** (ዮና፡ 4፥1-3)

ዮናስ ወደ ነነዌ የሚወስደውን መርከብ ትተው ወደ ተርሰስ የሚወስደውን የመርከብ ትኬት ከቆረጠ በኋላ ጉዞ እንደጀመሩ ብዙ ማዕበል በባህር ላይ ሲነሣ ከሕዝቡ ጩኸት

የተነሣ የራሱን ኃጢአት አልካደም ከዚህ የተነሣ ወደ ባህር አንስታችሁ ጣሉኝ አለ፡፡ (ዮና፡ 1፥22)

ዮናስ በባህር ውስጥ ከተጣለ በኃላ እግዚአብሔር ዮናስን የሚውጥ ዓሣ አዘጋጅቶ ስለነበረ ዓሣው ዮናስን ዋጠ፡፡ ዮናስ በዓሣ ሆድ ውስጥ ሶስት ቀንና ሶስት ሌሊት ከቆየ በኃላ ወደ እግዚአብሔር የንሰሃ ፀሎት ፀለየ እግዚአብሔርም ትልቁን ዓሣ ዮናስን ወደ የብስ አውጥቶ እንዲተፋ አዘዘ፡፡

ዮናስ ከዓሣ ሆድ ከወጣ በኃላ እግዚአብሔር ወዳዘዘው ወደ ነነዌ ከተማ ሄዶ የንሰሃን ስብከት ሰበከ፡፡ ዮናስ በመጀመሪያ ወደ ፈረንጅ አገር ወደ ነኔዌ ሄዶ እንዲሰብክ ጥሪውን ተቀበለ፡፡ እርሱም የፍርድን ስብከት ከሰበከ በኋላ የነኔዌ ሕዝብ ንሰሐ ገቡ፡፡ (ዮና፡ 3፥1-10)

ዮናስ በዓሣ ነባሪ ሆድ ውስጥ 3 **ቀንና ሶስት ሌሊት ቆይቶ መውጣቱ የሚገልጸው ኢየሱስ ክርስቶስ በመቃብር ውስጥ** 3 **ቀንና** 3 **ሌሊት ቆይቶ እንደሚነሣ የሚገልጽ ነው፡፡** (ማቴ፡ 12፥40)

እግዚአብሔር ለመልዕክተኞች የራሱን እቅድ ሲሰጥ እምቢ ሲሉ እነርሱን አስተውሎ ጥሪውን እንደገና የሚሰሩበትን ሁኔታ ይፈጥራል፡፡ ስለዚህ በሮሜ፡ 8፥28 **ላይ የተገለጸው ቃል መመሪያ ይሆናል፡፡ ቃሉም "እግዚአብሔርን ለሚወዱት እንደ አሳቡም ለተጠሩት ነገር ሁሉ ለበጎ እንዲደረግ እናውቃለን" ይላል፡፡ እኛ እግዚአብሔር በሚሰራበት ጊዜ ባንረዳም ቃሉ የሚለውን መታዘዝ ያስፈልጋል፡፡**

ዮናስ ከእግዚአብሔር ሸሽቶ ወደ ተርሰስ በመርከብ ላይ ተሳፍሮ ሲሄድ ማዕበሉ ተነሣ ከዚያም በኋላ ብዙ ንብረቶች ከወደሙ በመርከቡ ላይ ያሉት ሰዎች እያንዳንዳቸው የየራሳቸውን አምላክ ጠርቶ ንሰሐም ከገቡ በኋላ ይህ ነገር በማን ምክንያት እንደመጣ ለማወቅ እጣ እንጣጣል ብሎ ዕጣ ሲጥሉ ዕጣውም በዮናስ ላይ ወደቀ፤ በመርከብ ውስጥ ያሉት ተሳፋሪዎች ዮናስን ጠይቀው የዮናስን ማንነት ከተረዱ በኋላ እንደ ሀሳቡ ወደ ባህር አንስተው ጣሉት፡፡ (ዮና፡ 1፥15,16)

በሕይወት እያሉ የእግዚአብሔርን ፈቃድ እምቢ ለሚሉት ሰዎች መከራና ችግር ይደርስባቸዋል፡፡ ስለዚህ የሰላምን ሕይወት ለመኖር የሚፈልጉ ሰዎች የራሳቸውን መርከብ መሪ ሆነ የራሳቸውን ሁሉንም ነገር ለጌታ መስጠት የጥበብ መንገድ ነው፡፡ (ምሳ፡ 16፥3,9)

የነኔዌ ሰዎች ንሰሐ ገብተው ከፍርድ ስለዳኑ ዮናስ አይቶ ተቆጣ፡፡ ነገር ግን እግዚአብሔር ክፉ ሰዎች ወደ እርሱ በንሰሐ ሲመለሱ ይደሰታል፡፡ (ሕዝ፡ 18፥23) **እኛ ኃጢያተኞች ንሰሃ እንዲገቡና ወደ እግዚአብሔር እንዲመለሱ ብዙ ልንፀልይላቸው ያስፈልጋል፡፡**

ሐዋ.20÷24 “**ይሁን እንጂ ከጌታ ኢየሱስ የተቀበለሁትን ሩጫዬንና የእግዚአብሔር የፀጋ ወንጌል የመመስከር አገልግሎቴን ብፈፅም ለእኔ ህይወቴ ከምንም እንደ ማይቆጠር እንደ ከንቱ ነገር ናት፡ ፡**”

ምዕራፍ አስራ ስድስት

የእስራኤል እናት ዲቦራ (መሳ፡ 4፥1-10)

የዲቦራ ልደት

ዲቦራ ለፈደትን አገባች፡፡ (መሳ፡ 4፥4)

ዲቦራ መስፍን ከሆነች በኃላ

እስራኤላዊያን ዲቦራ መስፍን እንድትሆን ጠሩ፡፡ (መሳ፡ 4፥4)

ዲቦራ በኤፍሬም አገር እስራኤላዊያንን መራች፡፡ (መሳ፡ 4፥5)

ዲቦራ ለባርቅ ስለ እስራኤል ሕዝብ ሄደህ እንድትዋጋ ብላ ጠራች፡፡ (መሳ፡ 4፥6-7)

ዲቦራና ባራቅ የኢያቢስ ሠራዊት አለቃ የሆነውን ሲሣርን አሸነፉ፡፡ (መሳ፡ 14፥14-24)

ዲቦራ የድል ዝመሬን ዘመረች፡፡ (መሳ፡ 5፥1-31)

ዲቦራ እስራኤላዊያንን ለ40 **ዓመት መራች፡፡** (መሳ፡ 5፥31)

ዲቦራ መስፍን ናት መሳፍንት የእስራኤላዊያን ወኪሎች ናቸው፡፡

መሳፍንት በውጊያ ጊዜ የሠራዊቱ መሪ ናቸው፡፡ የእስራኤል መሳፍንት 14 **ናቸው፡፡ ነገር ግን ከመሳፍንቱ ውስጥ ሴት የሆነችው አንዷ ዲቦራ ናት፡፡ ኢያሱ ከሞተ በኃላ ሳሙኤል ሳኦልን ንጉሥ አድርጐ እስከ ሚያቆም ድረስ** 450 **ዓመታትን ፈጀ፡፡ በዚህ ቆይታ እስራኤላውያን እግዚአብሔርን ሰባት ጊዜ ካዱ፡፡ ነገር ግን እግዚአብሔር ሁሉንም ይቅር አላቸው፡፡**

እስራኤላዊያን እግዚአብሔርን ከካዱት ከሰባቱ ክህደቶች መካከል አንዱ ዲቦራ የኖረችበት ጊዜ ነው፡፡ እስራኤላውያን እግዚአብሔርን ትተው ባኦልን (ጣአት) አምላኪዎች ሆኑ፡፡ ከዚህ የተነሣ የመጨረሻ ውጤቱ ከከነዓን ንጉሥ ከኢያቢስ ጋር ጦርነት ተፈጥሮ ብዙዎች በአደጋ ላይ ወደቁ፡፡ በዚህ ጊዜ ዲቦራ በእምነት ከእግዚአብሔር እውቀትና ጥበብ ስለተቀበለች የከነአን ንጉሥ ኢያብስ አሸንፉ ደግሞም የእስራኤል ሰዎች አስተማሪና ለችግሮቻቸው መፍትሄ የምትሰጥ ሴት ሆና የእናትነትን ክብር አገኘች፡፡ (መሳ፡ 5፥7)

እግዚአብሔር ለዲቦራ የከነዓን ንጉሥ የኢያቢስን ሠራዊት አሳልፎ ሰጠ፡፡ ዲቦራ ይህንን ለባራቅ ነገረች፡፡ በዚህን ጊዜ የኢያቢስ አለቃ ሠራዊት በጣም ኃይለኛ ሰረገላዎች በቁጥር 900 የሚሆኑ አሉ፡፡ ነገር ግን የእስራኤል ሠራዊት ጠራቸው በጣም ትንሽ ነበር፡፡ (መሳ፡ 5፥7,8) ነገር ግን እግዚአብሔር ከዲቦራና ከባራቅ ጋር ስለሆነ የኢያቢስን ሠራዊት ድል አደረጉ፡፡ ዲቦራ ሴት በተፈጥሮዋም ደካማ ናት፡፡ ነገር ግን እግዚአብሔር ከዲቦራ ጋር ስለሆነ እውቀትንና፣ ጥበብን እንዲሁም ድፍረትን ሰጥቶ እንድታሸንፍ አደረገ፡፡ (1ቆሮ፡ 1፥27) ዛሬ እግዚአብሔር ከዲቦራ ጋር እንደሆነ በእምነት የሚታዘዝና የሚያደረግ ሰውን ይፈልጋል፡፡ እኛም እንደ ዲቦራ የእግዚአብሔር ቃል ስንታዘዝ እግዚአብሔርን ልንጠቅም እንችላለን፡፡

ዲቦራ የእስራኤል ሰዎች ኃጢያትና ያለማመናቸውን ብዙ ጊዜ ለማዳን መስፍን ሆና ተመረጠች (መሳ.4፥1-4) በመስፍንነት ለ40 ዓመት እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ እስራኤልን መራች፡፡ (መሳ፡ 5፥31) ዲቦራ ሴትነቷን ሳትፈራ በመስፍንነት ቆመች፡፡ እኛ ቤተክርስቲያን እንዲመሩት ለወንዶች ብቻ ስፍራ ስንተው ዛሬም እንደ ዲቦራ ለእግዚአብሔር የሚቀኑ ሴቶች ስላሉ ለሴቶችም የመሪነትን ቦታ መስጠት ያስፈልጋል፡፡ ዲቦራ የከነዓን ንጉሥ ኢያቢስን ካሸነፈች በኋላ የዝማሬ ቅኔ ለእግዚአብሔር ዘመረች፡፡ (መሳ፡ 5፥1-31)

እኛ ደግሞ ኃጢአታችን ለእግዚአብሔር ተናዘን ለእግዚአብሔር የዝማሬ ቅኔ ልንዘምር ያስፈልጋል፡፡ ዲቦራ ራሱዋን መስዋዕት አድርጋ ለስራኤል ሰዎች ችግር መፍትሄ አምጥታ አለማመናቸውን ለመቀየር መድሀኒት ለመሆን ሞከረች (መሳ.4፥5-14 ምዕ.5፥7) እኛ ደግሞ እንደ ዲቦራ ደካሞችን ለመርዳትና በእምነት እንዲሰሩ ለማድረግ ራሳችንን ለእነርሱ አሳልፈን ልንሰጥ ያስፈልጋል፡፡

ምዕራፍ አስራ ሰባት

የጌዴዎን መታዘዝና ትህትና (መሳ፡ 7፥1-8)

መስፍን ከመሆን በፊት

ጌዴዎን የእስራኤል ሕዝብ ከምድያም ጦርነት ለማስመለጥና እስራኤላዊያንንም እንዲመራ ጥሪ ተቀበለ፡፡ (መሳ.6፥1)

ጌዴዎን ስንዴ በሚወቀጥበት ቦታ ተሸሽጐ እያለ ጥሪውን ተቀበሉ፡፡ (መሳ፡ 6፥11-16)

መስፍን ከሆነ በኃላ

ጌዴዎን እግዚአብሔርን ስለመጥራቱ ለማረጋገጥ ተአምራት እንዲያደርግ ጠየቀ፡፡ (መሳ፡ 6፥17-21)

ጌዴዎን የእግዚአብሔርን መላአክ በመንገድ ላይ ካየ በኃላ ለእግዚአብሔር መሠውያ ሠራ፡፡ (መሳ፡ 6፥22-24)

ጌዴዎን የባአል መሰውያ ስፍራ አፈረሰ (መሳ.6፥25-32)

ጌዴዎን ለሁለተኛ ጊዜ እግዚአብሔር በበግ ፀጉር ላይ ተአምራት እንዲያደርግ ጠየቀ፡፡ (መሳ፡ 6፥36-40)

ጌዴዎን 300 **የእስራኤል ሠራዊትን መረጠ፡፡** (መሳ፡ 7፥2-7)

ጌዴዎን የምድያምን ሰዎችን አሸነፈ፡፡ (መሳ፡ 7፥19-23)

ጌዴዎንን የኤፍሬም ሰዎች መጥተው "ለምን እኛን ምድያማዊያንን ለመዋጋት አልመረጥክም" ብለው ጠየቁ መፍትሄ ሀሳብ ተናገራቸው፡፡ (መሳ፡ 8፥1-3)

ጌዴዎን የምድያም አገርን ወሰደ፡፡ (መሳ፡ 8፥4-21)

እስራኤላዊያን ጌዴዎን ከምድያም እጅ ስላዳነው እርሱ እንድገዛ ስጠይቁት እምቢ አለ፡፡ (መሳ፡ 8፥22,23)

ጌዴዎን የወርቅ ጉትቶቻቸውን ወሰዶ ለራሱ ኤፉድ ጣአት አድርጐ ሠራ፡፡ (መሳ፡ 8፥24-27)

ጌዴዎን በመጨረሻ ዓመት ብዙ ሚስቶችን አገባ፡፡ (መሳ፡ 8፥29-31)

ጌዴዎን እስራኤላዊያንን ለ40 **ዓመት መራ፡፡** (መሳ፡ 8፥28)

ጌዴዎን በኢዮአስ መቃብር ተቀበረ፡፡ (መሳ፡ 8÷32)

እስራኤላዊያን እንደገና እግዚአብሔርን በሚክዱት ጊዜ የምድያም ሰዎች እስራኤልን መውጋት ጀመሩ፡፡ እግዚአብሔር ጌዴዎንን ከምናሴ ወገን የእርሻ ስራ የሚሰራውን እስራኤላውያንን ከሚዳማውያን እጅ 5 ጊዜ ድል እንዲያደርግ መስፍን እንዲሆን ጠራው፡፡ ጌዴዎን እግዚአብሔር ለራሱ እንደለየው ለማረጋገጥ ተአምራትን ጠየቀ፡፡ እግዚአብሔር ከድንጋይ እሳት አውጥቶ የመሥዋዕት ሥጋ እንዲያቃጥል አደረገ፡፡ (መሳ፡ 6÷17-21)

ጌዴዎን ለሁለተኛ ጊዜ ከእግዚአብሔር ተአምራትን ፈለገ፡፡ እግዚአብሔርም ጌዴዎን እንዳለው በመጀመሪያ በበግ ፀጉር ላይ ብቻ ጤዛ እንድሆን አደረገ፡፡ ደግሞ ሌላውን በበግ ፀጉር ላይ ብቻ ደረቅ ሆኖ በምድር ላይ ጤዛ እንድሆን አደረገ፡፡ (መሳ፡ 6÷36-40) ጌዴዎን ከእስራኤል ሰዎች መካከል ለውጊያ ከወጡት ከ32,000 ሰዎች ለውጊያ የማይፈሩ 300 ሰዎችን ብቻ መረጠ፡፡ የምድያም ሠራዊት 130,000 (አንድ መቶ ሰላሳ ሺህ) ሰዎች ናቸው፡፡

ነገር ግን የእስራኤል ሠራዊት ሦስት መቶ ብቻ ናቸው፡፡ (መሳ፡ 8÷10) ስለዚህ እግዚአብሔር ለምን በ300 ሰዎች እነዚያን 130 ሺህ ሰዎች ጋር ጦርነት እንድጋጠም ያደርጋል? (በመሳ፡ 7÷2) ላይ ያለውን ቃል “እግዚብሔርም ጌዴዎንን ከአንተ ጋር ያለው ሕዝብ በዝቶአል ስለዚህ እስራኤል እጄ አዳነኝ ብሎ እንዳይታበይብኝ” የተባለውን ቃል ለመፈፀም ነው፡፡ በጥቂት ሠራዊት የሚያሸንፍ ማን ነው? የእግዚአብሔርን ሥልጣን በእምነት የተቀበለው ሠራዊት ግን ያሸንፋል፡፡

የእስራኤል 300 ሠራዊቶች ወደ ጦርነቱ ይዞ የሄዱት ነገር ምንድር ነው? የጦር መሣሪያ ሳይሆን እነርሱ ይዘው የሄዱት መለከትን፣ ማሰሮና፣ ችቦ ብቻ ነበር፡፡ እኛ የመንፈሳዊ ጦርነትን ለማሸነፍ የወንጌል መለከት በመንፋት እንደ ማሰሮ በእኛ እግሮቻችን በመሄድ የመንፈስ ቅዱስ እሳትን ልናቀጣጥል ያስፈልጋል፡፡ ጦርነትን ያሸነፈውን ጌዴዎንን የኤፍሬም ሰዎች ለምን እኛን አልጠራህንም ብለው ሊጣሉ ሲፈልጉ ጌዴዎን ትሁት ስለሆነ የሚያስታርቅ ቃል ተናገረ፡፡ (መሳ፡8÷1-3)

ከውጊያ በኃላ የእስራኤል ህዝብ ጌድዮንና የጌድዮን ልጆች ህዝቡን እንዲመሩ ሲጠሩ ነገር ግን ጌድዮን ለህዝቡ እግዚአብሔር እራሱ ይግዛ እኔና ልጆቼ አንገዛም በማለት መልስ ሰጣቸው፡፡ (መሳ.8÷22-23)

ጌድዮን በጦርነት የሚረካቸውን ወርቅ ከሰዎቹ ወስዶ ለራሱ ኤፉድ አድርጐ ሠራ፡፡ (መሳ.8÷27) ጌዴዎን ብዙ ሚስቶችን አገባ፡፡ የልጆቹም ቁጥር 70 ነበር፡፡ ከ70ዎቹ አንዱ ሌሎች ልጆችን ሁሉ ገደላቸው፡፡ ጠላቶቹን ካሸነፈ በኃላ ጌድዮንና ቤተሰቦቹ

ለእግዚአብሔር ነገር ምንም አልተጠነቀቁም፡፡ ጌዴዎን ከሞተ በኋላ እስራኤላውያን የጌድዎን ቤተሰብን አላከበሩትም፡፡ (መሳ.8፥33-35)

የጌዴዎን ሠራዊት 300ዎቹ የምዲያም ሠራዊት 130,000 ሠራዊትን ከእግዚብሔር ጋር በመሄድ አሸነፉ፡፡ (መሳ.7፥2-23) ደግሞም እኛ እግዚአብሔርን ስናይና ስናምን በእግዚአብሔር መንግሥት ላይ የሚነሳውን ማንኛውንም ብዙ የመሰለውን ሠራዊት ማሸነፍ እንችላለን፡፡ (ፊልጵ፡ 4፥13) ላይ “ኃይልን በሚሰጠኝ በክርስቶስ ሁሉን እችላለሁ፡፡”

አሸናፊው ጌዴዎን ኤፉድን (ጣአት) ካሰራ በኃላ ለራሱ ብዙ ሚስቶች አገባ፡፡ (መሳ.8፥24-31) እኛ ደግሞ እግዚአብሔር በእኛ ትልቅ ሥራ ካደረገ በኋላ እንዳንታበይ ሁልጊዜ ልባችንን ልንመረምር ያስፈልጋል፡፡ (1ቆሮ፡ 10፥12) “ስለዚህ እንደቆመ የሚመስለው እንዳይወድቅ ይጠንቀቅ” ተብሎ ተጽፏልና፡፡

እስራኤላውያን በመከራቸው ጊዜ ወደ እግዚአብሔር ሲፀልዩ እግዚአብሔር ጌዴዎንን ከምዲያም እጅ እስራኤላውያንን እንዲያድን መረጠ፡፡ (መሳ፡ 6፥16) አሁን እኛ በመከራ ውስጥ ነን? ወደ እግዚአብሔር ብንጸልይ እግዚአብሔር መልስን ይሰጠናል፡፡ (ኢሳ፡ 58፥9)